ለዐድዋ ድል መዘክርነት የሚገነባው ማእከል የጥቁር ሕዝቦችን

ተረፈ ወርቁ

የእናንተው ” ኢብአዜ ፓርቲ!¡

በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

አመጣጣችን ለዶ/ር ነጋሶ ምስጋና ለማቅረብ ነበር

እየሩሳሌም አርአያ



## አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ስለ አዲሱ ፓርቲ ምን አሉ?


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 55 ግንቦት 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99



## የህወሃት አጣብቂኝ

ጌታቸው አሰፋን መስጠት¡ ወይ አለመስጠት¡



## የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ

# ከአዲሱ ፓርቲ ምን እንጠብቅ?



“የእኛ ፖለቲካ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን”

(አቶ ኦቻን ኦጋቱ)



“ማህበራዊ ፍትህን በሀገሪቱ ለማስፈን እንሰራለን”

(አቶ ኑሪ ሙደሲር)



“የተዋሃድነው መግለጫ ለማውጣት ሳይሆን ተወዳድረን ለማሸነፍ ነው”

(አቶ የሺዋስ አሰፋ)



“ራሳችንን ሳይሆን ሀገርን ማስቀደም አለብን ፤በሚለው ተስማምተን ዛሬ ላይ ደርሰናል”

(አቶ አንዷለም አራጌ)



“እየተሰባሰቡ መበታተንን በአዲስ አደረጃጀት ቀርፈነዋል”

(ዶ/ር ጫኔ ከበደ)



“አማራጭና የተሻለ የፖለቲካ ፕሮግራም ይዘን ቀርበናል”

(አቶ አዲስ ዳንኤ)

# ማውጫ

2
ኢሳትን ለባለቤቱ መልሰናል

12
የስልጣኔ ደወል

18
ብፅዕ ዶ/ር አቡነ ገሪማ ማን ናቸው?

21
የነጻው ፕሬስ ጉዞ ከየት ወዴት?



3
የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ

ከአዲሱ ፓርቲ ምን እንጠብቅ?

8
የዜግነት ፖለቲካና የፓርቲዎች ውህደት ለ"ታመመች ኢትዮጵያችን" መዳኛ!

19
ጆን ሚሊ ኢትዮጵያውያንን እየረዳ ፤ በኢትዮጵያዊ የተገደለው ዶክተር!

22
ሰሚ ያጣ ጩኸት

25
የመንግስት ጋዜጠኞች ማህበር 50ኛ ዓመታቸውን አከበሩ
የነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር አልባ ሆነዋል




ቁጥር 54 ዕትም

ግዮን

ቀጣዩ ዕትም ግንቦት 10 ይጠብቁን

# ኢሳትን ለባለቤቱ መልሰናል

አርበኞች ግንቦት 7 ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ለመጀመር ከወሰነ ጀምሮ ከሁሉም ነገር ቅድሚያ ሰጥቶ የተንቀሳቀሰው በህዝብና በሃገር ላይ ያሰፈሰፈውን አደጋ ህዝብን በማሳተፍ መቋቋም የሚችል አንድ ጠንካራ ሃገራዊ ፓርቲ በመመስረቱ ተግባር ላይ ነው። ንቅናቄው በማህበራዊ ፍትህና በዜግነት ፖለቲካ ላይ ጽኑ እምነት ካላቸው ድርጅቶች ጋር ተነጋግሮ ለአንድ ትልቅ ሃገራዊ ፓርቲ መመስረት ስምምነት ላይ የደረሰው ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ለማድረግ ወስኖ ወደ ሃገር ቤት በገባ በመጀመሪያው ወር ውስጥ ነው። በወቅቱ ከንቅናቄው ጋር ሌሎች ድርጅቶች ያደረጉት ስምምነት አዲሱ ፓርቲ በሚያዚያ ወር ምስረታው ተጠናቆ በፍጥነት እንቅስቃሴ እንዲጀምር ነበር። ይህን ትልቅና አጣዳፊ አጀንዳና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት አግ7 ሚያዚያ 29 ቀን በአዲስ አበባ ከተማ ከመላው ኢትዮጵያና ከሌሎች የአለማችን ክፍሎች የተሰበሰቡ አባላቱ በተገኙበት ጠቅላላ ጉባኤ በማድረግ የሚከተሉትን ውሳኔዎች በማሳለፍ ጉባኤው በስኬት ተጠናቋል።

**1.** ንቅናቄው ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ለማድረግ ወደ ሃገር ቤት ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ራሱን ወደ ፓርቲነት ለመቀየር ያከናወናቸውን ተግባራት በመገመገም፣ እራሱን ወደ ላቀ ሃገራዊ ፓርቲ ለመቀየር ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የገባውን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲችል፣ ራሱን አክስሞ በግንቦት 1 እና 2 በተጠራው በሰባት ድርጅቶች ውህድት የሚፈጠረው አዲስ ፓርቲ አካል እንዲሆን ወሳኔ አሳልፏል። ውሳኔው በ 243 ድጋፍ፣ በ18 ተቃውሞና በ14 ድምፀ ተአቅቦ አልፏል።

**2.** ከኤርትራ በረሃ የተመለሱ የሰራዊትና ከእስር የተፈቱ አባላቱን፣ እንዲሁም በሃገር ውስጥ ነፍጥ አንስተው ሲታገሉ የነበሩ ታጋዮቹን የመልሶ ማቋቋሙን ስራ አዲስ የሚመሰረተው ፓርቲ በሃላፊነት እንደሚረከበው፣ ይህም ወሳኔ የአዲሱ ፓርቲ መስራች ድርጅቶች መሪዎች ቀድመው የተስማሙበት ጉዳይ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ይህንን የመልሶ ማቋቋም ስራ እስካሁን በሃላፊነት ሲከታተል የነበረው የአግ7 ጸሃፊ በሃላፊነት እንዲከታተሉ የቀረበውን የውሳኔ ሃስብ በሙሉ ድምጽ ጉባኤው አሳልፎታል። ከዚህ ውሳኔ ጋር ጉባኤው ለሰራዊቱ አባላትና ሰራዊቱ ተልእኮ ሰጥቷቸው በጠላት እጅ ወደቀው በእስር ሲማቅቁ ለነበሩ አባላት የተለያዩ ፍላጎቶች ወጪ መሸፈኛ እንዲሆን 300.000 ሶስት ሚሊዮን ብር በአደራ እንዲቀመጥ ወስኗል። ይህ ገንዘብ የመልሶ ማቋቋም ኮሚሽን ለማይሸፍናቸው አልባሳትን ለመሳሰሉ ነገሮች ወጪ የሚሆን ይሆናል።

**3.** በኤርትራ ምድር የተሰዉ 65 የቀድሞ የአርበኞች ግንባር አባላትና ግንባሩ ከግንቦት 7 ጋር ከተዋሃደ ቦኋላ በአደጋና በህመም የተሰዉ 3 አባላትን በድምሩ የ68 ታጋዮችን አጽም ከኤርትራ አንገኦ፣ በሃገር ወስጥ ለግዳጅ ተሰማርተው ከተሰዉ የስራዊት አባላት አጽም ጋር በአንድ ቦታ እንዲያርፍና በቦታው የመታሰቢያ ሃውልት ለመስራት የሚሆን ወጪ 1.000.000 አንድ ሚሊዩን ብር በአደራ እንዲቀመጥ ወስኗል።

**4.** ህጻናት ልጆቻቸውንና ተጧሪ ቤተሰቦቻቸውን ትተው ትግሉን ከተቀላቀሉ ቦኋላ ለተሰዉ የታጋዮች ቤተሰብ ለማገዝ 5.000.000 ብር በአደራ ተያዞ በአስቸኳይ እንዲከፋፈል ወስኗል።

**5.** የንቅናቄውን ሃብትና ንብረት በሚመለከት

5.1. ጉባኤው በአደራ እንዲያዝ ከወሰነው ገንዘብ የሚተርፈው የንቅናቄው ገንዘብ በሙሉ አዲስ ለሚመሰረተው ፓርቲ እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

5.2. የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥዮንን (ኢሳት) በተመለከተ የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ አፋኝ ስርአት የሚደርስበትን የመረጃ አፈና ለመበጣጠስና በኢትዮጵያ ውስጥ ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ለማገዝ የግንቦት ንቅናቄ ኢሳትን ማቋቋሙን ለመጀመሪያ ጊዜ በጉባኤና በአደባባይ ግልጽ በማድረግ፣ የኢሳት ባለቤትነት ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት እንዲያገኝ በማሰብ፣ ኢሳት ከተመሰረተ ጀምሮ አብዛኛውን የገንዘብ፣ የመረጃና የቴክኒክ ድጋፍ ሲያገኝ የነበረው ከህዝብ መሆኑን በመገንዘብ፣ ሲያገለግልም የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ አይናና ጆሮ ሆኖ ስለነበር፣ የወደፊቱ የሚሻሻለው የሃገሪቱ የሚዲያ ህግ በሚፈቅደው አዲስ አሰራር መሰረት የኢሳት ባላቤት የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲሆን፣ ተቋሙም አትራፊ ያልሆነ ማህበራዊ ድርጅት ሆኖ እንዲመዘገብ፤ ኢሳት ሲያገለግላቸው የኖሩትን የሃገሪቱን ዜጎች በሙሉ የሚወክል ስፋትና ስብጥር ያለው ቦርድና የማህበር አባላት ያሉት ሃገራዊ ተቋም ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲደራጅ፣ ይህንን የሽግግር ስራ በወቅቱ ኢሳትን የሚያስተዳድሩ የቦርድ አባላት ከግቡ እንዲያደርሱት፣ ይህን ተቋም አዲሱ ፓርቲ በባለቤትነት የሚወርሰው ተቋም ስለማይሆን፣ ንቅናቄው ሲፈርስ የጉቤውን ውሳኔ በባለቤትነትና በበላይነት የሚያስፈጽም አካል ክፍተት እንዳይኖረው በማሰብ፣ አሁን ያለው የኢሳት ቦርድ የጀመረውን የማሸጋገር ስራ ተከታትሎ የሚያስፈጽም ኮሚቴ መኖር አስፈላጊነቱን በማመን፣ አዲሱ ፓርቲም በማያውቀው ጉዳይ ሃላፊነት ውስጥ ገብቶ ችግር ላይ እንዳይወድቅ በመስጋት፣ የሚቋቋመው ኮሚቴ አባላት ኢሳትን ከምስረታው ጀምሮ የሚያውቁት፣ ኢሳትን ነጻና ገለልተኛ ተቋም ለማድረግ የሚያስችል አቅም፣ ብቃትና የመርህ ጥብቅነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል በሚል እሳቤ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን፣ አቶ መአዛህ ታፈሰን፣ አቶ ሲሳይ አጌናንና አቶ ፋሲል የኔአለምን የኮሚቴው አባላት ሆነው እንዲሰሩ ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

5.3. ነጻነት አሳታሚዎችን በተመለከተ ነጻነት አሳታሚ የራሱ እሴት የሌለው፣ ስራው መጽሃፍ በማሳተም ለንቅናቄው የገንዘብ ግቢ ማሰባሰብ መሆኑን ግልጽ በማድረግ፣ ነጻነት አሳታሚዎች ሙሉ በሙሉ የአዲሱ ፓርቲ ንብረት ሆኖ እንዲተላለፍ፣ በወቅቱ ነጻነት አሳታሚዎች የጀመራቸውን ስራዎች ማስፈጸሚያ የሚሆን ገንዘብ ሁሌም ሲደረግ እንደነበረው በንቅናቄው እጅ ካለው ገንዘብ እንዲመደብለት፣ ከእነዚህ ስራዎች የሚሰበስበውን ማናቸውንም ገቢ ተጠያቂነትና ግልጽነት ባለው መንገድ ለአዲሱ ፓርቲ ገቢ እንዲያደርግ፣ የነጻነትን አሳታሚዎች ልምድና ኤክስፐርቲዝ በመጠቀም አዲሱ ፓርቲ አሳታሚ ብቻ ሳይሆን ራሱ የህትመት ስራ ውስጥ መሳተፉ ከፍተኛ ድርጅታዊ ጥቅም እንደሚኖረው በማሳሰብ፣ ከላይ የቀረቡትን ከነጻነት አሳታሚ ድርጅት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የውሳኔ ሃሳቦች ጉባኤው በሙሉ ድምጽ አሳልፏል።

በመጨረሻም ጉባኤው፣ “ሰው በጠፋበት ወቅት ሰው ሆነው ለተገኙ ሃገር ወዳድ የንቅናቄው አባላትና ደጋፊዎች በንቅናቄው ስም ያዘጋጀውን የእውቅና ሰነድ ይፋ በማድረግና ከአግ7 ጋር በመሆን በአዲስ አበባ ከተማ ከግ 1 እስከ ግንቦት 2 በሚደረገው ሃገራዊ ስብሰባ ላይ አዲስ ፓርቲ ለመመስረት ራሳቸውን ካከስሙ የቀድሞ ስደስት ድርጅቶች ሊቃነመናብርት የእንኳን ደስ ያላችሁ መልእክት በማዳመጥ በከፍተኛ ስሜትና ስኬት ተጠናቋል። ዘላለማዊ ክብር፣ ለዜጎች ነጻነት ለወደቁ ሰማእታቶቻችን፤ ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!

በፅናትና በትግስት ከንቅናቄያችን አግ7 ጋር ለቆያችሁ ውድ አመራሮችና አባላት እንኳን ደስ ያላችሁ የሚያኮራ ድርጅት የሚያኮራ ስራ ሰርቶ ከስሟል።

የአርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ዴሞክራሲ ንቅናቄ ሚያዚያ 29 2011 ያደረገውን ጠቅላላ ጉባኤ አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ ሚያዚያ 29/2011

***የአርበኞች ግንቦት 7 ንቅናቄ የመጨረሻው ጠቅላላ ጉባኤ አዲስ አበባ***

## የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ

# ከአዲሱ ፓርቲ ምን እንጠብቅ?

ስድስት የዜግነት ፖለቲካን መሰረት ያደረጉ ፓርቲዎች፣ እንዲሁም የቀድሞው አንድነት ፓርቲ አመራሮችን ያቀፈ ቡድን፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አንድ ወጥ ፓርቲነት ለመለወጥና ውህደት ለመፍጠር፣ ከስምምነት ላይ የደረሱት ከወራት በፊት እንደነበር ይታወሳል። በዚህም መሰረት ለግዙፉና በያዝነው ሳምንት መገባደጃ ይፋ ለሆነው አዲስ ፓርቲ ምስረታ ዕውን መሆን፤ ሰማያዊ ፓርቲ አስቀድሞ ሲከስም፣ ቀሪዎቹ ፓርቲዎችም እስከ ሚያዝያ 29 ቀን ድረስ ሙሉ ለሙሉ ራሳቸውን በማክሰም ቀደምት ፓርቲያቸው በ"ነበር" እንዲቀር አድርገዋል።



የውህዱ ፓርቲ ምስረታ ግንቦት 1 ቀን 2011 ዓ.ም ለህዝብ ይፋ ከመሆኑ አስቀድሞ ሰኞ ሚያዝያ 28/2011 ዓ.ም በአዲስ ቪው ሆቴል በተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ፤ ፓርቲዎቹ ለጥምረትና ለውህደት ቅድመ ስምምነት ሲያደርጉ ዜግነትን መሰረት ያደረገ ፖለቲካን የሚያራምድ፣ በዛ ውስጥም ማህበራዊ ፍትህ እንዲሰፍን ጠንክሮ የሚሰራ አንድ ወጥ የሆነ ፓርቲ የመመስረት ዓላማን አንግበው በመሆኑ፤ በፖሊሲ ረገድ ፓርቲዎቹን ሙሉ ለሙሉ የሚያግባቧቸው ነጥቦች የገዘፉ በመሆናቸው፤ ሁሉም ቡድን ቀደምት ፓርቲያቸውን በማክሰም ወይም ደግሞ ሙሉ በሙሉ በመሰረዝ ወደ ውህደትና አንድነት እንዲመጡ ያስቻላቸው መሆኑን ይፋ አድርገዋል።

ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ወሳኝ መርህዎችን መሰረት ያደረገ ውይይት በሁሉም አባላት ፓርቲዎች ፊት ተደርጎ፤ እውነተኛ መግባባት ላይ መድረስ መቻሉ የውህድ ፓርቲውን ምስረታ እውን መሆን አፍጥኖታል። ከዚህ ቀደም የተለያዩ ሀገራዊ ፓርቲዎች ህብረት በመፍጠር፣ በጋራ ለመስራት ያደረጉት ጥረት ፍሬያማ ሊሆን ያልቻለበትን፤ ፓርቲዎችም ባለመግባባት ወደ መበታተንና ቀድሞ የነበሩበት የተናጠል ጉዞ የሚያመሩት ለምንድን ነው? በሚል ሰፊ ጥናት ከተደረገ በኋላ፤ ወረዳን መሰረት አድርጎ፣ የወረዳ አባላት የሚቆጣጠሩበት መዋቅር ተዘርግቶ፣ ማንኛውም ፓርቲ ውስጥ ያለ ውክልና ከወረዳ እንዲመነጭ ተደርጎ መሰራቱና መደራጀቱ የተሻለ መፍትሄ እንደሆነ ስለታመነበት፣ ፓርቲዎችን በጥቂት ሰዎች ቀጥጥር ስር አድርጎ ከመጓዝ መንገድ በወጣ መልኩ የአዲሱ ፓርቲ አመራሮች ከስር ጀምረው እየተመረጡ እንዲመጡ ተደርጓል፡ ፡

"ለበርካታ ዓመታት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ተሳትፌያለሁ። ግን ካሳለፍኩት ተሞክሮ አንፃር ይሄኛው አካሄድ ለየት ያለ ነው። እንኳን ስድስት ፓርቲዎችና አንድ የቀድሞ ስብስብ አይደለም፣ ሰባት ሰዎች አንድ ላይ ሆነው የሰመረ ነገር መስራት በእኛ ሀገር ባህል ብዙ የተለመደ አይደለም" ያሉት የቀድሞ የአንድነት ፓርቲ አመራር አቶ አንዷለም አራጌ፤ አሁን በፍፁም ወንድማዊነትና መግባባት እንዲሁም አንድ ዓላማ ከፊት ለፊት በማስቀመጥ፤ ያንን እውን ለማድረግ በቅን መንፈስ የተሰባሰቡ ከመሆናቸው አኳያ አንዳችም የሚሻክር ስሜት በሁሉም ላይ ሳይፈጠር የፓርቲውን ምስረታ ዕውን ለማድረግ እንደተዘጋጁ ይፋ አድርጓል።

የቀደሞ አንድነት አመራሮችን በተመለከተም ከማንም ግለሰብ ሆነ ቡድን ጋር ጭቃ የመቀባባት ፍላጎት እንደሌላቸው የተናሩት አቶ አንዷለም አራጌ የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግሮች አንጥሮ በማውጣት፣ በመፍትሄዎቻቸው ላይ መስራት እንጂ በእንካሰላንቲያ ጊዜ የማጥፋት እሳቤ እንደሌላቸው፣ እንዲህ አይነቱ አካሄድም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባህል መሆን እንደሌለበት ጭምር በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ የገለፁትና በሚመሩት አንድነት ፓርቲ ምክንያት ለሰባት ዓመታት ያህል ለዕሥር የተዳረጉት የቀድሞ አንድነት ፓርቲ ም/ፕሬዝዳንት አቶ አንዷለም አራጌ "በአሁኑ ሰዓት‹ አንድነት ፓርቲ እየተባለ ቢነገርም፣ ስለመኖሩ ፈፅሞ አላውቅም፤ አለ ብዬም አላምንም። ይህ ባለበት ሁኔታ እኔ ራሴን የቀድሞ አንድነት ፓርቲ አመራር አባል ብዬ መጥራቴ ለምን ጥያቄ እንደሚያጭር አልገባኝም" ሲሉ ተናግረዋል።

በየአካባቢው የሚነሱ ግጭቶችን በተመለከተ መግለጫ የማውጣትና ያለማውጣት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሰው የሆነ ሁሉ የሚያዝንበት፣ የሚያነባበት፤ በውስጡ የሚቆስልበት ክስተት በሀገራችን እየታየ በመሆኑ ከማዘን ባሻገር፤ መፍትሄውን ለማፈላለግ በእጅጉ እንደሚጨነቁ የገለጹት አቶ አንዷለም አራጌ "በጉዳዩ ላይ ለምን መግለጫ አላወጣችሁም ከሆነ፣ ዞሮ ዞሮ ችግሩ እኛ ትኩረታችንንም ሸሚዛችንንም ሰብስበን የምንገባበት ጉዳይ ነው፡ ፡ በመሆኑም ወደ ፊት በእያንዳንዷ ጉዳይ ላይ ትኩረት ሰጥተን፣ የፖሊሲ አቅጣጫ ሳይቀር በአማራጭነት ቀርፀን እናቀርባለን" ብለዋል።

"ለብዙ ጊዜያት ፓርቲዎች ሲጣመሩ እናያለን፣ ሲፈርሱም እናያለን። ይሄኛው የእኛ ውህደት ግን ከዚህ ሙሉ በሙሉ ይለያል። የፖለቲካው ዓለም እንደምናውቀው እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል ሊሆን አይችልም። ግን ለዚህች ሀገር ምን ይሻላል? ምን ያዋጣል? የሚሉ ነጥቦችን ይዞ አብሮ መጓዝ ግን ይቻላል። እኛም ሀገራችን ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ይዘን ልንራመድ በሚገባን የዜግነት ፖለቲካ ላይ በመግባባታችን ወደ ውህደት መጥተናል" የሚሉት የጋምቤላ ክልላዊ ንቅናቄ ፓርቲ ኃላፊ ይህን ፓርቲ ከወዲሁ አላስፈላጊ ግምት መስጠትና ይፈርሳል ብሎ መተንበይ ዘበት ነው፡ ፡ ፍፁም የሆነ መግባባትና እውነተኛ የሀገር ➔

ፍቅር ላይ መሰረታችንን ያፀናን በመሆኑ ይሄ ለሰከንድም አያስጨንቀንም" ሲሉ አቋማቸውን በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ አስረድተዋል፡፡

ወረዳን መሰረት ያደረገ ምስረታ ሲባል፤ ግንቦት ሰባት ይሁን ሰማያዊ አልያም የኢዴፓና የሌሎች ፓርቲ አባሎች አንድ ላይ ሆነው ጉባኤ በማድረግ፤ ስራ አስፈፃሚዎችን በመምረጥ ባለፉት ወራት ፓርቲዎችን የማዋሃድ፣ ደንብና ፕሮግራም ላይ የማወያየት እንዲሁም ስልጠና የመስጠትና የጉባኤ ተወካዮችን የመምረጥ ስራ እንደተከናወነ ያመላከቱት ዶ/ር ጫኔ ከበደ በበኩላቸው በየወረዳው በሚመረጡ የጉባኤው ተወካዮች ውስጥ ሴት አባላትን በተቻለ መጠን ለማካተት በጥልቀት እንደተሰራ ብሎም አካል ጉዳተኞች በወረዳው ካሉ በጉባኤ ተወካይነት እንዲያዙ እንደ መስፈርት በማስቀመጥ ጭምር ትልቅ የምስረታ ስራ በጥልቀት መከናወኑ ገልፀዋል፡፡

አዲሱን ፓርቲ በውህደት ለመፍጠር ስብሰባ ሲጀምር በምርጫ መሸነፍና ማሸነፍ የስብሰባ ስኬት መለኪያ እንዲሆን ታስቦ ሳይሆን፣ ዘላቂ የሆነና የተረጋጋ ዴሞክሲያዊ ስርዓት ለመፍጠር፤ ፖለቲካችን ባለፉት 27 ዓመታት ሲካሄድበት ከነበረው የዘር ፖለቲካ በወጣ መልኩ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት የሚያይ፣ በዜግነት ፖለቲካ ላይ የተመረኮዘና ዝርዝር ጥናቶች የተደረጉበት ወጥ የሆነ አንድ ፓርቲ ለመመስረት ታምኖበትና ታስቦ ውህደቱ እንደተተገበረ የገለፁት የቀድሞ የአርበኞች ግንቦት ሰባት ሊ/መንበር ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ፤ ኢትዮጵያዊ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመትከል በሚደረገው እንቅስቃሴ፣ ሕዝቡ ውስጥ የዘር ፖለቲካ በማስረፅ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ችግሮች ቢኖሩም፤ ዘለቄታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመፍጠር፣ ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች መኖር እንዳለባቸው ጠቁመው፤ ኢህአዴግ ከዚህ ቀደም ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ስላልነበረ በዛው ልክ በዚህች ሀገር ላይ ዴሞክራሲን ማስፈን እንዳልተቻለ ገልፀዋል፡፡

አሁን ለደረስንበት ደረጃ ትልቁ ነጥብ ማንንም ዘር ሳንጠይቅ፣ ማንም ሐይማኖቱ ሳይጠየቅ፣ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን በነፃነት ከሁሉም ድርጅቶች ተሰባስበው የመሰረቱት ፓርቲ በመሆኑ ፤ ከምንም በላይ ደግሞ እንደ ቀደምት የሀገራችን ፓርቲዎች ታሪክ ጥቂት ሰዎች ከላይ ሆነው ያደራጁት ፓርቲ እንዳልሆነ ያመላከቱት ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ "እኛ የምናስበው በረዥሙ ነው፡፡ ስለ ዛሬው ጩኸትና ቀጣዩ ምርጫን ስለማሸነፍ አይደለም የምንጨነቀው፡፡ የለውጥ ሂደት ላይ ሁልጊዜ ጩኸት አለ፣ ይሄ አያስበረግገንም፡፡ ሁሉም የሚያሳዝኑና የሚያሳፍሩ እንቅስቃሴዎች ቢሆኑም፤ በእኛ ልባዊ እምነት ግን እነዚህ ነገሮች በሙሉ ይከስማሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሌም ሰላም ይፈልጋል፣ የሚቆጣጠረው መንግስትም ይፈልጋል፡፡ መንግስትን የሚለካው ለመኖር የሚያስፈልገኝን ነገሮች ይሄ ስርዓት ይሰጠኛል ወይ? በሚል ነው፡፡ አሁን ያሉት እንቅስቃሴዎች በጊዜ ሂደት ሲታዩ የቱንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆኑም እየጠራ መሄዱ የማይቀር ነው" ሲሉ ዕምነታቸውን በውህድ ፓርቲው ምስረታ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ በይፋ አስታውቀዋል፡፡

በየቦታው የሚሞቱትና የሚፈናቀሉት ወገኖቻችን ቢሆኑም፣ የቱንም ያህል በተለያዩ ክልሎች ችግሮች ቢባባሱም ፈፅሞ ተስፋ መቁረጥ እንደማይገባና የኢትዮጵያ ተስፋ ከፊት ለፊታችን ላይ የተቀመጠ መሆኑን ማሰብ እንዷ፤ አክራሪ ኃይሎች በሚፈጥሯቸው ግጭቶችና ጥቃቶች መበርገግ እንደማይገባ ጭምር ነው አንጋፋው ፖለቲከኛ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የገለፁት፡ ፡ "የምናስባቸውን ነገሮች በሙሉ ለመተግበርና የተሻለች ኢትዮጵያን ለመፍጠር መጀመሪያ ሀገሪቱ መረጋጋት አለባት፡፡ ከዛም በሰላማዊ ሁኔታ ምርጫው ይካሄድ፣ ያኔ የኢትዮጵያ ሕብ የመረጠውን በደስታ እንቀበላለን፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያ ውስጥ እሰራለሁ የሚል የፖለቲካ ድርጅት ይሄን አምኖ በዛ ውስጥ መንቀሳቀስ አለበት፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶች ተሰብስበው የፈጠሩት የቃል ኪዳን ሰነድ አለ፣ በዚህ ነው የምንመራው ብለው፣ ስለዚህ እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ለዛ ቃል ኪዳን እስከመጨረሻው መገዛት አለበት" ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፤ ይሄ ማለት ሀሳቦች በነፃነት የትም ቦታ የሚገለፁበትና የሚሰበኩበት፣ ሕብረተሰቡም በነፃነት የፈለገውን የሚመርጥበት ስርዓት እንዲዘረጋና ዕድል እንዲፈጥር ያስችላል ሀሳባቸውን በግልፅ አስቀምጠዋል፡፡

ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊት ሀገር እንድትሆን የሚፈልጉ ኃይሎች፤ በየቦታው ያለውን አክራሪ ጩኸት ቀስ እያሉ እያበረዱ፣ ሀገሪቱን ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ይወስዷታል የሚል ዕምነት እንዳላቸው የተናገሩት፤ ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ በውህድ ፓርቲው ምስረታ አመራር ምርጫ ላይ፣ በጉባኤው የሚደረጉ ውሳኔዎችን የሚወስኑት ከየወረዳው ሕዝብ የመረጣቸው ወኪሎች ብቻ ናቸው፡፡ ያ የሕዝብ ውክልና የሌለው ሰው እዛ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ መምረጥ አይችልም፡፡ ወይም መመረጥ አይችልም፡፡ መሳተፍና ውይይቱ ውስጥ መካፈል ግን ይቻላል፡ ፡ የመምረጥ የመመረጥ መብት ግን የፓርቲ የወረዳ አባላት ተሰብስበው የወከሉት አካል ብቻ ነው ያለው፡፡ ከዛ ውጭ ከተለያዩ የውጭ ሀገራት የመጡ የተለያዩ ድርጅቶች አባላት የነበሩ እዚህ ፖለቲካ ውስጥ የመሳተፍ መብት አላቸው፡፡ የውጭ ሀገር ዜግነት ካላቸው ግን መምረጥና መመረጥ አይችሉም፡፡ ይሄን የሀገሪቱም ህግ ስለማይፈቅድ፡፡ ሌላው ሀገር ውስጥ ሆነው በወረዳ ምርጫ ላይ ያልተሳተፉ፣ ግን ድርጅቱን በማቋቋም ረገድ ብዙ ነገር ሲሰሩ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች አሉ፤ እነሱ መምረጥ ባይችሉም ስብሰባው ውስጥ ግን መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ወደ 150 የሚደርሱ የመምረጥ መብት የሌላቸውና ፓርቲውን በመመስረት ሂደት ላይ ያገዙን ሰዎች በጉባኤው ላይ እንዲሳተፉ የተፈለገው፣ የእነሱ ሀሳብ ድርጅቱን ለማዳበርና ለማሳደግ ይጠቀማል የሚል ዕምነት በመኖሩ እንደሆነም አስረድተዋል፡ ፡

## የአዲሱ ፓርቲ ምስረታ እውን መሆን

ግንቦት 1 ቀን 2011 ዓ.ም ማለዳ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ከመክሰም ወደ ውህደት የተሸጋገሩት ፓርቲዎች ያቋቋሙት፣ ታላቅና አዲሱ ፓርቲ ምስረታ ዕውን የሆነው 6 ኪሎ አከባቢ በሚገኘው የስብሰባና ባህል ማዕከል አዳራሽ ነበር፡፡

ከሶስት መቶ አስራ ሁለት ወረዳዎች የተወከሉ መራጭና ተመራጮች፣ ከባህር ማዶ ለምስረታው ጉባኤ የመጡ ኢትዮጵያኖች፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች የተገኙበት ስነስርዓት፤ ከጅምሩ የደመቀ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ እስከዛሬ ድረስ ከተከናወኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምስረታ ታሪክ ሁሉ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ብዙ ሕዝብ የተገኘበት ታሪካዊ አደረጃጀት ነው ሊባል ይችላል፡፡

በዜግነት ፖለቲካ ውስጥ ማህበራዊ ፍትህን መሰረት አድርጎ ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲና ለነፃነት የሚደረገውን ሰላማዊ ትግል ዕውን ከማድረግ ባሻገር፤ ለዜጎች ሰላምና መረጋጋት በጥልቀት ለመስራት፣ ብሎም በሀገሪቱ ዘለቄታዊና ዴሞክራሲዊ ስርዓትን ለማስፈን የተቋቋመው ፓርቲ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ የሚል መጠሪያ የተሰጠው ሲሆን፤ ስብስቡም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ጉዞ ውስጥ ጥሩ አቅጣጫ ጠቋሚ አባላትን የያዘ መሆኑ ከወዲሁ እየተነገረለት ይገኛል፡፡

አዲሱ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ በይፋ መቋቋሙ በአዳራሹ ለተገኘው ታዳሚ ከተበሰረ በኋላ፣ ለሁለት ቀን የሚዘልቀውን ጉባኤ መክፈት አስመልክቶ መልዕክት እንዲያስተላልፉ የተጋበዙት፤ የቀድሞ አርበኞች ግንቦት ሰባት ከፍተኛ አመራር አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ ረዥም ዓመታት ከዘለቀው የፖለቲካ ሕይወት ልምዳቸው አኳያ (በተለይም ከአርበኞች ግንቦት ሰባት ፈታኝና ስኬታማ ጉዳዮች በመነሳት) አዲሱ ፓርቲ ከመዋቅር ሂደት እስከ አመራር ምርጫና ሕዝብ አገልጋይነት፣ ምን ዓይነት መንገዶችን መ ከተል እንዳለበት የሚያስረዳ ዕሁፍ አቅርበዋል፡፡

በመቀጠልም የአዲሱ ፓርቲ መስራች ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ የሺዋስ አሰፋ ስድስቱን ፓርቲዎች እንዲሁም የቀድሞ አንድነት ፓርቲ አመራሮችና አባላትን የያዘውን ፓርቲ ስብስብ ወደ ውህደት ለመውሰድ የተሄደበትን መንገድና ሀሳቡንም ዕውን ለማድረግ የተቋቋመው የነበሩት የተለያዩ ኮሚቴዎች፣ ያከናወኗቸውን ስራዎች በመግለፅ ታሪካዊው የምስረታ ቀን እንዲመጣ ከመላው የድርጅቱ አባሎች ባሻገር ከተለያዩ መንግስታዊ መ/ቤቶችና ግለሰቦች ለተደረገው መልካም ትብብር ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

በመክፈቻው ቀን ከተለያዩ የሀገሪቱ ክልል ተውጣጥተው የተገኙ አባሎች ስለ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ ምስረታ ያላቸውን ስሜትና አስተያየት የሚሰጡበት ዕድል የተመቻቸ ሲሆን፤ ከምሳ ሰዓት በኋላ በነበረው የአባላት ዝግ ስብሰባ ላይም በህግና ደንቡ ዙሪያ ሁሉም የጉባኤው ተሳታፊ ጥልቅ ውይይት አካሂዷል፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ የራሱ የሆነ ዓርማም አዘጋጅቷል፡፡ ዓርማው በተገመደ አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ገመድ ዙሪያው የተከበበ ነው፤ መሀሉ ላይ የፍትህ ምልክት የሆነው ሚዛን፤ ሚዛኑ ላይም ብዕር ያለ ሲሆን፣ ትርጓሜው ባለባንዲራው ገመድ በኢትዮጵያዊነት የተገመደና አንድነትን የሚያሳይ፣ ሚዛኑ ለፍትህና ለዴሞክራሲ የቆመ አመራርና ህብረተሰብ መፍጠርን፣ ብዕሩ ደግሞ ሠላማዊ ትግልን፣ በእውቀትና አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ህብረትን ማሳያ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ከተዋሀዱት ሰባት ፓርቲዎች ውስጥ የስድስቱ አመራሮች በውህደቱ ላይ የሰጡትን አስተያየት ከገፅ 14 እስከ 17 ድረስ ያቀረብን ሲሆን እንድታነቡት እንጋብዛለን፡፡

# የህወሃት አጣብቂኝ

## ጌታቸው አሰፋን

## “መስጠት” ወይ “አለመስጠት”

መላክ ቢ.

1983 ዓ.ም ለህወሃት የዘመናት ተጋድሎ ፍሬ ማጣጣሚያ ዘመን ሆኖ ብቅ ሲል በዚያው መጠን በስልጣን የበላይነት እና በአመራር የጠቅላይነት ባህሪውም አደገ። 27 ዓመታት ቆይቶ የመጣው ለውጥ ከ2010 መጋቢት ወር በኋላ ለህወሃት  ታላቅ ፈተና የደቀነ ሆነ። ኢህአዴግ የሚባለው ፓርቲ ወትሮም በህወሃት የበላይነት የተጠቀለለ አሻንጉሊት ፓርቲ ሆነና ህልውናውን የማያምኑበት ሲጠሩት ከነስሙም “ህወሃት/ኢህአዴግ” ብለውት ቀረ።

### ህወሃት/ የትግሉ ግብ

በኢህአዴግ ውስጥም ይሁን ከኢህአዴግ ውጪ ለለውጥ የተካሄዱ ትግሎች ሁሉ ቀዳሚ ግባቸው ህወሃትን ከስልጣን ማስወገድ መሆኑ ግልጽ የወጣው የለውጥ ሃይሉም ይሁን ህዝቡ በአላማ አንድ ሆኖ ህወሃትን እንደጋራ ጠላት ማውገዙ ሲታይ ነው። የለውጥ ሃይሉ ራሱ ስልጣን እንደያዘ ሰሞን የህወሃትን ጨቋኝ እና አምባገነንነት በዘወርዋራም ይሁን በቀጥታ መንገድ ሲናገር እና በግልጽ ከህወሃት ጋር ያለውን ተቃርኖ ይፋ ሲያወጣ በሌላ በኩል ኢህአዴግ የተባለውን ፓርቲ አምርሮ ሲታገል የኖረው በውጭና በውስጥ ያለው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ደግሞ ህወሃት ከፌዴራል ተቋማት ተባርሮ በመቀሌ ከተማ መወሰኑን ሲያይ ኢህአዴግን መቃወም ማቆሙና ትግሉ መቋጨቱን ማወጁ ነው። “ኢህአዴግ ዛሬም በመድረኩ ላይ እያለ ለውጥ የለም” የሚለው ህዝብ እንዳለ ሆኖ “ህወሃት ከስልጣን መባረሩ ብቻውን የኢትዮጵያን ህዝብ የለውጥ ጥያቄ የመለሰ ነው” የሚለው መብዛቱ የትግሉ ግብ ህወሃትን ከስልጣን ማስወገድ እንጂ ኢህአዴግን መገርሰስ እንዳልነበር ያመላክታል የሚሉ አልታጡም። ህወሃትን ከስልጣን ማንሳት ለምን የለውጥ ትግሉ ግብ ሆነ የሚል ጥያቄ ሲነሳ ደግሞ በአብዛኛው የሚሰጠው ምላሽ ይህ ፓርቲ ስልጣኑን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ የኖረ በመሆኑ በሃገር አቀፍ ደረጃ ለተከሰቱ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ ለግድያዎች፣ ለሙስና ወንጀሎች፣ ለከባድ አሻጥሮች እና በ27 ዓመታት ተሰርተዋል ለሚባሉ “ቆሻሻ” ስራዎች



ሁሉ ተጠያቂ ስለሚያደርገው ነው የሚል ነው። በስልጣን ላይ ያለ አካል የምርቃትም፣ የወቀሳም ተቀባይ ነውና ህወሃት በኢትዮጵያ ውስጥ በኢህአዴግ ለተፈጸሙ ወንጀሎች በሙሉ በጋራ እና በተናጥል ተጠያቂ የሆነበት ምክንያትም ይኸው ነው።

ህወሃት ዛሬ ይዟቸው ከነበሩ ዋና ዋና የፌዴራል መንግስት ስልጣናት ተሰናብቷል። በዚህ ያኮረፈው የህወሃት አመራር ሙሉ በሙሉ በመቀሌ ከትቷል። እነዚያ ላለፉት 27 ዓመታት ሃገር ሲያንቀጠቅጡ የነበሩ ባለስልጣናት ዛሬ በመቀሌ ሆቴሎች ውስጥ ተቀምጠው ቀናቶቻቸውን ያለስራ እያሳለፉ ነው። ዋናው ጉዳይ ግን በ27 ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ ለጠፉ ጥፋቶች ተጠያቂ የሆኑት ሁሉ መከሰሳቸው እና ለፍርድ መቅረባቸው እውን ሲሆን፣ ህወሃት ከፌዴራል መንግስቱ ጋር ያለው ወትሮም ቋፍ ላይ የነበረ ግንኙነት መቋረጡ እና ፍጥጫ ለመፈጠር በር መከፈቱ ነው። ህወሃት ከዚህ ቀደም የሜቴክ ዋና ዳይሬክተር የነበሩት ጄኔራል ክንፈ ላይ ክስ ተመስርቶ ተፈላጊነታቸው ሲገለጽ አሳልፎ የሰጠ ቢሆንም አሁን አንድ በአንድ በጠቅላይ ዐቃቢ ህግ ብርሃኑ ፀጋዬ መግለጫ እየተሰጠባቸው ተፈላጊ መሆናቸው ይፋ የተደረጉትን አባላቱን ግን  አሳልፎ ይሰጣል ወይስ አይሰጥም የሚለው ጥያቄ ገንኖ ወጥቷል። በርግጥም ህወሃት አሁን አጣብቂኝ ውስጥ የገባ መስሏል። ለዚህ ውጥረት ምክንያቱ ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቢ ህግ ሰሞኑን የሰጠው “የክስ መመስረት” መግለጫ ነው።

እንደመግለጫው የቀድሞ የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር በሆኑት አቶ ጌታቸው አሰፋን ጨምሮ በ26 የአገልግሎቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ላይ ክስ ተመስርቷል። በዚህ ክስ መሰረት ደግሞ የትግራይን ክልላዊ መንግስት የሚመራው ህወሃት ተከሳሾቹን አሳልፎ መስጠት ሊኖርበት ነው። ከለውጥ ሃይሉ ጋር ተኳርፏል የሚባልለት ህወሃት ዛሬ የለውጥ ሃይሉ ለፍርድ ይቅረቡ ያላቸውን እና በተለይም እንደአቶ ጌታቸው ያሉትን በምክር ቤቱ ስራ አስፈጻሚ ሆነው የተመረጡ ሰው አሳልፎ ለእስር ይሰጣል የሚለው ጥያቄ ከወዲሁ የጸቡ ማጠቃለያ ወይም የሰላማዊ ግንኙነቱ መጀመሪያ ተደርጎ እየታሰበ ነው።

### ሲጠበቅ የቆየው ውሳኔ?

የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ለመገናኛ ብዙሃን ይፋ እንዳደረገው ከሆነ ለረጅም ጊዜያት ከባድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ፈጽመዋል ተብለው በተጠረጠሩ የፌደራል ፖሊስ ወንጀል መርማሪዎች፤ የማረሚያ ቤት የሥራ ኃላፊዎች ላይ እንዲሁም የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የሥራ ኃላፊዎች ላይ የተዋቀረው ቡድን ምርመራ ሲያካሔድ ቆይቷል። በዚህም ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው የተጠረጠሩ በወንጀል መርማሪዎች ላይ፤ በማረሚያ ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ላይ እንዲሁም በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ላይ በሶስት የተለያዩ መዝገቦች ክስ ተመስርቷል።

ቀዳሚው የክስ መዝገብ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመርማሪዎች ላይ የተመሰረ ተው ክስ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ  በማረሚያ ቤት ኃላፊዎች ላይ →

የተመሰረተው ክስ ነው፡፡ ሁለቱም መዛግብት በየዘርፋቸው ፍርድ ቤት ቀርበው የክስ ሂደቱም በዚያው መጠን ቀጥሎ በችሎት ምስክር ለመስማት ቀጠሮ ተይዟል፡፡

ዋናውና የኢትዮጵያ ህዝብ ሲጠብቀው የነበረው ክስ ሶስተኛው ክስ ነው፡፡ ይህ ከሶስቱ ክሶች የመጨረሻ የሆነውና 46 ክሶችን በያዘ መዝገብ የተደራጀው ክስ 26 የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች የተካተቱበት እና በተለይም አይነኬ ናቸው የሚባሉት ብዙዎች በመንፈስ መስለው የሚስሏቸው አቶ ጌታቸው አሰፋ የተከሰሱበት መሆኑ የብዙዎችን ቀልብ ስቧል፡፡

በነአቶ ጌታቸው መዝገብ ከሚገኙት 26 ተከሳሾች ውስጥ 22ቱ ተከሳሾች በአሁኑ ወቅት በእስር ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ በሌላ በኩል የቀድሞ የአገልግሎቱን ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው አሰፋን ጨምሮ አቶ አጽብሃ ግደይ፣ አቶ አሠፋ በላይ እና አቶ ሽሻይ ልዑል ደግሞ በቁጥጥር ስር ያልዋሉ ናቸው፡፡ እነዚህ አራት ዋና ዋና ተከሳሾች በሌሉበት ሚያዚያ 29 ቀን 2011 ዓ.ም በከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡

በአቶ ጌታቸው ላይ ከተመሰረቱት ክሶች ዋና ዋናዎቹ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ በመተላለፍ ስልጣንን ያለአግባብ መገልገልና ከባድ የሙስና ወንጀል መፈጸም ፣ በዚሁ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ እና የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ በመተላለፍ ስልጣንን ያለአግባብ በመገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

በሌሎቹ ሁሉም ተከሳሾች ላይ አንቀጹ ይለያይ እንጂ የተከሰሱባቸው ወንጀሎች በሙሉ ስልጣንን ያለአግባብ መገልገል እና ከባድ የሙስና ወንጀል መፈጸም የሚሉ ናቸው፡፡ ዐቃቢ ህግ እንደሚያብራራው በነዚህ ባለስልጣናት ላይ ሥልጣንን ያለአግባብ መገልገል ክስ ሊቀርብባቸው የቻለው ተከሳሾች በግልጽ ከተሰጣቸው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፈው በመስራት እንዲሁም ሥልጣናቸው ወይም ኃላፊነታቸው የማይፈቅድላቸውን በተለይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖራቸው በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማሰብ በተበዳዮች ላይ ከባድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በመፈጸማቸው ነው ይላል፡፡

በተለይ በአቶ ጌታቸው ላይ በንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ክስ ሊቀርብባቸው የቻለው

1ኛ) በሚኒስትር ማዕረግ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ጀነራል የነበሩ በመሆናቸው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃቸው ከፍተኛ በመሆኑ፤

2ኛ) ኃላፊነታቸውን የጣሱበት ዓላማ ከባድ በመሆኑ እንዲሁም

3ኛ) በሕዝቦች ወይም በተጎጂዎች ላይ የደረሰው ጉዳት ከባድ በመሆኑ የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ ሊያደርገው በመቻሉ መሆኑን ይዘረዝራል፡፡

ከነዚህ ተከሳሾች በሙሉ የተዘረዘሩትን የወንጀል ማክበጃ ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ አሟልተው የተገኙት አቶ ጌታቸው ብቻ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ተከሳሾች በሙሉ ክስ ሊቀርብባቸው የቻለው ከላይ ለአቶ ጌታቸው ወንጀል ከባድነት ከተጠቀሱት ምክንያቶች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ተሟልቶ በመገኘቱ ነው፡፡

እንደጠቅላይ ዐቃቢ ህግ አቶ ጌታቸውን ጨምሮ በአራቱ ተከሳሾች ላይ በሌሉበት ክስ ሊመሰረት የቻለው የቀረቡባቸው ክሶች ከባድ በመሆናቸውና ይህም በህጉ መሰረት በሌሉበት ክስ ሊያስቀርብባቸው ስለሚችል ነው ተብሏል፡፡

ጉዳያችን አቶ ጌታቸው አሰፋና በዋና ደይሬክተርነት ይመሩት የነበረው ብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ከሆኑ፤ ስለአቶ ጌታቸው ከማውራታችን በፊት ይህ ተቋም ለምን እንደሜቴክ የሙስና እና የሰብዓዊ መብት ጥሰት ጎተራ ሆነ የሚለውን በቅድሚያ መቃኘት ይበጃል፡፡

## ብመደአ - የህወሃት ጅራፍ

የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት በእንግሊዘኛው (National intelligence and security services) በደርግ ዘመን ከነበረው ህዝብ ደህንነት ይልቅ ሃገርን ከጥቃት ህዝብንም ከአደጋ የሚከላከል ነው የሚል ግምት የብዙሃኑ ነበር፡፡ ነገር ግን የኋላ ኋላ ስምና ግብሩ ከቀድሞው ህዝብ ደህንነትም የባሰ ሆነ፡፡ ኢትዮጵያውያን ዜጎችን በገዛ ሃገራቸው ፍጹም ለሰው ልጅ በማይመጥን ጭካኔ በትር ስር የጣለ ተቋም ሆነ፡፡ አገልግሎቱ የስርዓቱን እድሜ ለማስቀጠል እና የምዝበራ እና ሙስና ወንጀልን አስፍኖ ሃገር በአጥንቷ እንድትሄድ ያደረገ ቡድንንም ፈለፈለ፡፡ በተለይም ለህወሃት ቀንድ የሆነ ስልጣኑን ለማራዘም አይገቡ ገብቶ የተቃዋሚ ዳናን የሚያጠፋ መረዝ የሆነ ተቋም ሆኖ ተፈጠረ፡፡

በኢትዮጵያ የደህንነት መዋቅር ውስጥ የተደራጀው በአቶ ጌታቸው አሰፋ የሚመራው አፋኝ ቡድን የናዚውን ጄስታፖ አይነት መዋቅር የያዘ ከባድ የወንጀል ቡድን ነው ይባላል፡፡ ብዙዎች ይህንን ተቋም ሲገልጹት ከብላክ ሴፕቴምበርም በላይ አስፈሪ ነው ይሉታል፡፡ በተቋም ደረጃ የበላይ አመራሩ አቅጣጫ እየሰጠበት የራሱን ኤምፓየር የገነባው ይኸው አሳሪ፣ አፋኝ እና ገዳይ ቡድን ኢትዮጵያ የፈረመችውን አለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ የጣሰ እና ዜጎችን ከፖለቲካ አመለካከታቸው ጋር ብቻ እያያያዘ ያሰቃየ ተቋምም ነው፡፡

ብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አዲስ አበባ ውስጥ ባዘጋጃቸው ሰባት ድብቅ እስር ቤቶች ውስጥ የብዙዎችን ደም ደመ ከልብ አድርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል ፈጽሟል፡፡

ይህ ቡድን ዜጎችን የሚያሰቃይበት መንገድ ከስቃይ ሰለባዎቹ አንደበት እንደተሰማው ከሆነ ዘግናኝ ነው፡፡ የታሰሩ ሰዎችን በኤሌክትሪክ ወንበር ላይ አስቀምጦ መመርመር፣ በብልት ላይ የፕላስቲክ ውሃ ማንጠልጠል፣ ቆዳን በፒንሳ መጎተት፣ ገልብጦ እና ዘቅዝቆ መግረፍ፣ በቆሻሻ ፎጣ ማፈን፣ ሰዎችን ያለወንጀላቸው የሃሰት ማስረጃ እያደራጁ ማሳሰር እና ማስፈረድ፣ ሃሩር ላይ ለረጅም ሰዓታት ማስቀመጥ፣ ግብረሰዶም መፈጸም እና ሴቶችን መድፈር፣ ሰዎችን ራቁታቸውን ጫካ ወስዶ መጣል፣ አይንን አጥብቆ በማሰር ለአይነስውርነት መዳረግ፣ እግርን መቁረጥ እና መግደል እንዲሁም በጣም ብዙ ተዘርዝረው የማያልቁ ወንጀሎችን ፈጽሟል፡፡

በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ድብቅ፤ ነገር ግን እጅግ አደገኛ እስር ቤቶች በመክፈት በተለይ የፖለቲካውን ተቃዋሚ አካል ጸጥ ለማድረግ ያለመ ተግባር ተከናውኗል፡፡ የግንቦት ሰባት ምክትል ሊቀመንበር አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የመን ላይ በዚሁ አካል ተይዞ ወደኢትዮጵያ በገባበት ጊዜ ከታሰረባቸው ስፍራዎች ዋናው ከነዚህ ማሰቃያ የድብቅ እስር ቤቶች አንዱ በሆነው ገነት ሆቴል አካባቢ በሚገኘው እስር ቤት ነው፡፡

ይህ ተቋም ለውጥ ከመጣም በኋላ አደገኛ ስራውን ቀጥሎ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይን ለማስገደል አስከመሞከር ደርሷል፡፡ ለህዝብ ደህንነት ሳይሆን ስጋት ሆኖ መኖሩ የተረጋገጠው አገልግሎቱ በተለይም በሰኔ 16 የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ የድጋፍ ሰልፍ ላይ ዶክተር አብይን ለመግደል በተቀነባበረው ያልተሳካ ጥቃት ጀርባ መኖሩም ተደርሶበት ይኸውም በይፋ ተነግሮ እንደነበር አይዘነጋም፡፡

ሌብነት፣ ሙስና እና ጥቅመኝነት ያረበበበትን ስርዓት ህልውና በመሳሪያ እና በስልጣኑ ጠብቆ በአንጻሩ አዲስ ቀን ለማምጣት የሚታገሉትን በአሸባሪነት እየፈረጀ ከባድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እና አካላዊ ጥቃት እንዲሁም ግድያ ፈጽሟል፡፡

ይህ ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በአቶ ጌታቸው አሰፋ የተቀነባበረ እና ከርሳቸው እውቅና ውጪ ያልተፈጸመ መሆኑ ሲታወቅ ደግሞ የሰውየው አደገኛነት እጅግ ጎልቶ ይወጣል፡፡

ህወሃት እኚህን ሰው አሳልፎ አይሰጥ ይሆን የሚለውን ጥያቄ ከማንሳታችን በፊት ስለሰውየው ማንነት ጥቂት እንበል፡፡

## ጌታቸው አሰፋ ማናቸው?

ህወሃቶች በጌታቸው ረዳ በኩል "አቶ ጌታቸው ለዚህች ሃገር ደህንነት መከበር ረጅም ጊዜ የራሱን ህይወት መስዋዕትነት አድርጎ የኖረ ሰው ነው" ብለው ይመሰክሩላቸዋል፡፡ ከራሳቸው ጥቅም ይልቅ የሃገርን ጥቅም ያስቀደሙ መሆናቸውንም ነው የሚናገሩላቸው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን እንኳን በውል የማያውቀውን ጌታቸው አሰፋን "የህወሃት መንፈስ" ናቸው እያለ ምን አይነት ፍጡር መሆናቸውን ለማወቅ ሲጥር ይታያል፡፡ ግለሰቡንም በኢትዮጵያ በኢህአዴግ አስተዳደር ዘመን ለተሰሩ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና ከባድ የሙስና ወንጀሎች ተጠያቂ ያደርጋቸዋል፡፡

ዊኪሊክስ "በውል የማይታወቅ ግራ ሰው" የሚላቸው ፣ ቢቢሲ ስለሰውየው በቂ መረጃ

ማግኘት ይቸግራል ብሎ ምስጢረኝነታቸውን የገለጸላቸው፣ በፌዴራል የመንግስት ስልጣን ላይ ሳሉ አንድ እንኳን ፎቶግራፍ እና ቪዲዮ ያልተቀረጹ ሰው፣ መንግስትን ሲመሩ እና ሲያሽከረክሩ፣ ፌዴራል ፖሊስን ጨምሮ በብዙ ቦታዎች ሲሰሩ በመንግስት መገናኛ ብዙሃን ቀርበው መግለጫ ያልሰጡ ሰው ለምን ራሳቸውን ደበቀው ይኖራሉ? ለሚለው ጥያቄ አንድም ምላሽ ያገኘ ሰው የለም፡፡

በ1940 መጨረሻ መቀሌ ቀበሌ 16 አካባቢ በሚገኝ አንድ የድሆች ሰፈር ውስጥ የተወለዱት ጌታቸው አሰፋ የደርግ የደህንነት መኮንን የነበሩት የሻለቃ አሰፋ ልጅ ነው፡፡ የጌታቸው አሰፋ አባት ሻለቃ አሰፋ በ1969 ወሳኝ ወቅት ሃገራቸውን በመረጃ ስራ ያገለገሉ ናቸው፡፡

አቶ ጌታቸው በጊዜው ንቁና ጎበዝ ተማሪ ጭምር ነበሩ፡፡ እነመለስ ዜናዊ ዊንጌት ሲገቡ ጌታቸው በ1968 በረሃ ገቡና አፋር ሰልጠና ወስደው መንግሰት ላይ ድንገተኛ ጥቃት ማድረስ ጀመሩ፡፡ በዚያው ለጥቃታቸው የሚያሰባስቧቸው መረጃዎች በሙሉ እየተጠናቀሩ ለተለያዩ ገብዓቶች ሲውሉ ትኩረታቸውም ወደመረጃና ደህንነት ሆነ፡፡ "ጌታቸው ግትር ነው" ይላሉ የሚያውቋቸው ሰዎች፡፡ በትግል ዘመን በነበራቸው ግትር አቋም ሶስት ጊዜ ከደረጃ ዝቅ ብለዋል፡፡ የህወሃት ስብሰባ ላይ "ሁላችሁም ሙሰኛ ናችሁ ከአባይ ወልዱ በቀር" ብለው በመናገራቸው ብዙዎች ጥርስ ነክሰውባቸው ነበር ይባላል፡፡ በህወሃት ታሪክ መሰነጣጠቅ በሚባለው ህንፍሽፍሽ ላይ እጃቸው ስለነበረበት ቢታሰሩም ይቅርታ ጠይቀው ተመልሰው ስራ የጀመሩ ሰውም ናቸው፡፡

ደርግ ሲወድቅ መከላከያ ሚኒስቴር ገብተው የኦፐሬሽን ሃላፊ ነበሩ፡፡ ከዚያም ፖሊስ ኮሚሽንን በኮሚሽነርነት ሲመሩ ቆይተው የብሄራዊ መረጃና ደህንነት የቀድሞ ዋና ሃላፊ አቶ ክንፈ ሲሞት ጌታቸው ወዲያውኑ የዘርፉ ዳይሬክተር ጄኔራል ሆነው ተቀመጡ፡፡ ባለፉት 27 ዓመታት ለተከሰተው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ዋና ተጠያቂ ተደርገው የቀረቡት የሁለት ሴቶች ልጆች አባት የሆኑት አቶ ጌታቸው አንዴ ከሃገር ሸሽተዋል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ መቀሌ ናቸው እየተባለ ውዝግብ ውስጥ በተገባበት ጊዜ ህወሃት የክልሉ ስራ አስፈጻሚ አባል አድርጎ ሾሟቸው እነሆ በሌላው የኢትዮጵያ ምድር በተፈላጊነት በመቀሌ ግን በባለስልጣንነት እና በነጻነት እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡

በአንድ ወቅት ስለእኚህ ሰው እና ህወሃት ለምን ለፍርድ እንደማያቀርባቸው ወይም የእስር ትዕዛዝ ወጥቶባቸው ሳለ እንዲያዙ ለምን አሳልፎ እንዳልሰጣቸው ሲጠየቁ አቶ ጌታቸው ረዳ ሲናገሩ እንዲህ ብለው ነበር፡፡

*"ጌታቸው አሰፋ እኮ የራሱ እስር ቤት የለውም፣ የርሱ ስራ መረጃ ማቀበል ነው ፣ በርሱ መረጃ ላይ ተንተርሰው ወንጀል የፈጸሙ አሉ ከተባሉ ፖሊስ ኮሚሽነሩና ማረሚያ ቤት ሃላፊው ናቸው፡፡ እነርሱ እያሉ ለምን እሱ ብቻውን ይፈለጋል፡፡ ጌታቸው ማረሚያ ቤት አያዝም፣ ፖሊስንም አያዝም ፡፡ የደህንነት ሀላፊ ነው፡፡ የሌለውን ስልጣን ተጠቅሟል ማለት አንድ ሆኖ ሁሉንም ጥፋት ለሱ መስጠት ግን አይገባም፡፡ በመሰረቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያላዘዟቸው ኦፐሬሽኖች አይካሄዱም፡፡ ለፍርድ እናቅርብ ካልን በየደረጃው የሚመለከተውን ሰው ለፍርድ ማቅረብ ነው፡፡ እርምጃ መወሰድ አለበት ከተባለ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ትዕዛዝ ነው ፖሊስ የሚሰማራው፡፡ ሁሉንም ጥፋት ለርሱ ማሸከም ተገቢ አይደለም፣ ጌታቸው ሃገሩን የሚወድ ሰው ነው፡፡ ነገር ግን ለሁላችንም በሽታ ተጠያቂ ሆኖ የቀረበ ሰው ነው"*

## የህወሃት አጣብቂኝ

ህወሃት ሁለት ምርጫዎች ውስጥ የገባ ይመስላል፡፡ አንድም ምን ያህል ህግ አክባሪ መሆኑን እና ለዜጎች መበደል እንደሚቆረቆር ማሳያ ይሆን ዘንድ ጌታቸው አሰፋን አሳልፎ መስጠት፣ ሁለትም ፌዴራል መንግስቱ የሚከፍተው የክስ መዝገብም ይሁን የሚሰነዝረው ወቀሳ እንደማያሳምነው ይፋ አወጥቶ ተናግሮ በግልጽ ተጠርጣሪን አሳልፌ አልሰጥም ብሎ ማወጅ፡፡ ከነዚህ ሁለት አማራጮች ህወሃት የሚያገኘው እና የሚያጣው ነገር ቢሰላ ብዙ ነው፡፡ ቀዳሚው ጌታቸው አሰፋን አሳልፎ በመስጠት የራሱን መቅኔ ሰብሮ ለጋራ ሃገርና መንግስት ያለውን ተባባሪነት እና ለህዝብ ያለውን ተገዢነት ያሳያል፡፡ ይህ የቀደመ ኩራቱን እና ማን አለብኝ የሚል አካሄዱን ያስተካክልለታል፡፡ ምናልባትም ከዚህ በኋላ በትግራይ ክልል ብቸኛ እና ሃያል ተደርጎ መታየቱ ያከትማል፡፡ በዚህም ተወዳዳሪ የትግራይ ፓርቲዎች ይገዳደሩት ይሆናል፡፡

> ***...አቶ ጌታቸው በጊዜው ንቁና ጎበዝ ተማሪ ጭምር ነበሩ። እነመለስ ዜናዊ ዊንጌት ሲገቡ ጌታቸው በ1968 በረሃ ገቡና አፋር ሰልጠና ወሰደው መንግሰት ላይ ድንገተኛ ጥቃት ማድረስ ጀመሩ...***

አላስረክብም ማለት ደግሞ ከፌዴራል መንግስቱ ጋር ከመቃቃር ያለፈ አደጋ እና ፍጥጫ ውስጥ ይከትተዋል፡፡ ይህንን ማድረጉ በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት አሳጥቶት ህወሃት ራሱ የወንጀለኛ ስብስብ የመሆኑ ነገር እርግጥ ይሆናል፡፡ በዚህ የትግራይ ህዝብ በወንጀለኛ ሰዎች እየተመራ ነው ወደሚል እሰጥ አገባ እና በዚያ ወገንም ለመከላከል በሚደረግ ውርወራ ጡዘት ሊፈጠር ይችላል፡፡ በአንድ ክልል እና በፌዴራል መካከል እንዲህ ያለ ውዝግብ በሚነሳበት ጊዜ የሚዳኝ አካል በሌለበትና መተማመን በጠፋበት፣ህወሃት በሃገሪቱ ካሉት እያንዳንዱ ግጭቶች አትራፊ ነው የሚለው ግምት ባየለበት በዚህ ጊዜ በርግጥም የጠቅላይ ዐቃቢ ህግን ትዕዛዝ መሻር ለማዕከላዊ መንግስቱ አለመገዛትን ያመጣል፡፡ በዚህ የአስተዳደሩ ልዩነት ምክንያት የሚከሰት ውጥረት ምናልባትም በክልሉ ሃላፊዎች ላይ ከፌዴራል መንግስት የአገልግሎት እና መሰል ማዕቀቦች ሊያስጥል፣ የጉዞ ክልከላዎች እና መሰል የመንቀሳቀስ ነጻነቶችን ሊገድብ እና በክልሉ እንደአጠቃላይ ደግሞ በህዝቡ ላይ ተጽዕኖ ያላቸው ግልጽና ግልጽ ያልሆኑ ተጽዕኖዎችን ሊያሳርፍ ይችላል፡፡

በዚህ ተጎጂው በመጀመሪያ የክልሉ ህዝብ በመሆኑ ህወሃት በጊዜ መስመሩን ከማዕከላዊ መንግስት ጋር አድርጎ ሰላማዊ ግንኙነት ከሌሎች ህዝቦች ጋር እንዲካሄድ ማድረግ አማራጭ የለውም፡፡ ፌዴራል መንግስት ከአንድ ክልል ጋር የሚኖረው ግንኙነት በዚህ መልክ ሲሆን፣ ሌሎች ክልሎችም ተመሳሳይ እምቢተኝነትን እንዳይማሩ የሚሄድበት ርቀት ወደአምባገነንነት ያደርሰዋል፡፡ በሌሎች ክልሎች (ቤኒሻንጉል፣ጋምቤላ ወዘተ) አመራሮችን ሳይቀር አዲስ አበባ እየጠራ ስልጣን ልቀቁ እንዳላለ ትግራይ ላይ ሲደርስ መቀዝቀዙም ጥያቄ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ ሁለቱም በህዝብ ዘንድ ሊሰጣቸው ከሚችል ግምት አኳያ ፍጥጫ ውስጥ እንዳይገቡ ያሰጋል፡፡

አንድ አስተያየት ሰጪ እንዳሉት የትግራይ ክልል መታዘዝ፣ የፌዴራል መንግስቱም የማዘዝ ጠገጋቸውን መርሳት የለባቸውም፡፡ ይህ ካልሆነ ህግ የሚከበርባት ሃገር አለች ስለማያስብል ሌላውም በፈለገው ጊዜ አጉራ ዘለል ሆኖ ህግ መጣሱ አይቀሬ ነው፡፡ ይህም መውቀሻ መንገድ ያሳጣል፡፡

*"ወንጀለኛ ሰብስቦ የያዘው፣የፌደራሉን መንግስቱን በግልፅ ሃገር ማስተዳደር የማይችል ነው የሚለው የትግራይ ክልልን የሚመራው ህወሃት በሃገር ላይ ሌላ ሃገር መስርቶ የመኖሩ ነገር ሊያበቃ ይገባል፤ በክልሉ የከተሙ ተጠርጣሪ ወንጀለኞችም ከህግ በላይ አለመሆናቸው ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ ካልሆነ ኢትዮጵያ የህግ የበላይነትን የሚያረጋግጥ ለውጥ ውስጥ ነኝ ብላ መናገር አትችልም፡፡ ትዕግስት የህግ የበላይነትን ተፈታትኖ፣አለቃ እና ምንዝር የማይታወቅበት ስድ ፖለቲካ እስኪያመጣ ድረስ ልቅ መሆን የለበትም፡፡ የትግራይ ክልል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት ስር እንደመሆኑ መጠን በክልሉ ያሉ ተጠርጣሪ ወንጀለኞችን እንዲሰጥ መለመን ሳይሆን መታዘዝ ነው ያለበት፡፡ ለወራት ወንጀለኛን ደብቆ ያስቀመጠው የትግራይ ክልል መንግስት ወንጀል ሰርቷልና ከደበቃቸው ወንጀለኞች እኩል መጠየቅ አለበት"*

በአንድ ወቅት ወደ ጀርመን ተጉዘው የህወሃት ደጋፊዎችን ያነጋገሩት አቶ ጌታቸው ረዳ "ህወሃት በሌላ ይታዘዝ ማለት ነውር ነው" ሲሉ የተናገሩት ንግግር ህወሃቶች ለራሳቸው የሰጡትን ትልቅ ግምት አመላካች ነው ይባላል፡ ፡ እንዲህ ባለ አለቅጥ በተጋነነ የትልቅነት ስነ-ልቦና ውስጥ የቆየው ህወሃት ዛሬ መቀሌን ብቸኛ አጥር አድርጎ መኖሩ ሊቀበለው የማይፈልገው ሃቅ ነው፡፡ እንዲያም ሆኖ አባሎቹ የእስር ትዕዛዝ ሲወጣባቸውና ክስ ሲመሰረትባቸው አሳልፎ ለመስጠት እንደሚገዳደርም ይገመታል፡፡ አሁን ህወሃት አጣብቂኝ ውስጥ የሚገባበት ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ጌታቸው አሰፋን አሳልፎ መስጠት ወይም አለመስጠት፡፡ ህግን አክብሮ በማዕከላዊ መንግስት መተዳደሪያ መመራት ወይም የሚያዘን የለም ብሎ በጀመረው መንገድ መቀጠል፡፡ አካሄዱ የሚያስከትለው ጦስ ግን ወደፊት በሂደት የሚታይ ይሆናል፡፡

# የዜግነት ፖለቲካና የፓርቲዎች ውህደት ለ"ታመመች ኢትዮጵያችን" መዳኛ!

ላለፉት አስራ ሁለት ወራት ሀገራችን ኢትዮጵያ በፖለቲካው ዘርፍ ብልጭ ባለላት ተስፋ ውስጥ ሆና የተለያዩ ክስተቶችን ስታስተናግድ ቆይታለች፡፡ ወደ አዲስ ዴሞክራሲያዊ ባህልና ሁለንተናዊ ዕድገት የሚያራድ በሚመስለው ያልተጠበቀ የብርሃን ጭላንጭል ውስጥ በየጊዜው የሚፈጠሩ ሁከቶችና ግጭቶች የብዙኃኑን ሕልምና ምኞት ቢያደበዝዙትም ለውጡ ይዟቸው የመጣው ፖለቲካዊ ትርፎች ዘርፈ ብዙ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

በተለይም የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ መንግስት የፖለቲካ ምህዳሩን ከማስፋት አኳያ በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ የነበሩ ፓርቲዎች ሲጠረጠሩበትና ሲወነጀሉበት የነበረው የሽብርተኝነት ክስ ሙሉ በሙሉ በማንሳት የወሰደው ዕርምጃ፤ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ምቹ ነፃነትን ቢፈጥርም፣ ከአንድነት ይልቅ ልዩነትን የሚያሰፉ፣ ከመፈቃቀርና ከመከባበር ይልቅ በሕዝቦች መሀል መጠላላትትንና መገፋፋትን የሚሰብኩ፤ የተስፋይቱን ምድር ሕልውና ከማሳደግ ይልቅ ሞቷን ሊያፈጥኑ ቀን ከሌሊት የሚባዝኑ፣ የብሔር ፓርቲዎችንም በስፋት እንድንመለከት አስገድዶናል፡፡

ከእነዚህ ፅንፍ የያዘ የዘረኝነት ባህሪይን ከተከናነቡ የጎጥ ድርጅቶች ውስጥ የተፈለፈሉ ጥቂት የማይባሉ ምሁራን፣ፖለቲከኛና አክቲቪስት ነን ባዮች ደግሞ፤ አንድን ብሔር ከሌላው በማጋጨቱና በማለያየቱ ረገድ የራሳቸውን ሚና እየተጫወቱ የለውጥ ተስፋው የደበዘዘ እንዲሆን ከማድረጋቸው ባሻገር፤ ሕወሓት መራሹ መንግስት "እኔ ከሌለሁ ትፈርሳለች" ለሚላት ኢትዮጵያ የቤት ስራው አድርጎ ለ27 ዓመት ሲደክምበት የቆየውን ሕዝብን የማለያየትና እርስ በርስ የማጋጨት የቤት ስራ በታማኝነት እያስፈፀሙለት ይገኛሉ፡፡

የትኛውም ብሔር መደራጀቱና መብቱን ለማስጠበቅ መንቀሳቀሱ ላይ አንዳችም ቅሬታ ባይኖረንም፤ ፖለቲካን በዘር ላይ መሰረት አድርጎ መደራጀት ግን ከአንድነት ይልቅ ልዩነት፣ ከመቻቻልና መግባባት ይልቅ መቃቃርን ፈጥሮ፤ ሀገሪቷን ከከባድ አረንቋ ውስጥ ሊከታት እንደሚችል ዛሬም፣ ነገም ደግመን ደጋግመን ከመናገር ወደ ኋላ አንልም፡፡ "እከሌ ብሄር ተበድሏል" እያሉ የሚደራጁ፣ የ"ፖለቲካ ሽቃዮችም" በትክክልም እንወክለዋለን የሚሉት ህዝብ ተበድሎ ከሆነ (በደል ባይደርስበትም ጭምር) ከፖለቲካው በፀዳ መልኩ የሚንቀሳቀሱ የሲቪክና የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን በመመስረት፤ ለሚቆረቆሩለት ሕዝብ ድምፅ መሆን የሚችሉበት ዕድል እንዳለም መዘንጋት የለበትም፡፡ ከምንም በላይ ኢትዮጵያዊነት ይቀድማልና፡፡

በጣም የወረደ የብሔር ፖለቲካ በተስፋፋበት በዚህ ዘመን፣ ሰሞኑን የዜግነት ፖለቲካን የሚያቀነቅኑ ሰባት የፖለተካ ፓርቲዎች ሙሉ በሙሉ ከስመው ወደ አንድ ውህድ ፓርቲ መቀየራቸው፤ ጎጠኝነት ላይ ለተንጠላጠለው ለሀገራችን ፖለቲካ ትንሳኤ፣ ለዝህባችንም ትልቅ ተስፋ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በቀጣዩ ምርጫ ተፎካካሪ ሆኖ ከመቅረብ ባሻገር፤ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ብቸኛ አማራጭ የሆነው የዜግነት ፖለቲካን የሚያቀነቅኑት እነኚህ ፖለቲከኞች በዘርፉ ያላቸው ልምድና ዕውቀት የዳበረ መሆኑ ደግሞ፣ አዲሱን ፓርቲ ከወዲሁ ተጠባቂ፣ ታማኝና ተስፈኛ ጭምር ያደርገዋል ግምት በብዙዎች ዘንድ አሳድሯል፡፡

በአክራሪ ብሔርተኝነት ስሜት እየተደራጁ፤ አንድም ሀገር ለመበታተን፣ ሁለትም ለኑሯቸው መደጎሚያ የሚሆን ገንዘብ ለመለቃቀም ሲሉ ለተመሰረቱት ጥቂት የማይባሉ የብሔር ድርጅቶች (ሌሎቹንም ጨምሮ) ከሰሞነኛው የፓርቲዎቹ ውህደት በቂ ትምህርት ሊወስዱ ይገባል እንላለን፡፡ "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" እንደሚሉት አበው፤ አንድነት በተለይም የዜግነት ፖለቲካ ለታመመችው ኢትዮጵያችን ትልቅ መዳኛ ነውና እዚህ ላይ ትኩረት ማድረጉ ለሀገርም ለህዝብም ይበጃል፡፡

በፕ/ር ብርሃኑ ነጋ ይመራ የነበረውና በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው አርበኞች ግንቦት ሰባት "እኔ ታላቅና ተሰሚነት ያለኝ ድርጅት ነኝና ብቻዬን እጓዛለሁ" ሳይል፤ ለሀገር ዕድገትና ብልፅግና፣ ለህዝቦች ዘለቄታዊ ሰላምና ተስፋ በማሰብ፣ ራሱን ዝቅ አድርጎ ብዙም ካልገዘፉ፣ የዜግነት ፖለቲካን ከሚያቀነቅኑ ፓርቲዎች ጋር ውህደት እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ማመቻቸቱ በራሱ የሚደነቅና የሚመሰገን በጎ ተግባር ነውና ሁሌም ዕድሜና ዕውቀታቸውን ለዚህች ሀገር ከመስጠት ወደ ኋላ የማይሉ እውነተኛ ኢትዮጵያኖችን ሳናመሰግን አናልፍም፡፡ በቀጣይነት ሌሎች የዜግነት ፖለቲካን መሰረት አድርገው የተቋቋሙ ፓርቲዎች ( ምናልባት ካሉ ማለታችን ነው) በእንዲህ ዓይነቱ ውህደት ወደ አንድነት በመምጣት፤ ዕውነተኛ የሕዝብ አገልጋይነታቸውን ቢያሳዩን የተሻለ መሆኑን ለመጠቆም እንወዳለን፡፡ የዜግነት ፖለቲካ ለታመመች ኢትዮጵያ መዳኛ!


**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**

**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**

ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**

ሮቤል ምትኩ

አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**

ቶማስ አያሌው (ከአሜሪካ)

**ከፍተኛ አዘጋጅ**

ብሩክ መኮንን

መለስ ሽኔ

**አምደኞች**

ፍቅሩ ኪዳኔ (ከሲውዘርላንድ)

ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

መስፍን ጌታቸው

አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ(ከአሜሪካ)

ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

ታምራት መርጊያ

**ጸሐፊ**

ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**

ፍፁም ንጉሴ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**

አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1

አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207

ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029

ስልክ ፡ +251 911 227661

+251 912 165606

+251 118 12 2333

**ኢ-ሜይል፡**

enqu2013@ gmail.com

Ghion2011meg@gmail.com

**Facebook**

Gihon-meg Fekadu

www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**

ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ

ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

ምልከታ

## ለም/ከን ኢ/ር ታከለ ኡማ፡-

# ለዐድዋ ድል መዝክርነት የሚገነባው ማእከል የጥቁር ሕዝቦችን የነጻነት ታሪክ የሚወክል ይሁን !



ተረፈ ወርቁ

### ታሪካዊ መንደርደሪያ

"The Adowa Victory provided practical expression to Ethiopianism: self-worth, dignity, unity, confidence, self-reliance, race pride, spirituality and freedom from colonialism." ~ Nelson Rohillala Mandela

ዛሬ በነጻነት የምንኖርባት ውድ፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ በብዙ አባቶቻችንና እናቶቻችን - ጀግንነትና ክብረት የጠነከረ ወኔ፣ ቆራጥነትና ብርቱ መሥዋዕትነት በክብርና በኩራት የተረከብናት ባለ ታላቅ ታሪክ ባለቤት የኾነች ሀገር ናት፡፡

ከቅርብ የታሪካችን ዘመን ብንነሣ እንኳን ‹‹የቋራው አንበሳ›› ዐፄ ቴዎድሮስ ከደባርቅ እስከ መቅደላ ከግብጻውያን እና ከእንግሊዝ ጦር ጋር ተፋልመው፣ ዐፄ ዮሐንስ ከጉራዕ እስከ ጉንደትና መተማ ድረስ ዘልቀው፤ከደርቡሾችና ከግብፃውያን ጋር ተናንቀውና አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው፣ ‹‹አፍሪካዊው ጀግና የጦር ጄኔራል›› የሚል ክብርን የተጎናጸፉት አሉላ አባ ነጋ በዶጋሊ ግንባር ከወራሪው ጣሊያን ሰራዊት ጋር በጀግንነት ተጋድለው፤

ዐፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱም ከአምባላጌ፣ መቀሌ እስከ ዐድዋ ግንባር ድረስ- ከበርካታ ውድ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ልጆቿ ያደረጉት የእምቢ ለነጻነቴ ተጋድሎና ያስመዘገቡት አንጸባራቂ ድል፣ የእነ ኮ/ል አብዲሳ አጋ ከኢትዮጵያ አልፎ እስከ ሮም ድረስ በተሰማው ጀግንነቱ የጻፉት ክቡር ታሪክ፣ የፋሽስት ጦር በአምስቱ አርበኝነት ዘመናቸው እረፍት የነሡት "የበጋው መብረቅ" በመባል የሚታወቁት ጀግናው አርበኛ እና የጦር መሪ፣ ሌፍተናት ጄኔራል ጃጋማ ኬሎ አኩሪ ጀግንነት ገድል፤

የእናት አርበኞቻችን እነ ሸዋረገድ ገድሌ፣ እነ ብዙነሽ ከበደ… እልፍ የሚሆኑ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንና እናቶቻችን ለሀገራቸው ኢትዮጵያ ነጻነት፣ ሉአላዊነትና አንድነት የከፈሉት መሥዋዕትነት፣ ዓለም ሁሉ በአድናቆት የሚመሰክርለት፣ ታሪክ በአድናቆት የከተበው እውነታ ነው፡፡ የታሪክ መዛግብት እንደሚመሰክሩትም፤ ይህ የአባቶቻችን የነጻት ተጋድሎ፣ ክብረት የጠነከረ አይበገሬነት፣ ወኔ እና ጀግንነት ሀገራችንን ኢትዮጵያን- ለአፍሪካ፣ ለአፍሪካ አሜሪካውያን፣ ለመላው ጥቁር ሕዝቦች እና እንዲሁም ነጻነታቸውን ለሚወዱና ለሚያከብሩ የሰው ልጆች ሁሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ - የነጻነት ቀንዲል እና የሉዓላዊነት ትእምርት/Symbol እንድትሆን አድርገዋታል፡፡

ጀግኖች አባቶቻችን እና እናቶቻችን ለሀገራቸው ነጻነት ካደረጉት አያሌ ጦርነቶች መካከል ደግሞ፤ የዐድዋን ጦር ግንባርን እና ድሉን ታሪክ በታላቅነቱ የሚያስታውሰው ነው፡፡ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ አውሮፓውያን ይህችን የሺሕ ዘመናት የነጻነት ታሪክና የገናና ሥልጣኔ ባለቤት የሆነች ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ያደረጉት ሙከራ ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን 'በዐድዋ ግንባር' ሕልማቸውን ከንቱ አስቀርተውታል፡፡ ከዚህም የተነሣ፤ ባለውለታዎቻችን፣ ጀግኖቻችን በዓለም መድረክ ነጻነቷ፣ ታሪኳና ክብሯ የተጠበቀች ሉዓላዊ፣ ታላቅ ባለ ታሪክ ሀገርን- ኢትዮጵያን በታላቅ ክብር አስረክበውናል፡፡

### ዐድዋ የኢትዮጵያውያን አንድነት እና ነጻነት ሕያው ምስክር ነው !

በዐድዋ ተራሮች ላይ ከመቶ ዓመታት በፊት አባቶቻችን ሃይማኖት፣ ዘር፣ ቋንቋ ሣይሉ በአንድነት በመተባበር ያስመዘገቡትን ታላቁና ታሪካዊው የዐድዋ ድል- ለሁላችንም ኢትዮጵያውን የአንድነታችን ሕያው ምልክትና ብሔራዊ ኩራታችን ነው፡፡

ትናንትናት፣ ዛሬም፣ ነገም፣ ሁሌምና መቼም በዐድዋና በሶሎዳ፣ በእነዛ ሰማይን ጫፍ የነኩ በሚመስሉ በሰሜን ግዙፍ ተራሮች ማዶ ልቆና ገኖ የሚሰማ አንድ የነፃነት ደወል ድምፅ፣ የነፃነት ልዩ ውበት አለ፡፡ በጀግኖቻችን እልፍ የሕይወት መሥዋዕትነት- በደም የተቀደሰ፣ በደም የተዋበ፣ በደም ለዘመናት የጸና፣ የኃያላኑን



የአውሮፓውያን ቅኝ ገዢዎችን ሕልም ያመከነ፣ ጽኑ ክንዳቸውን የረታ፣ በምንምና በማንም ያልተበገረ፤ በሁላችንም ልብ ውስጥ ዘልቆ የሚሰማ ክቡር ሕያው የነፃነት ድ-ም-ፅ!!

ይህ የእናት አገር ኢትዮጵያ የጀግኖች ልጆቿ የነጻነት ተጋድሎ ከአድማስ አድማስ ያስተጋባ፣ አፍሪካን፣ መላው ጥቁር ሕዝቦችንና በአጠቃላይ ነፃነታቸውን የሚያፈቅሩ የሰው ልጆችን ሁሉ በአንድነት ያስተሳሰረ ውብ የነፃነት ልዩ ዜማ፣ የአንድነታችን ልዩ ቅኔ ነው፡፡ ዛሬ በኩራት የምንተነፍሰው ውብ የነጻነት አየር፣ በዓለም ፊት ደረታችንን ነፍተን የምንናገርለት አባቶቻችን የነጻነት ታሪክ ተጋድሎ፣ በደም የተገዛ፣ በደም የከበረ፣ በዋጋ የማይተመን የብዙዎች ክቡርና ውድ ሕይወት የተከፈለበት ነው፡፡ ተወዳጇ አርቲስት እጅጋየሁ/ጂጂ በዓድዋ ዜማዋ ላይ እንዲህ እንደተቀኘችው፣

**"የተሰጠኝ ሕይወት ዛሬ በነጻነት፣**
**ሰው ተከፍሎበታል ከደምና ከአጥንት፡፡**
**ምስጋና ለእነርሱ ለዓድዋ ጀግኖች፣**
**ለዛሬ ነጻነት ላበቁኝ ወገኖች፡፡"**

በአንፃሩ ደግሞ አሳዛኙ ጉዳይ ይህ የሁላችን ኢትዮጵውያንና አፍሪካውያን የነጻነት ኩራት ምንጭ የሆነ ድል የልዩነታችን ማስመሪያ የታሪክ ክሥተት ከሆነ መሰነባበቱ ነው፡፡ የታሪክ ሊቃውንቱ "ታሪክ የትውልዶች መገናኛ ድልድይ ነው" ሲሉ ቢደመጥም፤ ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ታሪክ የትውልዱ የልዩነት ማስመሪያ ቀይ ቀለም ነው፡፡ የዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ለዘውግ ፖለቲካ ማፋፋሚያ ዓይነተኛ ማገዶ ሆኗል፡፡ ላለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ታሪክ ለየዘውጉ (በ"ጨቋኝ" "ተጨቋኝ" ትርክት) ዘውጋዊ ንቃት መፍጠሪያነት እንጂ ከዚህ በተሻገረ መልኩ የአገራዊ ውህድ ህላዌ መጋቢና ደጋፊ ሆኖ ሲገለጽ አይስተዋልም፤ አልተስተዋለምም፡፡

የማንነት ፖለቲካን የታከከ የታሪክ ትርጓሜ ጐልቶ በሚታይበት ኢትዮጵያ፤ በአገር ግንባታ ሂደቶች የታዩ ክስተቶችን በተመለከተ የበረታ ፉክክር፣ 'እኛ እና እናንተ እኮ' የሚል መፈራረጅና ማግለል ይስተዋልበታል፡፡ አፍሪካውያንና ዓለም ሁሉ በአድናቆት የጻፉለት፣ የተናገሩለት፣ የዘመሩለት የዐድዋ ድላችንም ከዚሁ አክራሪ ብሔርተኞች የታሪክ ውዝግብና ሽሚያ ከመጠለፍ አልዳነም፡፡ ስለሆነም ይህ የሁላችን ኩራትና የነጻነታችን ትእምርት/Symbol የሆነ ድል ➔

ለመዘከር በፒያሳ የሚገነባው የዐድዋ ማእከል ሁላችንንም ኢትዮጵያውያንን በአንድነት መንፈስ የሚያስተሳስረን መሆን እንዳለበት ከወዲሁ ሊሰመርበት ይገባል።

ክቡር ኢንጂነር ታከለ ኡማ የዐድዋ ማእከል ዘር፣ ጎሳ፣ ሃይማኖት፣ ፆታ ሳይለይ ሁሉንም ኢትዮጵዊ በአንድነት የሚወከልበት፣ የቀደመው አኩሪ የጀግንነት ታሪካችን በፍቅር ቃል-ኪዳን የሚያስተሳስረን እንዲሆን ቢታሰብበት መልካም ነው።

ከዚሁ ከላይ ካነሣሁት ሐሳብ ጋር በተያያዘም ባሳለፍነው ሳምንት የኪነ ሕንጻ ባለሙያ አርቴክት ዮሐንስ መኮንን የተባሉ ሰው በመዲናችን አዲስ አበባ ሊገነቡ ስለታሰቡት ታላላቅ ፕሮጀክቶች ባለሙያዎችን ለውይይት የሚጋብዝ መድረክ ‘በአዲስ አበባ ማእከል’ እንደሚደረግ በማኅበራዊ ድረ ገጻቸው ላይ አስፈርው ነበር። እኚሁ ባለሙያ ከውይይት በኋላ በገጻቸው ላይ ባሰፈሩት ጽሑፍም፤ “በከተማችን ለመሥራት የታቀዱት እንደ ዐድዋ ማእከል ያሉ ታላቅ ፕሮጀክቶች ብዙ ወጪ የሚጠይቁ፣ የሚወክሉት ሐሳብ ግዙፍ፣ የትናንቱን ታሪክ፣ ዛሬን አስተሳሰብ እና የነገውን ተስፋ የሚወክሉ በመሆናቸው በመንግሥት/ ጠቅላይ ሚ/ር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ በኩል ተገቢው ትኩረት እንዲሰጣቸው፤” ጠይቀዋል።

አርክቴክት ዮሐንስ ጨምረውም፤ “እነዚህ ፕሮጀክቶች ትውልዱንና ሀገራዊ ታሪኮችን በሚወክል መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ እጅግ ከፍ ያለ ሀገራዊ ዕውቀትን/ክህሎትን እና ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ የሚጠይቁ በመሆናቸው ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት በሀገር አቀፍ ደረጃ ባለሙያዎችን ያሳተፈ ውይይት አስፈላጊ መሆኑን አሰምረውበታል።

አርክቴክት ዮሐንስ ያነሷቸው ሐሳቦች ሁላችንም የሚያስማማን ይመስለኛል፤ ስለሆነም የከተማዋ አስተዳደር የዐድዋ ድልን ለመዘከር ሊገነባ ያሰበው ማእከል- አንጋፋ የታሪክ ምሁራን፣ ሀገራዊ የኪነ ጥበብ ቅርሶቻችንና እሴቶቻቸውን በሚገባ የሚያውቁና የተረዱ፣ የሚያከብሩ ባለሙያዎች የሚሳተፉበት፣ ሁላችንም የእኔ/ የእኛ ነው ብለን የምንኮራበት ፕሮጀክት ይሆን ዘንድ ይገባዋል። ይህ ትልቅ ፕሮጀክት ሌሎች እኔ/እኛ ያልተወከልንበት ብለው የሚያኮርፉበት፣ ጥቂቶች ደግሞ ታሪክን በመሻማትና የታሪክ ሐቅን በመበረዝ/by Distorting History የግል ፍላጎታቸውን መሰሪ ዓላማቸውን የሚያስፈጽሙበት እንዳይሆን ከወዲሁ በአጽንኦት ሊታሰብበት ይገባል እላለሁ።

## ዐድዋ ለአፍሪካውያን እና ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነጻነት ፋና ነው !

የአፍሪካውያን፣ የጥቁር ሕዝቦች ታሪክ የሰው ዘር ታሪክ ነው። የሰው ዘር ምንጭ፣ ባለ ግዙፍ ታሪክና የገናና ሥልጣኔ ባለቤትና እምብርት ኾና የምትጠቀሰው አፍሪካ፣ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ያላት ስፍራ ደግሞ እጅግ ደማቅ፣ ታላቅና ግዙፍ ነው። ሺህ ዘመናትን በሚያስከነዳው የአህጉሪቱ ታሪክ ውስጥ አፍሪካውያን እንደተቀሩት የዓለም ሕዝቦች ኹሉ በታሪካቸው አያሌ የብርሃንና የጨለማ ዘመናትን ዐይተዋል፣ አሳልፈዋል። በአፍሪካውያን ካለፉባቸው የጨለማ ዘመናት አስከፊ ታሪካቸው መካከልም ትልቁንና የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው ደግሞ የአህጉሪቱ ሕዝቦች በባርነትና በቅኝ ግዛት ቀምበር ስር ወድቀው ያሳለፉት ይኸው አስከፊው የባርነትና ቅኝ ግዛት ዘመን ታሪካቸው ነው።

መላው አፍሪካና ጥቁር ሕዝብ በባርነትና በቅኝ ግዛት ቀምበር ስር ወድቆ በሚማቅቅበት በዛ የአኅጉሪቱ የጨለማና የሰቆቃ ዘመን ታሪክ ውስጥ ጥቁር ሕዝቦችንና መላው የሰው ልጆችን ያስደመመ፣ ያስደነቀ፣ በደስታና በሐሴት ጮቤ ያስረገጠ የነጻነት ተጋድሎ ከምሥራቅ አፍሪካዊቷ አገር ከወደ ኢትዮጵያ ነበር የተሰማው። ነጻነታቸውን፣ ሉዓላዊነታቸውን፣ ሃይማኖታቸውንና ክብራቸውን የሚያፈቅሩ ሕዝቦች በአፍሪካ ምድር አዲስ የሆነ የአይበገሬነትና የነፃነት ተጋድሎ ሕያው ታሪክን በደማቸው ጻፉ።

የነጻነትን ልዩ ውበትንና ታላቅነትን በዐድዋ ተራራ በደማቸው የጻፉ የቀደሙ አባቶቻችንና እናቶቻችን በአፍሪካ ምድር፣ በጥቁር ሕዝቦች ምድር- አጥንታቸውን ከስክሰው ነጻነት ለሰው ልጆች ከፈጣሪ ዘንድ የተቸረ የማይገሠሥ ጸጋ መኾኑን ዳግመኛ ለመላው ለዓለም አረጋገጡ። ነጻነታቸውን የሚያፈቅሩ ሕዝቦች የነጻነት ብርሃን ጎሕን በደማቸው ቀለምነት፣ በአጥንታቸው ብዕርነት በጻፉ፣ ባበሰሩ ኢትዮጵያውያን ሕዝቦች ለአፍሪካና ለጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ቀንዲል ተስፋ የሆነ ብርሃን ሻማም ተለኮሰ።

ከጥንታዊቷና ከባለ ግዙፍ ታሪኳ የኢትዮጵያ ምድር የታየው ይህ የዐድዋው የነጻነት ጎሕ በመላው ዓለም የነጻነትን ብርሃን ፈነጠቀ፣ እምቢ ለነጻነቴ፣ እምቢ ለአገሬ፣ እምቢ ለክብሬ… የሚል ወኔንና መንፈስን ናኘ። በእርግጥም ዐድዋ ለአፍሪካ፣ ለጥቁር ሕዝቦችና በአጠቃላይም ነጻነታቸውን ለሚያፈቅሩ የሰው ልጆች ሁሉ የተበሰረ የነጻነት የምስራች ደወል ነበር፣ ነውም!! ዐድዋ የኢትዮጵያውያን ድል ብቻ አይደለም፤ የአፍሪካ፣ የመላው ጥቁር ሕዝብ እና ነጻነታቸውን የሚያፈቅሩ የሰው ልጆች ሁሉ የተቀዳጁት ታላቅ ድል ነው።

ስለሆነም፤ “የአፍሪካ መዲና” ተብላ በምትጠራ በከተማችን አዲስ አበባ ሊገነባ የታሰበው የዐድዋ ማእከል ሁሉንም ኢትዮጵያዊ፣ አፍሪካውያን እና መላው ጥቁር ሕዝቦችን የነጻነት ተጋድሎ ታሪክን እና የነጻነት መንፈስን የሚወክል መሆን ይኖርበታል። በዚህ ረገድ መንግሥት ለዐድዋ ማእከል ግንባታ ኢትዮጵያውን፣ አፍሪካውያን እና አፍሪካ አሜሪካውያን የታሪክ ምሁራን፣ የቅርስ ጥናት ተመራማሪዎችን እና የኪነ ሕንጻ ባለሙያዎችን ተሳትፎ እንዲያደርጉ፣ ሐሳብ እንዲያቀርቡ መጋበዝ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም የዛሬዎቹ እና መጪው አፍሪካውያን ትውልዶች ዐድዋ- ‘የእኛም ድል ነው!’ ብለው እንዲኮሩበት ማድረግ ይኖርብናል። ዐድዋን የመሰለ ታላቅ ድል፣ እንግሊዛዊው የታሪክ ጸሐፊ ጆርጅ በርክሌይ እንዳለውም፤ “የዓለም ታሪክ ለሁለት የከፈለና ኢትዮጵያውያንና መላው አፍሪካውንን በዓለም መድረክ በክብር ከፍ ያደረገን ይህን ታላቅ የታሪክ ክሥተት” ዐድዋን የአፍሪካውያን ሁሉ ኩራት እንዲሆን በማድረግ ረገድ መንግሥትም ሆነ በእኛ በኩል ይህ ነው የሚባል ሥራ ተሠርቷል ብሎ ለመናገር አያስደፍርም። በርካታ ሀገራት ትንሽዬ ታሪካቸውን አግዝፈውና አተልቀው የብሔራዊ ኩራታቸው ምንጭ፣ የአንድነታቸው ምልክት እና የቱሪስት መስህብ ሲያደርጉት እኛ ግን ታሪኮቻችንን፣ ቅርሳችንን የውዝግብና የግጭት መንሥኤ ከማድረግ ባለፈ የአንድነታችን ምልክት፣ የብሔራዊ ኩራታችን ምንጭ እና የቱሪስት መስህብ በማድረግ ረገድ እምብዛም አልተሳካልንም።

ስለሆነም አዲስ አበባ ‘የአፍሪካ መዲና’ የሚለው ስያሜዋ በይበልጥ ትርጉም የሚሰጥ እንዲሆን ከተፈለገም እንደ ዐድዋ ያሉ የአፍሪካዊነት ወይም የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ተጋድሎ ኩራት የሆኑ ድንበር ተሻጋሪ ታሪካዊ ቅርሶቻችን ሌሎችም አፍሪካውያን ወንድሞቻችን በኩራት እንዲጋሯቸው ለማድረግ ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል። በዚህ ረገድም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ዕውን ለማድረግ ያሰበው የዐድዋ ማእከል የመላው አፍሪካና የጥቁር ሕዝቦችን የነጻነት ተጋድሎ ታሪክ የሚዘክር እንዲሆን በብርቱ ሊታሰብበት ይገባል።

ይህም ብቻ አይደለም አፍሪካውያን የነጻት ተጋድሎ የታሪክ ቅርስ፣ ክብር እና ኩራት የሆነው የዐድዋ ድል - በአፍሪካ ኅብረት አዳራሽም መታሰቢያ ሊኖረው ይገባል። በኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመን ነጻነት ወኔና ብርታት ሆኗቸው ዘረኛውን የአፓርታይድ ሥርዓትን ከሕዝባቸው ጫንቃ ላይ ለማውረድ በጽኑ ለታገሉት ለጀግናው ማንዴላ/ለማዲባ በአፍሪካ ኅብረት አዳራሽ መታሰቢያ እንዲሆንላቸው የወሠኑ የአፍሪካ አገራትና መሪዎች፣ እንዴት ለአፍሪካ አገራትና ለመላው ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ተጋድሎ ትልቅ ወኔንና መነሳሳት የፈጠረው ዐድዋ- በኅብረቱ አዳራሽ ቋሚ መታሰቢያ ወይም መዘክር እንዴት ሊነፈገው፣ ሊነፍጉት ቻሉ?! የእኛ ዝምታ ወይንስ…?! ይህንን ጥያቄ አጥብቀን፣ አብዝተን ልንጠይቅ ይገባናል እላለሁ።

ስለሆነም መንግሥት፣ ነጻነቱን የሚያፈቅር፣ የሚያከብር ኢትዮጵያዊ ኹሉ እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በታሪክ፣ በቅርስ፣ በባህልና በቱሪዝም ዘርፍ ላይ የሚሠሩና የተሰማሩ አካላትና ምሁራንም የበኩላቸው ጥረት በማድረግ ዐድዋን የመላው አፍሪካ፣ የጥቁር ሕዝቦችና ነጻነታቸውን የሚያፈቅሩ ሕዝቦች ኹሉ የነጻነት ዓምባና የቱሪስት መዳረሻ በማድረግ ረገድ የተቀናጀ ሥራ ለመሥራት ከመቼውም በላይ ጊዜው አሁን ይመስለኛል። የዐድዋ ማእከልም በዚህ የቁጭት መንፈስ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ፣ አፍሪካውያንና መላው ጥቁር ሕዝብ ታሪክ ክብርና ኩራት ሆኖ ሊገነባ ይገባዋል!!

በተጨማሪም ዓድዋ በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብ ተጀምሮ የነበረውም እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባውም ለማንሳት እወዳለሁ። በመጨረሻም በዓድዋ ጀግኖቻችን መንፈስና ወኔ፣ ብርታትና ጽናት በዚህ ትውልድ የተጀመረው ጉዞ ዐድዋ አድማሱን አስፍቶ ሌሎች አፍሪካውያን ወንድሞቻችን እና ነጻነታቸው የሚያከብሩ የሰው ልጆች ሁሉ በነጻነት ኩራትና ስሜት የሚሳተፉበት ጉዞ ሆኖ እንዲቀጥል በመንግሥትም ሆነ በእኛ ዘንድ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ጽሑፌን የደቡብ አፍሪካ ቀድሞ ፕሬዚደንት ታቦ እምቤኪ በአንድ ወቅት ስለ ዐድዋ በተናገሩት አባባል ልደመድመው ወደድኹ፤ “Adowa Victory Made Africa a Victor, not a Victim!”

***ክብር ለዛሬ ነፃነት ላበቁን ለዐድዋ ጀግኖች አባቶቻችን እና እናቶቻችን ሁሉ!***

# አንደበት






“ይህንን አዲስ የለውጥ ኃይል፡ ፡ በሂደት መሥራት የሚገባው አንደኛ የሚድያ ካውንስል መቋቋም ነገር ተሰምቷል፡፡ የሚዲያን ጉዳይ ጥሩ ይሆናል፡፡ እነዚህ ነገሮች በሌለበት መንግስት ዝም ብሎ ተነ፡ ፡ እነዚህ አካላት በሚያቀርቡት ነገር አልተወጣም ተብሎ ሲጠየቅ ይችላል፡ ለመውቀስ ትንሽ መቸኮል ይሆናል፡ ተግባር እንዳለ ሊታወቅ ይገባል፡፡ አለበት፤ ይሄ ይቋቋማል የሚል የሚከታተሉ ኮሚሽኖች ቢቋቋሙ ሲደራጁ እኮ ነው ጋዜጠኛው ስቶ ምን ሳድርግ ሊል አይችልም፡ መግስት ግዴታውን ተወጥቷል፡፡ :”

***አቶ ማዕረጉ በዛብህ***

*ቦሌ ታይምስ ጋዜጣ ሚያዝያ 26 ቀን 2011 ዓ.ም*



“ብሄር ወይም ጎሳ ማለት ማንንም ለማሳነስና ለማግዘፍ አይደለም፡፡ ከዓለም አቀፋዊውና ሳይንሳዊው አረዳድ አኳያ፣ ብሄር የሚያሰኝ ክልል አለ ወይ ካልን፣ ምንም የሚያሰኘው ነገር የለም፡፡ ብሄር ሀገር ነው፤ ክልልን እንደ ሀገር መውሰድ አይቻልም፡፡ ብሄር ለመሆን ብዙ መስፈርቶች አሉ፡፡ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር መስፈርቶቹን ታሟላለች፡፡ ክልልን ብሄር ብሎ ማቅረብ ተገቢ አይደለም፡፡ የብሄር ነገር የመጣው፣ “የብሄር ጭቆና አለ” የሚለውን መነሻ ባደረገ መልኩ ነው፡፡ እውነታው ግን፣ የትኛውም ብሄር የትኛውንም ብሄር ጨቁኖ አያውቅም፡፡ በታሪክ የነበረውን የመደብ ጭቆና ከመካድ ጋር የተያያዘ ነው”

*ዶክተር ታዬ ብርሃኑ /የ”ፌደራሊዝም በኢትዮጵያ፣ እውነታውና አቅጣጫው” መጽሐፍ ደራሲ/*
*ኢትዮጲስ ጋዜጣ ሚያዝያ 27 ቀን 2011 ዓ.ም*



“ትልቁ የሀገራችን የፖለቲካ ችግር መነሻውና መድረሻው አስተሳሰብ ጤናማ ያለመሆኑ ነው፡፡ በአሃዳዊ ስርዓቱ ውስጥ የነበረውን ለአንድ ወገን ያደላ የፖለቲካ አስተዳደር ትተን አሁን እንኳ ያለውን ህገ መንግስት ብንመለከት ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባለቤት መሆናቸውን ይገልፃል፡ ፡ ዛሬ ላይ ረጋ ባለ መንፈስ ብናየውና ማነው ብሔር፣ ማነው ብሔረሰብ ህዝብስ የቱ ነው ብለሽ ብትጠይቂ መልስ አታገኚም፡፡ በዚህ ህገ መንግስት እንደሚመስለን ተርጎመን በማስቀመጣችን ነው ሁሉም መብት አለኝ ብሎ መብቱ እንዲከበርለት ጥያቄ እያቀረበ ያለው፡፡ ደግሞም ሀይማኖት ቋንቋና ብሔር ተፈጥሮአዊ መብት ሆነው ሳለ የፖለቲካ አጀንዳ ሊሆኑ አይገባም ነበር፡፡ የፖለቲካ አጀንዳ ስናደርጋቸው ነው ልዩነት የተፈጠረው፤ ከባልሽ ባሌ ይበልጣል እንደሚባለው ሁሉ ማለት ነው፡፡”

*ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካርያ*
*አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሚያዝያ 26 ቀን 2011 ዓ.ም*



“በህገመንግስቱ አንቀፅ 29 ላይ የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን የሚደነግገው ክፍል በጣም ጥሩ ነው፡፡ ምንም ከልካይነት የሌለው አለም አቀፋዊ ነው፡፡ ነገር ግን እርሱን ተከትለው የሚወጡ ህጎች ከልካይነታቸው የበዛ ነው፡፡ መነሻው የግሉን ፕሬስ እንደጠላት በማየት ነው፡፡ ሌላው ምንም ይሁን ምን መንግስት ስልጣኑን መጠበቅ አለበት በሚል ሲሆን፤ ይህን ለማስቻል መንግሥት ራሱን ከፕሬስ ይከላከላል፡፡ ሶስተኛው ግን መንግሥት የሚሰራው ነገር ልክ ነው ብሎ የማሰብ የዋህ አስተሳሰብ ነበረ፡፡ ነገር ግን ፕሬሱ የሚፈለገው እንደመንግስት ያሉ ጉልበተኞችን ተጠያቂ ለማድረግ ነው፡፡”

*ዶክተር ጌታቸው ድንቁ /የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር/*
*አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሚያዝያ 25 ቀን 2011 ዓ.ም*



“አሁን ግን ይህ ቀርቶ ከዚህ ብሄርና ከዚህ ክልል ይሄን ያህል ተጨዋች ተመረጠ ወደሚል ሁኔታ የምንገባበት ጫፍ ላይ መሆናችን ያሳዝናል..... የዘረኝነት መንፈስ ከኳሱ ላይ የግድ መጥፋት አለበት፤ ካልጠፋ ደግሞ መጥፎ ሁኔታ ውስጥ የምንገባ ይመስለኛል፡፡ እግር ኳሱን የምናሳድገው በዘረኝነት መንፈስ አይደለም፡፡ ኳሱ እስካሁን ባለበት ሁኔታ እንዲቆይ የሆነው የቀድሞ ተጫዋቾች በዘረኝነት ውስጥ ስለሌሉበት ብቻ ነው.... ሌላው ደግሞ ባለሙያዎቹ ራሳቸውን በእውቀት ማሳደግ አለባቸው፤ ስልጠና ላይ ያሉ አሰልጣኞቻችን አመቱ ሲያልቅ ለቀጣዩ አመት ዝግጅት ማድረግ አለባቸው የተሻለ ኮርስ አዳዲስ ፍልስፍና ማየት አለብን፡፡”

*ፍፁም ገ/ማሪያም /የመከላከያ ተጫዋች/*
*ሀትሪክ ጋዜጣ ሚያዝያ 30 ቀን 2011 ዓ.ም*

## ጠቅላላ እውቀት

■ ላይተር ከክብሪት በፊት የተፈጠረ ግኝት መሆኗን ያውቃሉ?

■ በዓለማችን ላይ ወደ 6,800 የሚጠጉ ቋንቋዎች እንዳሉ ሰምተዋል?

■ ላሞች ላብ የሚያስወጡት በአፍንጫቸው መሆኑን ያውቃሉ?

■ ጭልፊት አሞራ ሰማያዊ ቀለምን መለየት የሚችል ብቸኛው የአዕዋፍ ዝርያ ነው፤ ዓሳዎችን የሚፈጃቸው ይህን ስጦታውን ተጠቅሞ ነው፡፡

■ 111222333444555666777888999 እነዚህ ቁጥሮች በሙሉ የ37 ቁጥር ብዜት መሆናቸውን ተረድተዋል? እስቲ ይሞክሩት፡፡

■ በተፈጥሯዊ የሞመንተም ክስተት ምክንያት ጨው በበዛባቸው ውቅያኖሶች ውስጥ ዓሳዎች ወደኋላ መዋኘት እንደማይችሉ ያውቃሉ? በቀላሉ ለመጠመድም ለመበላትም የዳረጋቸው ይህ አጋጣሚ ነው፡፡

## ግጥም

### ኢትዮጵያ ሃገሬ



ኢትዮጵያ ሃገሬ ገናና ክብርት
በጣም ታምሪ ነበር ሆነሽ በህብረት፤
ምንድን ነው ወሬው፣ ያፍሪካን እመቤት
መጥቶ የሚወራው
አይደለም ከውጭ የራሷ እኮ ልጅ ነው፤
ትግሬው ከየት መጣ የኢትዮጵያ ልጅ
ኦሮሞ የማነው የኢትዮጵያ ልጅ፤
አማራስ የማነው የኢትዮጵያ ልጅ
አፋሩስ የማነው የኢትዮጵያ ልጅ፤
የነዚህ ሁሉ እናት ኢትዮጵያ ሃገሬ
በጣም ደስ ይለኛል ካንቺ መፈጠሬ፤
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንደሚባለው
ኢትዮጵያን ማንኳሰስ ጠቡ ከእግዜር ነው፤
ያለፈው አለፈ ሰላም ያምጣልን
ኢትዮጵያ ሃገሬን ወደ ቀድሞ ክብሯ
ይመልስልን!!!

***ከአስናቀች ገ/ኢጋዕዝት(ዕድሜ መጽሄት ቁ.9)***
***ሐምሌ 1994 ዓ.ም***



ፍቅርተ ተሾመ

# የስልጣኔ ደወል

ሩሲያዊው ፓውሎቭ ውሻ ነበረው የኖብል ሽልማትን ያስገኘ ውሻ፡፡ ፓውሎቭ ውሻው ምራቁን የሚውጠው በፊቱ ምግብ ሲቀመጥለት ብቻ አድርጎ ያስብ ነበር፡፡ ሆኖም አይደለም ውሻው ረሃቡ የሚነሳው እና ምራቁን የሚውጠው በፊቱ ምግብ ሲቀመጥለት ሳይሆን የምግብ አቅራቢውን እና የተንከባካቢውን የፓውሎቭ ኮቴ ሲሰማ ሆኖ አገኘው፡፡ ፓውሎቭ አሰበ እናም ይህ አሁን በሳይኮሎጂ ጥናት እና ግልጋሎት ውስጥ ትልቅ አስተዋፅኦ ያለውን ሳይንሳዊ ግኝት አስገኘለት፡፡

ፓውሎቭ ሲታሰብ ወደ አእምሮ የሚመጣው በጥናቱ ግኝት ላይ ያሉት ለሃጫቸውን የሚያዝረበርቡ ውሻዎቹ ቢሆኑም በጥናቱ በህክምና እንዲሁም በሳይኮሎጂ ብዙ እመርታን ያመጡ ግኝቶችን አበርክቷል፡፡ አስቦም አልቀረ ፓውሎቭ ጥናቱን አደራው፡፡ ፓውሎቭ በአንድ ወቅት ለውሾቹ የሚሰጠውን ምግብ ከደውል ጋር ማገናኘትን አሰበና እንዲህ አደረገ፡፡ ለውሾቹ ምግብ ሲሰጥ ሁል ጊዜ ደውል እንዲደወል አደረገ፤ እናም ውሾቹ በደውሉ እና በምግቡ መካከል ግንኙነቱን አጤኑና የደውሉን ድምፅ በሚሰሙበት ሰዓት ሁሉ ምራቃቸውን በመዋጥ ይጠብቃሉ፡፡ ይሄንንም የተለያዩ ሙከራዎችን እያደረገ አዳብሮታል፡፡ በግኝቱም ሰዎችም ይሁኑ እንስሳት እንዴት አንድን ሁኔታ ከሌላ አጋጣሚ ጋር አገናኝተው እንደሚላመዱ ማሳየት ችሏል፡፡

አውሮፓውያንን ከእርስ በእርስ መጠፋፋት ወደ ሰላም እና መረጋጋት እንዲያመሩ ካደረጉዋቸው ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ የጋራ እሴቶችን ማሳደግ ሲሆን፤ የሰሩትም የአውሮፓዊነት ስነ ልቦና ነው፡፡ ማንነት የሚለው ቃል አሁን ላይ ባለፈው ስርዓት እንደ አቸናፊ እና አሸናፊ አይነት ጦርነት ውስጥ ባይገባም የትርጉም አጠቃቀሙ ላይ ሁሉም የራሱን ፍላጎት መግለጫ ማድረጉ እየታየ ነው፡፡ ማንነት ሰዎች የሚፈጥሩት የጋራ ስያሜ ነው በማለት ልሂቃኑ ይገልፁታል፡፡ ብቸኛው የጋራ ማንነት ሰው መሆን ነው በማለትም ያስቀምጡታል፡፡ አውሮፓውያንም ይህን ይዘው የማህበራዊ ውቅራቸውን ገነቡ፡፡ ይሄ አንደኛው ምክንያት ቢሆንም ከ160 አመት በላይ የፈጀባቸው ከፍተኛ እልቂትን እና ውድቀትን ያስከተለባቸው የእርስ በእርስ ጥላቻው አንገሽጋሽ መሆኑ በራሱ ሌላ ምክንያት ነው፡፡ ታዲያ ይህ ሲሆን ለውጥን ሲፀንሱ በፖለቲካው፣ በማህበራዊው፣ በባህል እና በምጣኔ ሃብቱ ላይ ለውጦችን በአንድነት ማስተናገድ ችለዋል፡፡

እንደ ጠቅላይ ምክንያት ማየት የሚቻለው ይህ የስነ ልቦና ስራ ለአሜሪካኖችም የሰራ ይመስላል፡፡ ታላቋ አሜሪካ፡፡ የፓውሎቭ ውሻ ለህልውናው መሰረት የሆነውን ምግቡን ከደውሉ ጋር አገናኝቶታል፡፡ ለፓውሎቭ ውሻ ፓውሎቭ መጣ ማለት ምግብ መጣ ነው፡፡ ለሃጬን ማዝረብረብ ይጀምራል፡፡ የስልጣኔ ደውል ተደውሏል፡፡ አፍንጫችን ቅቤ ካልተቀባ ለስልጣኔ መንገዱ ሰው የመሆን፣ አስከትሎም ኢትዮጵያዊ የመሆን ስነ ልቦና ነው፡፡ አውሮፓውያን ራሳቸውን የታደጉበት የአንድነት ስሜት ልክ ኢትዮጵያ በመሳፍንቶች ትመራ የነበረችውን ሃገር አንድ እንደማድረግ ሁሉ፤ ጀርመን እና ጣሊያንም ራሳቸው በማሰባሰብ ስራ በመጠመድ ራሳቸውን አንድ ለማድረግ ወጥነው ከግብ ማድረሳቸው የነበረውን የስነ ልቦና ጥንካሬ ያሳያል፡፡ ምዕራባውያኑ እ.ኤ.አ በ17ኛው ክ/ዘ ጀምሮ ሲዋዋሉ የቆዩት የዌስትፋሊያ ረጅምና ተከታታይ የስምምነት ሰነዳቸው በየጊዜው የገመናቸው መፍቻ በመሆን አገልግሏል፡፡

በነዚህ ሁኔታዎች ብዙ ውጣውረዶች እና መንገጫገጮችን አስተናግደዋል፡፡ ብዙም ከመሳፍንት ስርዓት ጋር የማይለያይ የአገዛዝ ስርዓት ውስጥ የነበሩት አውሮፓውያን ስምና ቅርፃቸው ባይመሳሰል ቀድሞ ያልነበራቸውን ሃገር አልያም ሃገረ መንግስት አቋቁመው እርስ በእርስ በሉዓላዊነት ጉዳይ መደራደር፣ መነጋገር እና መከባበር ከጀመሩ ሁለት ክፍለ ዘመናትን አሳልፈዋል፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ ሉዓላዊት ሃገር ለመባሉ እንደምትቀድም የታወቀ ነው፡፡ በነገራችን ላይ አውሮፓውያን 30 አመት ለቆየው ግጭታቸው ዋነኛ ምክንያት የነበረው የሃይማኖት ልዩነት ነው፡፡ የትኛው ሃይማኖት ነው ሃገራዊ ሃይማኖት የሚሆነው? በሚል፡፡

ይህን ለእርስ በእርስ ግጭት ምክንያት የሆነውን ነገር መፍትሄ ያስቀመጡት ደግሞ ሃይማኖትን እና አገዛዝን መነጣጠል በዋነኝነት ሃይማኖት ከአመራር ውስጥ እንዲወጣ በማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ በእንግሊዝ ውስጥ የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆነ ሰው ወደ አመራር እንዳይመጣ በህግ አግደዋል፡፡ በአዋጅ የሃገሪቱ ይፋዊ ሃይማኖት ፕሮቴስታንት ተደርጎ ባይቀመጥም ሃገሪቷን የካቶሊክ እምነት ተከታይ እንዳይመራት ተደርጓል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ መጠነ ሰፊ ጉዳቶች የደረሱ ሲሆን፣ ከ6ሚሊየን በላይ የሆኑ ሰዎች ህይወት ተቀጥፏል፤ የተፈጥሮ ሃብቶች ወድመዋል፤ ብዙ ብዙ ችግሮችን አስተናግደዋል፡፡ ከዚህ ሁሉ በኃላ ራሳቸውን ማረጋጋት ሲችሉና በሃገር ምስረታ ጉዳይ ራሳቸውን ሲያጠምዱ እንግሊዝ በሃብት እና የንግድ መስመር ፍለጋ ላይ ያተኮረውን አዲሱ የቅኝ ግዛት እቅድ ላይ አተኩራ ሌላውን የአለም ክፍል ማቃወስ ላይ ራሷን አዘጋጀች፡፡ ሌሎቹም የውስጥ ስራቸውን ሲያሳኩ ወደ ውጪያዊ ስራ ራሳቸውን አሰማሩ፡፡ አፍሪካን ተቀራመቱ፣ ስልጣኔን፣ ሃገር ምስረታን፣ ሃይማኖትን ልናስተምራችሁ መጣን አሉ፡፡

**በአዋጅ የሃገሪቱ ይፋዊ ሃይማኖት ፕሮቴስታንት ተደርጎ ባይቀመጥም ሃገሪቷን የካቶሊክ እምነት ተከታይ እንዳይመራት ተደርጓል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ መጠነ ሰፊ ጉዳቶች የደረሱ ሲሆን፣ ከ6ሚሊየን በላይ የሆኑ ሰዎች ህይወት ተቀጥፏል፤ የተፈጥሮ ሃብቶች ወድመዋል፤ ብዙ ብዙ ችግሮችን አስተናግደዋል፡**

አሁን ላይ ቆመን ሃገርነቷ ላይ ጥያቄ የሚፈጠርባት ኢትዮጵያ ሃገር የሆነችው መቼ ነው? የሚለው የወንዙ ጉዞ ሙዚቃ በመንገዱ በስልጣን ነፋስነት ወዲህ እና ወዲያ እየተላጋ ይሄዳል፡፡ እንኳን ይሄ መልስ ያለው ጥያቄ ይቅርና ከባዱን የሃይማኖት ግጭት እንኳን ቀድሞ 100 አመት ሙሉ ለተተበተቡበት ችግሮች ሁሉ ማሳረጊያ አድርገው መቶ አመታትን ራሳቸውን ሊገነቡ ወደ ስልጣኔ ጉዞ ሀ ብለው የዛሬ ሁለት መቶ ክ/ዘመን ጀምረው ተሳክቶላቸዋል፡፡

አሁን በእነርሱ መነፅር አይተን፤ ከነእርሱ የተሻለ እድል እንዳለን ተረድተን፤ ካለንበት አዘቅት በቀላሉ ለመላቀቅ ስነልቦናችንን ማጠብ የሚችል ስነልቦናዊ ሻወር አስፈላጊ መሆኑ የፓውሎቭ ውሻ ምስክር ነው፡፡ እንዴት ማለት ጥሩ፤ ደውሉ ሲደወል እርሱ ቅቤው ላይ ከሆነ ህልውናው ምግቡ አለፈው ማለት ነው፡፡ አፍንጫው እና አፉ በቅቤ እንደተለወሰ ውሻ ስጋውንና ዳቦው መለየት እንዳቃተው፣ አሳዳጊውን እና ሌባውን መለየት እንደሚያቅተው ሁሉ የመንገዱን ቀኝ እና ግራ በተለወስነው ምናምን ሃገሪቷን ለሌባ፣ እራሳችንን ለሞት እየማገድን የመኖር ክፍለ ጊዜ አልቋል፡፡ ደውል ተደውሏል፡፡ የእኛ ስልጣኔ፤ የአብሮነት ስልጣኔ ሰዓት ደርሷል፡፡ ደውል ተደወለ፤ በጉጉት ለሃጬ ተዝረበረበ፤ የፓውሎቭ ውሻ፡፡

በእርግጥም ደግሞ ቅቤው ወዴት አለ? እያለ እንደሚቦዝን ውሻ ህዝብም የተቀባውን የግጭት መቆስቆሻ እያሸተትን ስንተላለቅ መኖር፤ ተሰርቶ የተሰጠውን ሃገር ይህ ትውልድ በዚህ ዘመን በህይወት ያለን ሁሉ አካቶ ማለት ነው የተቀበለውን ሲያስረክብ ከምዕራቡ አለም ጋር በታሪክ እና ስነልቦና የበታች መሆኑን ፅፎ ይሄዳል፡፡



# “የእናንተው ‹ኢብአዜ ፓርቲ!”

በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

አንገቱ ላይ የታሰረውን ቀይ ከራቫት እያስተካከለ፣ ‹‹ምን ምን አላችሁ?›› አለ ፊት ለፊቱ የቆመውን አስተናጋጅ፡፡

‹‹ጌታዬ፣ ሜኑ ላምጣልዎ?››

‹‹የሚነበብ ነገር ጠላሁ!›› አለ ምሁር ቢያጡ በምሬት እየተርገፈገፈ፤ ‹‹ማን አንብቦ እዚህ ደረሰና ነው!?›› አስተናጋጁ በምሁር ቢያጡ መልስ ግራ ተጋባ፤ ሊስቅም ከጀለው፤ እረጋ ብሎ ሥራውን ቀጠለ፤ ‹‹እሺ ጌታዬ! የበግ ቅቅል፣ ጎመን በሥጋ፤ ፓስታ በሥጋ፤ ሥጋ ፍርፍር፤ እንቁላል በሥጋ፤ ድንች በሥጋ፤ ምሥር በሥጋ…››

‹‹ወንድሜ ከሥጋ ዘር ውጣ!›› አለ ምሁር ቢያጡ አሁንም በቁጣ፤ ‹‹ብትችል ሦስቴ ጮኽክ ውጣ!›› አስተናጋጁ አሁን አልቻለም፤ ፈገግ አለ፡፡

‹‹ምን ያስቅሃል?›› ምሁር ቢያጡ ግምኛ ተኮሳተረ፡፡

‹‹እሺ! የፆም ምግብ ይሁንልዎ!?›› አስተናጋጁ ባልተጓደለ ትህትና ጠየቀ፡፡

‹‹ከሥጋ ዘር ውጣ ብቻ ነው ያልኩኽ!›› ምሁር ቢያጡ አሁንም እንደተቆጣ ነው፡፡

‹‹እሺ! ፓስታ በአትክልት፤ ሽሮ ሽፍንፍን፤ ሽሮ ፈሰስ፣ የፆም ፍርፍር፣ አትክልት ሳንዱች፤ አሣ ጉላሽ…››

‹‹በቃ ፓስታ በእንጀራ ይሁንልኝ!››

‹‹ምን አሉኝ ጌታዬ!?››

‹‹ፓስታ በእንጀራ!››

‹‹እሺ!›› አስተናጋጁ በመገረም ራሱን ነቅንቆ ሄደ፡፡

ምሁር ቢያጡ ግራ ቀኙን ገላምጦ ከለበሰው ኮት፣ የውስጥ ኪስ ብዛት ያላቸው ወረቀቶች አውጥቶ ለምግብ ቤቱ ተጠቃሚዎች ማደል ጀመረ፡፡

አብዛኛው ተመጋቢ በመሰላቸት፣ ጥቂቱ ደግሞ የያዘውን መልዕክት ለማየት በመጓጓት ወረቀቱን ተቀበለ፡፡ ምሁር ቢያጡ ይቺን ቀዳዳ ተጠቅሞ የፖለቲካ ፓርቲውን ለምግብ ቤቱ ሰው ሁሉ ማስተዋወቅ ጀመረ፤ ‹‹ፓርቲያችን ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ጭቆናና ማነቆ አጥብቆ ይታገላል፤ ፓርቲያችን ሰዎች ፖለቲካዊ አመለካከታቸውን ያለምንም መሸማቀቅ በፈለጉት ጊዜ እና ቦታ እንዲገልፁ ለመታገል የቆመ ነው፤ ፓርቲያችን ሐሳብን በሐሳብ ይሞግታል እንጂ በዱላና በጠመንጃ አይሞግትም፤ ፓርቲያችን ‹በዚህ ግባ በዚህ ውጣ› በሚሉ አልባሌ ወፈፌዎች አይመራም፤ ፓርቲያች የተገፋ ዜጋ እንጂ የተገፋ ብሔር የለም ብሎ ያምናል፡፡››

‹‹ቢያጡ›› ምን ፈልጎ ነው ወደ ፖለቲካው ዓለም የገባው? …እንጃ፡፡ ‹‹ቢያጡ›› ዛሬ ወጋችንን ይዞ የሚጓዘው የባለታሪካችን ስም ነው፡፡ ብዙዎች፣ ‹‹ምሁር ቢያጡ›› ብለው ይጠሩታል፡፡ ከተጸውዖ ስሙ በበረታ ቅጥያው መለያው ነው፡፡ ‹‹ምሁር›› ቢሉ ቢያጡ፤ ‹‹ቢያጡ›› ቢሉ ምሁር፡፡

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ አንድ መቶ ሰባት የፖለቲካ ፓርቲዎች እና አንጃ ግራንጃዎች አሏት፡፡ እንዲኽ መሆኑ ‹‹ተመስገን!›› ቢያሰኝም፣ ይኼ ቁጥር፣ ቁጥሩ መቶ ሃያ ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ለሚነገርለት ሕዝብ እዚኽ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ … አዎ! እጅግ በጣም ትንሽ ነው፡፡

ስለዚህ እንደ ‹‹ምሁር ቢያጡ›› ዓይነት ምሁር የግድ አንድ አዲስ፣ የፖለቲካ ፓርቲ እየመሠረተ አገራዊ ግዴታውን መወጣት አለበት፡፡ (ይኼን የሚለው ራሱ ነው)

…ምሁር ቢያጡ አወጣ አወረደ፤ አነሳ፤ ጣለ፡፡ ልምድ ያላቸውን የፖለቲካ ሰዎችን አየ፤ አማከረ፤ ተመካከረ፤ ያገኘው ውጤት ግን ተስፋ ሰጪ አልነበረም፡፡ እንደ ሌሎቹ ዋና ዋና የዚኽ ጊዜ ፓርቲዎች፣ ብሔር ላይ ተለጣፊ የሆነ ፓርቲ ካልመሠረተ እንደማያዋጣው ቁርጥ ያለ ውሳኔ ላይ ደረሰ፡፡

ጭንቁ አሁን ነው፤ ብሔር ከየት ያምጣ? የብዙኃኑን ቀልብ የሚስቡት አውራዎቹ ብሔሮች ሁሉ፣ ከእርሱ በፊት በመጡ እሳቶች ተይዘዋል፡፡ የፓርቲዎቹ ህልውና የቆመው፣ በብሔር አመጣሽ ተራ አተካሮ እና ‹በእኛ ነን ባለተራ› ዓይነት የሥልጣን መቋመጥ ስለሆነ፣ ምሁር ቢያጡን ተስፋ አስቆርጦታል፡፡

በዚኽ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንዳለ ነው አንድ ሐሳብ ብልጭ ያለለት፡፡ ተደሰተ ምሁር ቢያጡ፤ አዎ! ሐሳቡ ከአእምሮው ሳያፈተልክ ወደ ወረቀት አወረደው፡፡

‹‹ኦአይ ዘወር በል እባክህ! ያሉትንም ፓርቲዎች ተዋውቀን አልጨረስናቸውም!›› አለ አንድ ሰውዬ ወረቀቱን ወደ መሬት በመሰላቸት እየወረወረ፡፡

‹‹ለመሆኑ ፓርቲያችሁ ማን የሚባል ነው?›› አለ አንድ ጥግ ላይ ቀይ ወጥ አዝዞ የሚበላ ተመጋቢ፡፡

‹‹ኢብአዜ ፓርቲ››

‹‹ኢብአዜ ፓርቲ ደግሞ ምን ማለት ነው?››

‹‹የኢትዮጵያ ብሔር አልባ ዜጎች ፓርቲ››

‹‹ወይ ጉድ! ዜጎች አገር አልባ እየኾኑ ባለበት ጊዜ፣ ብሔር አልባ ብላችኹ መጣችኹ? …እስኪ መጀመሪያ አገር በሁለት እግሩ ይቁምና የፈለጋችኹትን የቅዠት ፓርቲ ትመሠርታላችሁ!›› አንድ ደሙ የፈላ ግለሰብ ጮኽ ብሎ ተናገረ፡፡

‹‹ምን ያድርግ፤ ያሉት ብሔሮች በሙሉ ተያዙበታ!›› አለ ሌላ ተመጋቢ እየሳቀ፡፡

‹‹በየጊዜው አዳዲስ ብሔር እየተፈጠረ ነው፤ እሱስ አዲስ አይፈጥርም!?›› አለ አንድ አሽሟጣጭ፤ ‹‹ለነገሩ ያሉትም እርስ በእርስ እየተፈነቃቀሉ ነው፡፡ የት ክልል ሄዶ ሊፈጥር ነው!?››

‹‹ጌታዬ ይኽ የሥራ ቦታ ነው፤ መለመን አይቻልም!›› አለ የአስተናጋጆች አለቃ ድንገት መጥቶ፤ ‹ተነስና ውጣ› በሚል ትእዛዝ፡፡ ምሁር ቢያጡ ተበሳጨ፡፡

‹‹ምፅዋት ስጠይቅ አየኸኝ!?›› በቁጣ ጮኸ፤ ‹‹ስለምን አየኸኝ ወይ!?››

‹‹ነገርኩዎ ጌታዬ፤ የቤቱ ሕግ ነው፡፡ አይቻልም!›› ይባስ ብሎ መውጫ በሩን በእጁ እያሳየው ተናገረ፡፡

‹‹እየለመንኩ አይደለም ሰውዬ! አዲሱ የፖለቲካ ፓርቲዬን እያስተዋወቅኩ ነው! ይገባሃል?›› አለ ሰውየው ከያዘው ወረቀት አንዱን ሊሰጠው እየዘረጋ፡፡

‹‹ያው ነው ጌታዬ! ከልመና ምን ለየው!?›› አስተናጋጁ ወረቀቱን ላለመቀበል እጆቹን ወደ ኋላ ሰበሰበ፡፡

‹‹ምን? ምን አልክ አንተ!?›› ምሁር ቢያጡ ድምፁን ዘለግ አድርጎ የቤቱን ተስተናጋጅ በሙሉ እየቃኘ፤ ጠየቀ፤ ‹‹ግራ ቀኝ እየሰማችሁት ነው!?››

‹‹እኔ ያልኩት ምግብ ቤታችን ውስጥ ልመና ክልክል ነው! እባክዎ ይውጡልኝ!››

‹‹እየለመንኩ አይደለም፤ ፓርቲዬን እያስተዋወቅኩ ነው!?››

‹‹ኦአይ! ስሙን እንግዲህ አያሸሞንሙኑብኝ! …ይኽ ምግብ ቤት ነው!››

ትርምስምስ ተፈጠረ፡፡ ምሁር ቢያጡ ተናደደ፡፡

‹‹በገዛ አገሬ የፈለግኩትን ማድረግ አልችልም ማለት ነው!?›› በብስጭት ውስጥ ኾኖ ጠየቀ፡፡


‹‹ድሮስ ብሔር አልባ ፓርቲ ብለኽ መጥተህ አገር ሊኖርኽ ነው!? ጊዜው እንደኾነ የብሔርተኛ ነው!›› አለ የቅድሙ ተናጋሪ ፈገግ እያለ፡፡ ቤቱ በአንድ ድምፅ ሣቀ፡፡

# የውህድ ፓርቲዎቹ አመራሮች ምን አሉ?

*ሀሙስ ግንቦት 1 ቀን 2011 ዓ.ም የስድስት ፓርቲዎችና የቀድሞ አንድነት ፓርቲ አመራርና አባላት ስብስብ አንድ በመሆን፣ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ አማራጭ ሆኖ የቀረበውን አዲሱን ፓርቲ በተመለከተ፤ አስቀድመው የከሰሙት ፓርቲዎች አመራሮችን የመጡበትን የፖለቲካ ድርጅትና ቀጣይ የአዲሱ ድርጅታቸውን ጉዞና ዕቅድ አስመልክቶ አቶ የሺዋስ አሰፋ፣ አቶ አንዷለም አራጌ፣ ዶ/ር ጫኔ ከበደ፣ አቶ ኑሪ ሙደሲር፣ አቶ ኦቻን ኦጋቱ፣ አቶ አዲስ ዳንሳን የግዮን ጋዜጠኛ ሮቤል ምትኩ አነጋግሯቸው የሰጡትን ምላሽ እንደሚከተለው አቅርቦታል፡፡ መልካም ቆይታ፡፡*

## “የእኛ ፖለቲካ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን”

### *(አቶ ኦቻን ኦጋቱ)*



ግዮን፡- እርስዎ ቀደም ሲል በም/ሲቀመንበርነት የሚመሩት የጋምቤላ ክልሳዊ ንቅናቄ ፓርቲ መቼ ነበር የተመሰረተው?

አቶ ኦቻን፡- ጋ.ክ.ን እ.ኤ.አ በ2017 ዓ.ም በአሜሪካን ሀገር ነው የተመሰረተው፡፡ ከዛ ቀደም ሲል ጋምቤላን በመወከል የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ድርጅቶች ነበሩ፡፡ ይሄ አካሄድ ስለማያዋጣ እነዚህ የጋምቤላ ፖለቲካ ድርጅቶች ወደ አንድነት ቢመጡ የተሻለ ነው በሚል ሁለት ፓርቲዎች ተዋህደን ጋ.ክ.ንን (የጋምቤላ ክልላዊ ንቅናቄን) መስርተናል፡

ግዮን፡- ፓርቲውን በአንድነት ስትመሰርቱ ምን ያህል አባላት ነበራችሁ?

አቶ ኦቻን፡- እንግዲህ በአሜሪካን፣ በካናዳ፣ በኬንያ፣ ደቡብ ሱዳንን ጨምሮ በተለያዩ ቦታዎች ከሶስት ሺጎ በላይ አባሎች ነበሩ፡፡ እንደውም ከዚህ በፊት ወታደር የነበራቸው ድርጅቶች የጋምቤላ ድርጅቶች፤ በደቡብ ሱዳንና የኢትዮጵያ መንግስት ስምምነት መሰረት ሁሉም ታጣቂ ይዞት የነበረውን መሳሪያ ቢፈልግ ሸጦ አልያም ጥሎ ወደ መጠለያ ካምፕ እንዲገቡ ያደረግናቸው በርካታ አባሎችም ነበሩን፡፡

ግዮን፡- ይሄ የሆነው መቼ ነው?

አቶ ኦቻን፡- ከለውጡ በፊት ባሉት ዓመታት፣ በትጥቅ ትግል ለይ የነበሩ አባሎቻችን በሰላማዊ መንገድ ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ይሄን ፓርቲያችንን ይዘን ነው ከግንቦት ሰባት ጋር እንዲዋሃድ ያደረግነው፡፡

በነገራችን ላይ እኛ አስቀድመን ነው ከአርበኞች ግንቦት ሰባት ጋር መስራት የጀመርነው፡፡ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ከመታሰሩ በፊት ተነጋግረን፣ ተስማምተን፣ ኤርትራ ድረስ ተወካይ ሁሉ ልከን፤ ከተለያዩ አካላት ጋር ጥልቅ የሆነ መግባባት ላይ አድርገናል፡፡

ግዮን፡- አሁን ወደ ውህደት የመጣችሁበት ፓርቲ በዜግነት ፖለቲካ ላይ የሚሰራ ነው፡፡ እናንተ አስቀድሞ ከብሔር የፖለቲካ ፓርቲነት በራቀ መልኩ በዜግነት ላይ ትሰሩ ነበር?

አቶ ኦቻን፡- ከዚህ በፊት የነበረን ዕምነት፤ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር የጋራ ችግር ስላለን መሰል ጉዳይ ካላቸው አካላት ጋር አንድ ላይ ሆነን በመታገል፣ ያለብንን ጠላት አሸንፈን የመንግስትነት ስልጣን ተቆጣጥረን፤ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ፓርቲዎች ጋር ባሉብን ችግሮች ላይ በመምከር ይህቺን ሀገር ወደ ተሻለ ደረጃ እናሸጋግረታለን፡፡ የሚል ዕምነት ስላለን ነው ለውህደቱ መልካም ፍቃደኞች የሆንነው፡፡

ግዮን፡- በቀጣይ ከአዲሱ ፓርቲ ምን እንጠብቅ? በ1997 ዓ.ም በህዝብ ተቀባይነት አግኝቶ፣ በፍጥነት ከፈራረሰው ቅንጅት ፓርቲስ ስህተት ምን ተምራችኋል?


አቶ ኦቻን፡- ህዝብ በአሁኑ አዲስ ድርጅት ላይ ተስፋ ማድረግ ያለበት፤ ውህዱ ፓርቲ ቀደምት ሀገሪቷ ያሳለፈቻቸው መሰል ጉዞዎችን መነሻ በማድረግ፤ ለመፍታት የሰራና በዛ መንገድ የሚሄድ መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል፡፡ በቀጣይ የሚካሄደው ምርጫ በሰላማዊና ትክክለኛ መንገድ ይከናወናል ብለን እናምናለን፡፡ ይሄ ባይካሄድ እንኳን ከዚህ በፊት የተከተልነውን የትጥቅ ትግል እንደ አማራጭ አድርገን በእኛ በኩል አልወሰድንም፡፡

የመቻቻልና የመግባባት መድረክ እስካለ ድረስ በዚህ ሰላማዊ መድረክ ተማምነንና ተግባብተን ከማንኛውም አሸናፊ ፓርቲ ጋር ተደራድረን፣ የእኛ ፖለቲካ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ በዴሞክራሲዊ መንገድ እንታገላለን የሚል ዕምነት ነው ያለን፡፡ ይሄን የሰባት ፓርቲዎች ውህደት ውጤት የሆነውን አዲስ ድርጅት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ትኩረት ከመስጠት ባሻገር በሚቻለው መንገድ አብሮን እንዲሰራ ነው የምንፈልገው፡፡

ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡

# “ማህበራዊ ፍትህን በሀገሪቱ ለማስፈን እንሰራለን”

**(አቶ ኑሪ ሙደሲር)**



ግዮን፡- እርስዎ የነበሩበት መኢዴፓ ፓርቲ ከመክሰሙ በፊት መቼ ነበር የተመሰረተው?

አቶ ኑሪ፡- መኢዴፓ በ1996 ዓ.ም ነው የተመሰረተው፡፡ እንደምታውቀው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ አብዛኛው ፓርቲዎች አንዱ ከአንዱ እየተሸራረፈ በመሄድ ነው የሚመሰረቱት፡፡ በዚህ መሰረት አብዛኛዎቹ የእኛ አባሎች መነሻቸው መዐህድ ሲሆን፣ ከዛ ኢዴፓ በመቀጠል መኢዴፓ በመሆን ከመሀል በመውጣት የተመሰረተ ነው የእኛ ድርጅት፡፡

ግዮን፡- ያኔ ምን ያህል አባላት ነበራችሁ?

አቶ ኑሪ፡- ወደ ምርጫ ስትቀርብ ያለው ሁኔታና በአብዛኛው እንዲሁ የተመዘገበው አባል አንድ አይደለም፡፡ አንድ ፓርቲ ሲቋቋም በሚይዘው ህግና ደንብ መሰረት አስፈላጊውን የአባላት ቁጥር አስመዝግበን የተመሰረተ ድርጅት ነው፡፡

ባለፉት ዓመታት በነበሩት ምርጫዎች በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄዱ ምርጫዎች ላይ፤ አመርቂ ውጤት ሲያዝመዘግብ የነበረ ፓርቲ ነው፡፡ መኢዴፓ በክ/ሀገር ደረጃም እንደዚሁ በተለያዩ ቦታዎች የተዋቀሩ የም/ቤት አባላትም አሉን፡፡

ግዮን፡- በቅርቡ ከሌሎቹ ፓርቲዎች ጋር ወደ ውህደት ስትመጡስ ምን ያህል አባላትን ይዛችሁ ነበር?

አቶ ኑሪ፡- ከአስራ አምስት ቀንና ከሶስት ሳምንት በፊት ሁሉም ፓርቲዎች በመዋሃድ ምርጫ ስናካሄድ በየወረዳዎቹ ማለትም በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል፣ በሰበታ፣ በተለይ በስልጤ ዞን ባሉት አውራጃዎች፤ ሌሎች ፓርቲዎች አንድ ወረዳ ላይ ካልሆነ በስተቀር በአብዛኛው ወረዳ ላይ የእኛ አባሎች ብቻ ሆነው ተመራርጠው የቀረቡበት ሂደትም ተከስቷል፡፡ አማራ ክልል በአብዛኛው ወረዳዎች፣ የእኛ አባላት ናቸው ተወዳዳሪ ሆነው የቀረቡት፡፡ አማራ፣ ደቡብና ኦሮሚያ ክልል በርካታ አባሎች ነው ያሉን፡፡

ግዮን፡-መኢዴፓ ከመክሰሙ በፊት የዜግነት ፖለቲካን ያራምድ ነበር?

አቶ ኑሪ፡-ለእኔ የዜግነት ፖለቲካ ማለት ማህበራዊ ፍትህ ነው፡፡ አብዛኞቹ የሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊበራል ዴሞክራቶች ናቸው፣ መንግስት አስፈላጊ የፍትህ ጉዳይ ላይ ዝቅተኛ ኑሮ ላላቸው ማህበረሰቦች የሚያደርገውን ነገር እንጂ፣ በማህበራዊ ፍትህ ላይ በመብትና ነፃነት ጉዳይ ላይ በዴሞክራሲ ጉዳይ ሁሉም ሊበራል ፓርቲ ነው፡፡ የስካንዲቪያን ሀገሮችና ሌሎችም እንዲሁ በማህበራዊ ፍትህ ላይ ሁሉም አንድ ናቸው፡፡እኛም አስቀድመን የሊበራል ዴሞክራሲ አራማጆች ነበርን፣ ግን አሁን በአጠቃላይ በሀገሪቱ ማህበራዊ ፍትህን ለማስፈን ከዝቅተኛው ማህበረሰብ ለመነሳት ተዘጋጀን እንጂ የዜግነት ፖለቲካ ዞሮ ዞሮ ይሄንኑ ማህበራዊ ፍትህን የሚያራምድ ነው፡፡

ባለፉት ሀያ ሰባት ዓመት በተፈጠረብን አስከፊ በሽታ (ዘረኝነት) የተነሳ በየቦታው ሰው የሚፈናቀለው ዜግነትን በትክክል ካለመረዳት ነው፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ ማንነት ይጠፋል ማለት ሳይሆን፤ ለምሳሌ በእኛ ውህደት የወረዳ ምርጫ ሂደት ውስጥ አማራ ክልል ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበው አባል አማራ ነኝ የሚል፣ ስልጤ ወረዳም ብትሄድ እንደዛው፣ ኦሮሚያ ክልልም ባሉን ወረዳዎች የቀረቡት ተወዳዳሪዎች ኦሮሞ ነኝ ብለው የሚያምኑ ናቸው፡፡ ያንን ሰው መሰረት አድርገህ ስትነሳ ብሔር ብሔረሰብን የሚነቅፍ ወይም አንድነትን የሚያቆሽሽ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ እኛ ትክክለኛ ኢትዮጵያዊነትን፣ ትክክለኛ ብሔረሰባዊነትን ለማስከበርና ለማስጠበቅ ነው የምንሰራው፡፡

ግዮን፡- ከአዲሱ ውህድ ፓርቲያችሁ ምን እንጠብቅ?

አቶ ኑሪ፡- ኢንሻላህ፤ ለሀገራችን ፍትህ የሰፈነበትና ለሁላችንም የምትሆን ዜጎች በዜግነታቸው በእኩልነት የሚኖሩባት ሀገር፣ እውነተኛ ስልጣን ከምርጫ ኮሮጆ የሚገኝበትን ስርዓት ለማስፈን ዕቅድ ይዘናል፡፡ አላህ ይርዳን፡፡

ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡

# “የተዋሃድነው መግለጫ ለማውጣት ሳይሆን ተወዳድረን ለማሸነፍ ነው”

**(አቶ የሺዋስ አሰፋ)**

ግዮን፡- የከሰመውና በእርስዎ ይመራ የነበረው ሰማያዊ ፓርቲ መቼና እንዴት እንደተመሰረተ፣ ወደ ኋላ መለስ ብለው ቢነግሩን?

አቶ የሺዋስ፡- ሰማያዊ ታህሳስ 22 ቀን 2004 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ፓርቲነት ነው የተመሰረተው፡፡ በዛን ጊዜ በነበረው የፓርቲዎች ምስረታ ደንብ መሰረት፣ አንድ ሺህ አምስት መቶ አባላትን ከሁሉም የሀገሪቱ ክልል አባላትን አስፈርሞ ነው ይፋ የሆነው፡፡ በወቅቱ ሶስት መቶ አካባቢ ከየወረዳው የመጡ መስራቾች ነበሩ፣ 60 በመቶ የሚሆነው ከክ/ሀገር፣ 40 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ከአዲስ አበባ ነው የተሰበሰበው፡፡ የሥራ አስፈፃሚ አባላቱም አስራ አንድ ሲሆኑ፣ ም/ቤቱ ደግሞ ሀምሳ አባላትን የያዘ ነበር፡፡

በ2005 ዓ.ም የአዲስ አበባና የድሬድዋ ከተሞች የማሟያ ምርጫ የሚባል ነበር፤ ግን ያኔ በወቅቱ በነበረው የምርጫ ቦርድ ጫና ሰማያዊ ፓርቲ አልተሳተፈም፡፡ በቀጣይነት በተካሄደው የ2007 ዓ.ም ምርጫ ላይ ግን ተሳትፈናል፡፡ ከ1997 ዓ.ም በኋላ የተካሄዱት ምርጫዎች ምን ዓይነት ቅርፅ እንደነበራቸው ሁላችንም እናስታውሳለን፤ ለነፃነት፣ ለእኩልነት፣ ለፍትህ ለዴሞክራሲ፣ ለመገናኛ ብዙኃን ነፃነት መከበር በተደረገው ትግል ሰማያዊ ፓርቲ ያደረገውን አስተዋፅኦ ሁሉም ሰው ያውቀዋል፡፡

ሰማያዊ ሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ከተዘጋው ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ በኋላ ግንቦት



25 ቀን 2005 ዓ.ም እንዳካሄደ ይታወቃል፡፡ ከዛ በኋላ ከ2006 ዓ.ም መጨረሻ እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ እኔ እስር ቤት ነበርኩኝ፡፡ ግን የፓርቲው መስራች አባልና የብሄራዊ ም/ቤት ሰብሳቢ ነበርኩ፡፡ እኛ እስር ቤት ብንሆንም በፓርቲው ውስጥ የነበሩት ወጣቶች ያደረጉት አስተዋፅኦ ደግሞ ከፍተኛ ነበር፡፡ ➔

➔ አሁን ደግሞ የትግሉ ዓይነት ከፍ ሲል፣ አማራጭ ፓርቲ ሆኖ መምጣትና አገርን ለማስተዳደር የተጠናከረ የሠው ኃይል፣ በፋይናንስም፣ በሀሳብም፣ በአደረጃጀትም ጭምር ጠንክሮ መምጣትን ስለሚጠይቅ፤ ከአርበኞች ግንቦት ሰባት፣ ኢዴፓ፣ መኢዴፓ፣ ከቀድሞ አንድነት አመራሮችና ከሌሎች ስብስቦች ጋር በመዋሀድ ትልቅ ሀገራዊ ፓርቲ ለመፍጠር እየሰራን ነው ያለነው። እንደሚታወቀው ሲመሰረትም ሰማያዊ ፓርቲ የዜግነት ፖለቲካን ነው የሚያራምደው፤ የትኛውም ሐይማኖት፣ የትኛውም ብሔረሰብ ኢትዮጵያዊ እስከሆነ ድረስ፣ ዕድሜው 18 ዓመት ከሞላ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ነዋሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ በነፃነት የሚሳተፍበትን ፖለቲካ ነበር ስናካሂድ የቆየነው።

ግዮን፡- በምርጫ 97 ወቅት ቅንጅት በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ዕምነት ቢጣልበትም፤ በፍጥነት ድርጅቶቹ ከመበታተናቸው ባሻገር አንዱ ሌላውን የመወንጀል ሂደት ነበርና ከዛ የእናንተ ውህድ ፓርቲ ምን ተምሯል? ሕዝባችንስ ከዚህ አዲስ ፓርቲ ምን ይጠብቅ?

አቶ የሺዋስ፡- እንግዲህ ውህደቱ ከባለፈው ትምህርት የወሰደ ነው። ሁለት መሰረታዊ ነገሮች አሉት፤ አንደኛ የህዝቡን ሕይወት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ዝም ብሎ ሊበራሊዝም፣ ሶሻሊዝም፣ ካፒታዝም ወይም አብዮታዊ ምናምን ሳይል የሕዝቡን ሕይወት ሊያስተካክል የሚችል ማህበራዊ ፍትህ የተሰኘ ሰፊ አይዶሎጂ ይዞ ነው የመጣው።

በሁለተኛነት አደረጃጀቱ ወረዳን መሰረት ያደረገ ነው። ሁሉም ፓርቲ እታች ወርዶ ወረዳ ላይ ነው ውህደት የፈፀመው፤ ከዚህ በፊት እንደነበረው ከውህደት በኂላ ማክሰም ሳይሆን፣ ከከሰሙ በኂላ ወደ ውህደት መሄድን ስለተከተልን ብዙ ነገሮቹ የተዘጉ ናቸው። በመሆኑም ይሄ አዲስ ፓርቲ ቅድሚያ ሰጥቶ የሚሰራው በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት እንዲኖር ማድረግ ነው። ከዛ ቀጥሎ ለውጡን ተቋማዊ ማድረግና የተጀመሩት የሪፎም ስራዎች መስዋዕትነት የተከፈለባቸው እንደመሆናቸው በትክክል እንዲተገበሩ ማድረግ፤ እንዲሁም ቀደም ሲል እንደገለጽኩት አማራጭ ፓርቲ ለመሆን በሰው ኃይልም ሆነ በሌሎች መንገድ ተደራጅቶ መቀጠል ነው።

ስለዚህ ይሄ አዲስ ፓርቲ ከዚህ በፊት እንደነበረው መግለጫ ለማውጣት፣ ወይም የገዢውን ድክመት ለማጋለጥ ምናምን ሳይሆን በትክክል ተወዳድሮ ስልጣን ለመያዝ የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብም በዚህ መልክ ነው እየጠበቀው ያለው፤ በእውነትና በትክክል ለኢትዮጵያ ችግር መፍትሄ ይዞ የቀረበ፣ ምሁራን ያሉበት፣ ወጣቶች ያሉበት፣ ሴቶች ያሉበት ትልቅ የፖለቲካ ድርጅት ነው ማለት ይቻላል።

ግዮን፡- እናመሰግናለን።

# “ራሳችንን ሳይሆን ሀገርን ማስቀደም አለብን፣በሚለው ተስማምተን ዛሬ ላይ ደርሰናል”

(አቶ አንዷለም አራጌ)



ግዮን፡- የቀድሞ የአንድነት አመራር አባላትና ሌሎች ግለሰቦችን ያካተተው የእናንተ ቡድን ወደ ውህደቱ ለመምጣት መነሻ የሆነው ምክንያት ምን ነበር?

አቶ አንዷለም፡- እንደምታስታውሰው ከረዥም ዓመታት እስር ከወጣን በኂላ በድጋሚ ለአስራ ሁለት ቀን እስር ቤት ገብተን ነበር። እዛ በነበርንበት አስራ ሁለት ቀን ውስጥ ተመካክረን፣ እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ ነው የሚያዋጣን የሚል ውሳኔ ላይ ደርስን። ከዛ የአንድነት አመራር አባል ያልነበሩ ልጆችን ቀላቅለን፤ ያንን ሀሳባችንን ዕውን ለማድረግ ፓርቲዎችን ማነጋገር ጀመርን።

በአጋጣሚ ግንቦት ሰባትና ሰማያዊ ተመሳሳይ ዓላማ ነበራቸውና አብረን መስራት ጀመርን። የአንድነት አባል የነበሩም፣ ያልነበሩም ሰዎችን በማሰባሰብ አንድ ላይ ሆነን፤ ወደ እዚህ ውህደት ልንመጣ ችለናል። መውጫው መንገድ ይሄ ሆኖ ታይቶን ነበር፤ ጎተራ ፖሊስ ጣቢያ ታስረን በነበረበት ወቅት ነው ሀሳቡን ያመነጨነው።

ግዮን፡- አዲሱ ውህድ ፓርቲ የዜግነት ፖለቲካና ማህበራዊ ፍትህን መሰረት ያደረገ ከመሆኑ አኳያ ቀጣዩ የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ምን ይሆናል ብላችሁ ታስባላችሁ?

አቶ አንዷለም፡- እኛ ሁልጊዜም ልዩነት ይኑር፣ ሀሳብ ይኑር፤ ግን ሀሳቡ ግለሰብ ወይም የሆነ ቡድን ላይ የተንጠላጠለ ሳይሆን በሰለጠነ መንገድ ይቅረብ፣ የማያስፈልግም ከሆነ የማያስፈልግበትን መንገድ አፅንኦት ሰጥቶ ምክንያት በማቅረብ፤ በመወያየትና በመከራከር ለሀገራችን የሚጠቅም ነገር መምጣት አለበት ብለን እናምናለን። ይሄ ማለት ደግሞ ግዴታ እኛ የያዝነው መንገድ ብቻ ላይሆን ይችላል፣ ሌሎቹም የሚያቀርቡት ከሆነ ዋናው ነገር ሕዝቡ ሉዓላዊ ስልጣኑን ተጠቅሞ ይምረጥ ነው የምንለው።

በእኛ ዕይታ ግን ይሄ ብሔር ላይ ተመስርቶ በዘር ላይ ተመስርቶ የመደራጀት ነገር ጠንቅ እንደሆነ፤ ዓለም ላይ ብዙ ሀገሮች እንደውም ህግ እያወጡበት ያለ፣ ሕዝብ ከህዝብ እያጨረሰ ያለ መንገድ እንደሆነ፣ በእኛ ሀገርም ብዙዎች የተጫረሰቡት እንደሆነና አሁንም ድረስ ተሳቀን የምንኖርበት ሁኔታ እየተፈጠረ ስለሆነ፤ ይሄንን ነገር አሁን መድገሙ ብልህነት ሳይሆን ካለፈው አለመማር ነው ብለን ነው የምንወስደው። ይህን ማርከሻ ፍቱን መድኃኒት ይሆናል ብለን ነው የምናስበው ሰው በአስተሳሰቡ፣ ለሀገሬ አለኝ በሚለው ራዕዩና በብቃቱ ላይ ተመስርቶ የሚደራጅ አስተሳሰብ፤ ይሄን ችግር ለማድቀቅ፣ ኢትዮጵያንም ደግሞ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር አማራጭ ሀሳብ ነው ብለን እናምናለን። ለዛ ደግሞ ጠንክረን እንሰራለን። ርግጠኛ ነኝ ሕዝቡ በስፋት ይደግፈናል። ምክንያቱም ይሄ ሀሳብ የብዙኃኑ ሕዝብ ሀሳብ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በተፈጥሮው ሕብረ ብሄራዊ ነው፤ በተፈጥሮው ሀገሩን የሚወድ ሕዝብ ነው። ተከባብሮ፣ ተደጋግፎ፣ ተጋብቶና ተዋልዶ የሚኖር ሕዝብ እንጂ በጎጥ የሚደራጅ ሕዝብ አይደለም። ስለዚህ የህዝቡን ዕምነትና ፍላጎት ይዘንለት ስንሄድ በስፋት እንደሚያቅፈን እንደሚደግፈን እናውቃለን። ምልክቱንም ከወዲሁ እያየን ነው።

ግዮን፡- ቅንጅት በ1997 ዓ.ም ምርጫ ተስፋ ቢጣልበትም ፍርስርሱ ወጥቷል። አንዳንድ አባሎችም ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ በመሄድ የህዝብን ስሜት ክፉኛ ጎድተዋልና ይህ ነገር ዳግም እንዳይከሰት ምን ያህል ጥንቃቄ አድርጋችኋል?

አቶ አንዷለም፡- በፊት የነበረውና አንደኛው ችግር ግለሰቦች ራሳቸውን የማስቀደም ስሜትና ፍላጎት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የፓርቲዎች አደረጃጀት ግለሰቦች ተክለስብዕናቸው እንዲገነቡ የተመቸ ሆኖ መገኘቱ ነው። ሶስተኛ አገዛዙ ለዴሞክራሲ ቁርጠኛ አለመሆኑና አጠቃላይ ሕዝቡ የሚከፍለውን ግብር ለአፈና ማዋሉ፣ ፓርቲዎችን ለማጥፋትና ለማቀጨጭ የሚሰራ መሆኑ ነው። እነዚህ ይመስሉኛል ዋናዎቹ ምክንያቶች።

አሁን ባለበት ሁኔታ እነሱን ስናይ የፓርቲው አደረጃጀት ከሶስት መቶ አስራ ሁለቱም ወረዳዎች ያሉ ም/ቤቶች የሚወክሏቸውን ሰዎች መርጠው ነው የላኩት። እነዛን የወከሏቸውን ሰዎች ደግሞ እዚህ መጥተው በጠቅላላ ጉባኤ መርጠውም፣ ተመርጠውም የድርጅቱን ላይ ቁንጮ ድረስ የሚመጡ ሰዎችን ይመርጣሉ። በዚህ ሂደት የተወከሉ እነዛ ሰዎች ደግሞ የመረጧቿው የወረዳው ሰዎች ያንን መስፈርት የማያሟሉ ከሆነ ከተመረጡ በኂላ መልሶ ሌላ ጠቅላላ ጉባኤ አድርጎ ሌላ ሰው ሊተካባቸው ይችላል።

አገዛዙም በደህንነት ሰርጎ እየገባ፣ ለፍላጎቱ እንዳይመለምላቸው የሚያስችል ሂደት ነው እየተከተልን ያለነው።፤ በፊት ማዕከል ላይ ነበር ሰዎች የሚሰባሰቡት። አሁን በየወረዳው ስለሆነ፣ በየወረዳው ደግሞ ማን ምን እንደሆነ፣ ከቀበሌ እስከ ቤት ድረስ ሰው የሚተዋወቅ በመሆኑ፤ በተጨማሪም እንደምናየው አሁን ያለው መንግስትም ለእንዲህ ዓይነት ነገር የተመቸ አይደለም በሀቅ እንወያይ፣ በሀቅ እንስራና ሀገራችንን ወደፊት እናራምድ የሚል መንግስት ነው ያለው። በዚህ መንገድ ምን ያህል ርቀት እንደሚሄድ ወደ ፊት እናያለን፤ ግን እያየናቸው ያሉ ምልክቶች ግን ገንቢና በጎ አስተሳሰቦች ናቸው።

ይሄ የነበረውን ብዙ የተበላሸ፣ የሕዝብን ቅስም ይሰብር የነረበውን አካሄድ ያልመረጠና ለዛ ያልተደላደለ ነው ብለን ስለምናስብ ከበፊቱ የተሻለ ተስፋ አለ ብለን እናምናለን። በእኛ በኩል በቂ ትምህርት ወስደናል፤ ራሳችንን ሳይሆን ሀገራችንን ማስቀደም አለብን በሚል፣ አንድ ሆነን ምንም ነገር በድምፅ ብልጫ ሳንወስን በሙሉ ስምምነት ነው እስካሁኗ ደቂቃ ድረስ ተጉዘን ዛሬ ላይ የደረሰነው። ካለፈው ሀገርን ሳይሆን ግለሰብን ከሚያስቀድም አስተሳሰብ እንደወጣንም ትልቅ ማሳያ ነው። ሰዎች ነንና ወደ ፊት ልንሳሳት የምንችል ከሆነ ደግሞ ከህዝባችን እንማራለን።

# “እየተሰባሰቡ መበታተንን በአዲስ አደረጃጀት ቀርፈነዋል”

## (ዶ/ር ጫኔ ከበደ)



ግዮን፡- በቅርቡ የከሰመውና ወደ ውህደቱ የገባው ኢዴፓ መቼ እንደተመሰረተ ወደ ኋላ ተመልሰው ቢያስታውሱን?

ዶ/ር ጫኔ፡- ኢዴፓ የተመሰረተው በ1992 ዓ.ም ነው በወቅቱ ምርጫ ቦርድ የሚጠይቀውን መስፈርት አሟልተን፤ በሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲነት ነው ኢዴፓ የተመሰረተው፡፡ ከዛ በኋላ ጠንክሮ በመስራትና በጥሩ ድርጅት መንፈስ፣ በዛው በተቋቋመበት 1992 ዓ.ም ተድርጎ በነበረው ሀገራዊ ምርጫ ተሳትፈን ሁለት የም/ቤት ድምፅ አግኝተን ፓርላማ ገብተን ነበር፡፡

ያንን አደረጃጀት ተከትሎ እስከ ምርጫ 97 በነበረው ሂደት በርካታ አባላትን ለማፍራት ችለናል፡፡ በወቅቱ ብዙም ሀገር አቀፍ የፖለቲካ ድርጅቶች አልነበሩምና ኢዴፓ ነበር በስፋት ሲንቀሳቀስ የቆየው፡፡ ያኔ በመላው ሀገሪቱ ውስጥ እስከ 40 ሺህ የሚደርሱ አባላት ነበሩን፡፡ ከአፋር፣ ከጋምቤላና ሱማሌ ክልሎች ውጪ በሁሉም ክልሎች ጽ/ቤት ከፍተን አባላትን አደራጅተን ስንንቀሳቀስ ቆይተናል፡፡

በ1996 ዓ.ም መዐህድ ወደ መኢአድ ተቀይሮ ከመጣ በኋላ ውህደት ለመፍጠር ሙከራዎች ተደርገው ነበር፡፡ በኋላ ግን ቅንጅትን ለመመስረት ምሁራን ሀሳብ አቅረበው ስለነበር፤ ቅንጅት ሲመሰረት የድርጅቱ ማኒፌስቶና ፕሮግራም ሆኖ የቀጠለው የኢዴፓ ፕሮግራም ነበር፡፡ ኢዴፓ ሰፊ የፖሊሲ ትንተናዎች ነበሩትና ያ የፖሊሲ ትንተና በርግጠኛነት ሀገሪቱን ወደተሻለ ደረጃ ሊያሻግሩ የሚችሉ ፖሊዎችን ጠቋሚ ስለነበር፣ ያንን መሰረት አድረገን አብረን ከቅንጅት ጋር ሰርተናል፡፡

ምርጫ 97ን ተከትሎ የተከሰተው አጠቃላይ የፖለቲካ መፈረካከስ እንደገና አጣብቂኝ ውስጥ ከትቶ ነበረ፤ ከዛ በመነሳት የተወሰኑ አመራሮቻችን ከቅንጅት በመውጣታቸው ምክንያት ፓርቲው እንደገና ራሱን አድሶ በህብረ ብሔራዊነት እንዲቀጥል ቢደረግም፣ ከዛ በኋላ ያለው ሂደት አንተም እንደምታውቀው የፖለቲካው ምህዳሩ እየጠበበ የሄደበት ሁኔታ ተከሰተ፡፡ በዛ ሂደት ውስጥ ከ40ሺህ አባላት እየተመናመኑ 23ሺጎ የሚሆኑ አባሎችን ነው እንደገና ማደራጀት የቻልነው፡፡ ከዛ በኋላ በተለያዩ ምርጫዎች ላይ ብንሳተፍም ማሸነፍ ግን አልተቻለም፡፡

ግዮን፡- አዲስ ወደ ተመሰረተው ውህድ ፓርቲ ስትመጡ ምን ያህል አባሎችን ይዞችሁ ነበር?

ዶር ጫኔ፡- ወደ እዘህ ውህደት ስንገባ በእኛ በኩል አሰራ ሰባት ሺህ የሚሆኑ አባሎችን ይዘን ነው፡፡ በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች ማለት ይቻላል፡፡ የእኛ አደረጃጀት ሰፊ ህብረ ብሔራዊ ሽፋን ስለነበረው ቅድም ከነገርኩህ ሶስት ክልሎች ውጪ በሁሉም ቦታ ማለት ይቻላል በተለይ ኦሮሚያ ላይ ኢዴፓ ትልቅ ተቀባይነት ያለው ፓርቲ ነው፡፡ ወደ 80 የሚጠጉ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ አባሎችና አመራሮች አሉን በኦሮሚያ፡፡ እነኚህ ደግሞ ለእዚህ አዲሱ ፓርቲ ትልቅ ውበት የሰጡ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ትግራይም ላይ እንደዚሁ ኢዴፓ ሽፋን የነበረው ፓርቲ ስለነበር፣ በዛ በኩል ያሉ አባላቶቻችንን ስድስት የሚሆኑ የምርጫ ወረዳዎች በዚህ ውህደት ውስጥ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

ግዮን፡- በቀጣይነት ከውህድ ፓርቲው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ይጠብቅ?

ዶ/ር ጫኔ፡- እየተሰበሰቡ መበታተን የብዙ ኢትዮጵያውያን ስጋት እንደሆነ እናውቃለን፡፡ ይሄ አዲሱ በአደረጃጀት ተቀርፏል፡፡ ከዚህ በኋላ ይሄ አይኖርም፡፡ ፓርቲዎች አንድ ከሆኑ በኋላ የሚፈርሱበትን ዕድል ከመጀመሪያው እንዲዘጋ ነው ያደረግነው፡፡ ከወረዳ ምርጫ ጣቢያ ላይ አባላቶቻችንን ስለምናዋሀድ እንዲሁም ከውህደቱ በፊት የነበሩበት ፓርቲ ስለሚከስም፣ ከላይ የተነሳው አሳሳቢ ችግር እንዳይፈጠርና ህዝብ ስጋት ላይ እንዳይወድቅ መንገድ ዘግቷል፡፡

ይሄን ስጋት በዚህ መንገድ የምንቀርፍ ከሆነ ፓርቲው በጣም ትልቅ የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡ በተወሰነ የአደረጃጀት እንቅስቃሴ እንኳን እስከ312 የሚደርሱ የምርጫ ወረዳዎች ናቸው የተቋቋሙት፡፡ ከዚህ በፊት በሀገሪቱ ጠንካራ ፓርቲ የለም ይባል የነበረውን ነገር በቀረፈ መልኩና ተፎካካሪ ፓርቲ ሆኖ ሊቀርብ የሚችል፣ ወደ ፊት ምርጫው ሲደረስ ማኒፌስቶአችንን ግልፅ አድርገን ቅስቀሳ ስናደርግ፣ ደግሞ ደረጃችን የት ጋር እንዳለ በደንብ እንረዳለን፡፡ ፍፁም ሰላማዊና ተአማኒ የሆነ ምርጫ ማድረግ የምንችል ከሆነ መቶ ፐርሰንት ገዢው ፓርቲ አሸንፏል የሚባልበትን መንገድ ሰብረን፣ ብንችል የምናሸንፍበት ካልሆነም ተመጣጣኝ ድምጽ የምናገኝበት ሁኔታ ይፈጠራል ብዬ አስባለሁ፡፡

ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡

# “አማራጭና የተሻለ የፖለቲካ ፕሮግራም ይዘን ቀርበናል”

## (አቶ አዲስ ዲንሳ)



ግዮን፡- አ.ት.ፓ (አዲስ ትውልድ ፓርቲ) መቼ ነበር የተመሰረተው?

አቶ አዲስ፡- እኔ ፓርቲው ከተመሰረተ በኋላ ነው የገባሁት፡፡ ግን ድርጅቱ አሁን ከተመሰረተ ሰባት ዓመት ሆኖታል፡፡ በምስራቅም፣ በምዕራብም፣ በሰሜንም፣ በደቡብም አባላቶች አሉት፤ ሀገር አቀፍ ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን፡፡

ግዮን፡- በአትፓ ውስጥ የእርስዎ የስራ ድርሻ ምን ነበር?

አቶ አዲስ፡- የፓርቲው የውጭ ግንኙነት ኃላፊ ነበርኩ፡፡ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና ስራ አስፈፃሚም ነበርኩ አትፓ ከመክሰሙ በፊት፡፡ በዚህ ውህደት ላይ ትልቁ ነገር ሰው እንዳስተሳሰቡ የሚጓዝ ነውና መጀመሪያ ልዩነቶች ነበሩ፤ ግን መጨረሻ ላይ ከጥቂት ሰዎች ወጪ በሙሉ ድምፅ ውሳኔ አሳልፈን ነው ትልቅ ሀገራዊ ፓርቲ ለመመስረት ወደ ውህደቱ የተቀላቀልነው፡፡

ግዮን፡- ወደ ውህዱ የዜግነት ፓርቲ ለመምጣት መነሻችሁ ምን ነበር?

አቶ አዲስ፡- ትልቁና ዋነኛው የመግባባታችን ነጥብ ሀገሪቷ የምትገኘው ከፍተኛ ችግር ውስጥ በመሆኗ፤ ይህቺን ሀገር ለማዳን ሁላችንም አንድ ላይ ተባብረን መስራት ካልሆነ በተስተቀር፣ አሁን ያለውን የዘረኝነት መንፈስ ያለበትን አካሄድ መታገል አዳጋች ነው የሚሆነው የሚል እምነት ስለያዝን፤ በጋራ ያንን አክራሪ ኃይል ታግለን፣ ሀገሪቷን በሰላምና በተሻለ ሁኔታ እንድትሆን መተባበሩ ውጤታማ እንደሚያደርግ በማመናችን ጭምር በፖለቲካ አመለካከት ከሚመስሉን ድርጅቶች ጋር በመግባባት፣ በመነጋገር ውህደቱን ልንፈፅም ችለናል፡፡

ግዮን፡- የብሔርተኝነት ስሜቱ መንሰራፋቱንና ፓርቲዎችም በዘር ላይ ተንጠላጥለው በስፋት መቋቋማቸው፤ በቀጣይነት የዜግነት ፖለቲካ ለምታራምዱ አካላት ችግር አይሆንም?

አቶ አዲስ፡- በፍፁም ምንም ዓይነት ችግር አይገጥመንም፡፡ ምክንያቱም ሁለታችንም ሀሳብ ነው ያለን፤ ሀሳባችንን ለህዝብ ነው የምናቀርበው፡፡ ሕዝብ ደግሞ የሚፈልገውን ነው የሚደግፈው፤ ሕዝቡ የሚፈልገው ብሔርተኝነትን ከሆነ ብሔርተኝነት ያሸንፋል ማለት ነው፡፡ ሕዝቡ የሚደግፈው ግን አንድነትን ከሆነ እኛን ይመርጠናል፡፡ ዋናው ሜዳ ሕዝቡ ጋር ስለሆነ እኛ እንደ አክቲቪቶች እርስ በርስ የምንጋጭበት ሁኔታ ያለ አይመስለኝም፡፡

መታወቅ ያለበት ትልቁ ነገር እኛ ፈፅሞ እነሱን ብለን አንሰራም፡፡ የምንሰራው ሀገራችንን ለማዳን ነው፡፡ ኢትዮጵያ ማለት የሁሉ ብሔር ውጤት ናት፡፡ አንዱን ከአንዱን ለመለየት “ይሄ የእከሌ ብሔር ነው” የሚባለውነገር ግራ ነው የሚያጋባኝ፡፡ ምክንያቱም አካልን የመቁረጥ ያህል ነውና፡፡ አንድ ቤተሰብ ውስጥ የሁሉም ብሔር ሰዎች ይኖራሉ፤ ያንን ምን ታደርገዋለህ?

ሁሌም ትግላችን ሀገራችንን አንድ አድርገን በብሄርም፣ በጎሳም ሳትከፋፈል ወደ ፊት የምትቀጥልበትን መንገድ ማመቻቸት ነውና በዚህ ረገድ ብዙም ችግር ይገጥመናል ብለን አናስብም የተሻለና አማራጭ ፖለቲካ ይዘን ቀርበናል፡፡

ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስና በቤተ ክህነቱ ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነት አስተዋፅኦ እንደነበራቸው የሚነገርላቸው ብፁዕ ወቅዱስ ሊቀጳጳስ ዶ/ር አቡነ ገሪማ ባለፈው ዕሁድ ሚያዝያ 27 ቀን 2011 ዓ/ም ረፋድ ላይ ህክምናቸውን ሲከታተሉ በነበረበት ባልቻ ሆስፒታል ህይወታቸው አልፏል። ቅዱስነታቸው እስከ ፋሲካ ማግስት ሠኞ (ማዕዶት) ድረስም በስራ ገበታቸው ላይ እንደነበሩና ህመም ከጀመራቸውም በኋላ በቅዱስ ፓትርያርኩ ትዕዛዝ መሰረት ወደ ሀኪም ቤት ሄደው በህክምና ሲረዱ መቆየታቸውን ለመረዳት ተችሏል።


በ1937 ዓ/ም ከአቶ ወ/ቂርቆስ አሸብርና ከወ/ሮ ፅጌ ማርያም ወልደመድህን በሸዋ ክፍለ ሀገር ኢቲሳ ደብረ ፅላልሽ አቡነ ተ/ኃይማኖት ገዳም የተወለዱት ብፁዕ ወቅዱስ ሊቀ ጳጳስ ዶ/ር አቡነ ገሪማ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ህፃን የልጅነት ጊዜያቸውን በአካባቢያቸው እንዳሳለፉና የድቁና ትምህርት በመከታተል የድቁና ማዕረጋቸውን ከግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ የተቀበሉ ሲሆን፤በ1973 ዓ/ም ማዕረገ ምንኩስናን በደብረ ሊባኖስ ገዳም መቀበላቸውን የህይወት ታሪካቸው ያስረዳል።ሊቀ ጳጳስ ዶ/ር አቡነ ገሪማ በሦስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሀይማኖት አንብሮተ ዕድ ሐምሌ 9 ቀን 1973 ዓ/ም ኤጲስ ቆጶስነት ተሾመዋል፡ ፡ ብፁዕነታቸው በቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ታላቅ አባት ናቸው። በተለያዩ የስራ ሀላፊነቶች ላይም በመሾም የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ሲወጡ መቆየታቸውንም የቤተክርስቲኒቱ ሰዎች ይናገራሉ። ለዚህም አገልግሎታቸው ብቁ ያደረጓቸውን ዕውቀቶች በሚገባ የቀሰሙ ሲሆን፣ በመንፈሳዊው የትምህርት ዘርፍ በቤተ ክርስቲያኒቷ ልዩ ልዩ ገዳማትና ስፍራዎች የሚሰጡትን ዜማ፣ ቅኔ፣ አቋቋም የተሰኙ የትምህርት አይነቶች ከተለያዩ መምህራን ቀስመዋል።

ዘመናዊ ትምህርታቸውን በሐረር የራስ መኮንን አዳሪ ትምህርት ቤት እና በቅድስት ስላሴ ትምህርት ቤት በመማር የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። በ1958 ዓ.ም ወደ አውሮፓዊቱ አገር ሮማንያ ተልከው በቡካሬስት ዩኒቨርሲቲ በታሪክ ትምህርት የማስተርስ ዲግሪ እንዲሁም በነገረ መለኮት የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ለመቀበል የበቁ፤ በትምህርቱ መስክ የላቀ ውጤት የነበራቸው አባት እንደነበሩ በብዙዎች ዘንድ ይመሠከርላቸዋል።

በሌላም በኩል በአምስተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ የሹመት ዘመን የፓትርያርኩ የቅርብ ሰውና ብርቱ ምስጢረኛ እንደነበሩና የቤተ ክህነት ስራ አስኪያጅ ሆነው በሚሰሩበት ወቅትም የፓትርያርኩ ስም በተነሳ ቁጥር የእርሳቸው ስምም አብሮ ይነሳ እንደነበር የሚታወስ ነው። ፓትርያርኩ ተቃውሞ በገጠማቸው ስፍራዎች ሁሉ አብረዋቸው ይጓዙ እንደነበር፤ እንዲሁም በአገር ውስጥ በቀጨኔ መድሀኒአለምና በቅዱስ እስጢፋኖስ፤ በውጭ ደግሞ በአሜሪካ ሜሪላንድ ባልቲሞር ላይ ፓትርያርኩ ላይ ተቃውሞ ሲደርስና ቲማቲምና የገማ ዕንቁላል ሲወረወርባቸው ከጎናቸው በመሆን ፅኑ ደጋፊያቸው እንደነበሩ ብዙዎች ይናገራሉ።

ብፁዕ ወቅዱስ ዶ/ር አቡነ ገሪማ በ1990ዎቹ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን ውስጥ አወዛጋቢ አቋም ነበራቸው የሚሉ ቢኖሩም፤ በዚያው መጠን ደግሞ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገትና መጠናከር ወደር የሌለው ሚና እንደተጫወቱ የሚገልፁ ወገኖችም አልጠፉም። ብፁዕነታቸው በሁለት የተከፈለ አስተያየት ውስጥ የማለፋቸውን ያህል ግን በመንፈሳዊም ሆነ ሌሎች አገልግሎታቸው ላይና ለእምነቱ የነበራቸው ቀናኢነት የተለየ እንደነበረ በስርዓተ ቀብራቸው ላይ ስብከተ ወንጌል ያሰሙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቀውስጦስ ተናግረዋል። ብፁዕነታቸው፦ ‹‹ብፁዕ አባታችን ከተማሪ ቤት መልስ በአራት ኪሎ አጠገብ በምትገኘው መንበረ ፀባኦት ቅድስት ስላሴ ገድመው የኖሩ፣ ራሳቸውን የጠበቁ፣ የወጣትነት ጠባይ ያላሸነፋቸው ጠንካራ የቤተ ክርስቲን ልጅ እንደነበሩ አውቃለሁ። ቅድስናውንም፣ ቁምስናውንም፣ ጵጵስናውንም ያገኙት በጠንካራ ዓላማቸው ነው። በፅኑ ሀይማኖታቸው ቅድስናን፣ ድንግልናንና አገልግሎትን አስተባብረው ይዘው በመገኘታቸው ሁሉ ነገር የተፈፀመላቸው ቅዱስ አባት ናቸው›› ሲሉ ለብፁዕ ዶ/ር አቡነ ገሪማ ያላቸውን ምስክርነት ሠጥተዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ዶ/ር አቡነ ገሪማ በዐበይት በዓላት ላይ በሚያቀርቧቸው በቤተክርስቲያን ታሪክና ሀዋርያዊ ተልዕኮ ላይ በሚያተኩሩ ፅሁፋዊ ስብከቶችና ትምህርቶች ይታወቃሉ። ከ30 በላይ የተምህርታዊ ፅሁፎች ስብስብም በ2006 ዓ/ም ለህትመት ያበቁ ሲሆን፤ ከዚያ በፊትም ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ›› የሚል መፅሀፍ ለንባብ አብቅተዋል፡፤ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የሆኑ፦



1ኛ. “ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ መስፋፋት ጎልተው የሚታዩ ዘመናት” የሚል ባለ 150 ገፅ ፅሁፍ፤

2ኛ. “በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስርዓተ ቅዳሴና በባዛንታይን ስርዓተ ቅዳሴ የማወዳደር ጥናት” በሚል ርዕስ 234 ገፅ ፅሁፍ አዘጋጅተው አቅርበው እንደነበረም በጥቅምት 1992 ዓ/ም ታትሞ ከወጣው “ኢትኦጵ” መጽሄት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ ገልፀው ነበር።

ብፁዕ ወቅዱ አቡነ ገሪማ ከቢሯቸው የማይጠፉ፣ ምንም እንኳን እርግናው ቢያስቸግራቸውም የተሰጣቸውን ሀላፊነት ለመወጣት በጠዋት የስራ ገበታቸው ላይ የሚገኙ እንደነበሩ የተናገሩት ደግሞ የኢትዮጵያ ፓትርያክ ብፁዕ ወቅዱ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ናቸው።

ብፁዕነታቸው ቤተክርስቲኒቱን ያገለገሉባቸው ስልጣናትና ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው፦

በሱዳን - ካርቱም ኤጲስ ቆጶስነት ፤ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት፣ የድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የልማት እና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ኮሚሽነር፣ የቅድስት ሥላሴ እና የቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጆች ዲን፣ በመንበረ ፓትርያርኩ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ቢሮ ዋና ጸሐፊ፣ የምስካየ ኅዙናን መድኀኔዓለም ገዳም ሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ፣ የቦሌ ደብረ ሳሌም መድኀኔዓለም ወመጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ካቴድራል እና የካራኣሎ ደብረ ቅዱስ ደብረ ቀርሜሎስ መድኀኔዓለም እና ጻድቁ አቡነ ገሪማ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ፤ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት የውጭ ግንኙነት የበላይ ሓላፊ፤ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ምክትል አስተዳዳሪና ዋና ጸሐፊ፣ የትምህርት እና ማሠልጠኛ መምሪያ ሓላፊ፣ በብሥራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ በመምህርነት ይገኙባቸዋል።

ብፁዕ ዶ/ር አቡነ ገሪማ ሚያዝያ እሁድ 27 ቀን 2011 ዓ/ም ረፋድ ላይ በባልቻ ሆስፒታል ነበር ያረፉት። አስከሬናቸው ሚያዝ 29 ቀን 2011 ዓ/ም በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ስላሴ ካቴድራል የተለያዩ የፀሎት ስርዓቶች ሲደረግለት አድሮ ረቡእ ሚያዝያ 30 ቀን 2011 ዓ/ም የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ፤ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀደማዊ ሊቀጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሀይማኖት፤ ብፁዐን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቀሳውስት፣ ጥንግ ድርብ የለበሱ የአዲስ አበባና አካባቢዋ አድባራትና ገዳማት ተወካዮች፣ የሠንበት ተማሪዎች፣ የመንፈሳዊ ኮሌጅ መምህራንና ደቀመዛሙርት፣ የንስሃ ልጆቻቸው፣ ወዳጅ ዘመዶቻቸውና ምዕመናን በተገኙበት ስርዓተ ቀብራቸው ተፈፅሟል።



ብሩክ መኮንን

# ጆን ሚሊ ኢትዮጵያውያንን እየረዳ ፤ በኢትዮጵያዊ የተገደለው ዶክተር!

***ሚያዝያ 27 በኢትዮጵያ አርበኞች ያላሰለሰ ትግል፣ ለአምስት አመታት ኢትዮጵያውያን በኃይል ይዞ የነበረው የኢጣልያ ጦር ተሸንፎ የተባረረበት ሰባ አምስተኛ የድል በዓል ከብሯል፡፡ ኢትዮጵያውያን በአያት አባቶቻችን መስዋዕትነት የተገኘውን ድል ስናስታውስ፤ ዛሬ ለምንገኝበት ነፃነት እንድንበቃ የተከፈለውን ዋጋ እንዲሁም የሀገር ባለውለታ የሆኑ አርበኞችን የተጋድሎ ታሪክ ማወቅና መዘከር፣ ትውልድ ተሻጋሪም እንዲሆን የበኩላችንን አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርብናል፡፡***



በዛሬው የግዮን የታሪክ አምድ ከ83 አመት በፊት ኢጣልያ በዘመናዊ የጦር ኃይል፣ በአውሮፕላን፣ በመርዝ ጋዝና ቦንብ እየታገዘ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን ከወራሪ ጠላት እጅ እንዳትወድቅ የፈፀሙትን ተጋድሎ እንዲሁም በአለምአቀፉ ሕግ የተከለከለውን መርዝ እና ቦንብ የኢጣልያ ጦር በማን አለብኝነት ሲያዘንብባቸው የመመልከትና ተጎጂዎችን በማከም ስራ ላይ ተሰማርቶ ሕይወቱን የገበረው ዶክተር ጆን ሚሊን እንዘክራለን፡፡

ዶክተር ሚስናርድ ሚሊ የእንግሊዝ ቀይ መስቀል የአምቡላንስና የሕክምና ባለሙያዎችን የያዘ፣ የበጎፍቃደኞች ቡድንን በመምራት ነበር የኢትዮ ጣልያን ጦርነት ሲቀሰቅስ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው፡፡የፋሽስት ኢጣልያ አየር ኃይል አውሮፕላኖች በአለም አቀፍ ሕግ መሰረት ከጥቃት ነፃ መሆን ያለባቸው፣ የጦር ጉዳተኞችን ለማከም የሚንቀሳቀሱ የቀይ መስቀል የሕክምና መስጫ ተቋማትን፤ ሆን ብለው በመደብደብ በየቦታው የተቋቋሙ የድንኳን ሆስፒታሎችን ሲያወድም ከአንድም ሁለት ጊዜ ከጥቃቱ ተርፏል፡፡

እንግሊዛዊው ዶክተር ጆን ሚሊ ከጦርነቱ ቀደም ብሎ ባሉት ዓመታት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በአዲስ አበባ ሆስፒታልና የሕክምና ትምህርት ቤት ለመክፈት ተንቀሳቅሶ ነበር፡፡ ሆኖም በጊዜው የነበረው የመንግስት አሰራር መሰናክል ስለሆነበት ወደ ሀገሩ ተመልሶ ነበር፡፡

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በወሎ፣ በትግራይ ጠቅላይ ግዛቶች፣ ከኢጣልያ ጦር ጋራ ሲፋለሙ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ተዋጊዎችን ሕይወት ለመታደግ የተሰማሩ የሌሎች ሀገራት የቀይ መስቀል የበጎ ፍቃደኛ ሐኪሞችን በማስተባበር፤ ለወራት ያለእረፍት የሰራው ዶክተር ጆን ሚሊ በጦርነቱ በተለይ ማይጨው ላይ በደረሰው ሽንፈት፣ የኢትዮጵያ ጦር ተመቶ ጦሩ ሲበተን ወደ አዲስ አበባ ሲያፈገፍግ የሚመራውን የእንግሊዝ የቀይ መስቀል የሕክምና ቡድን ይዞ ወደ አዲስ አበባ ያቀናል፡፡

ከጥቂት የጦር አዛገሮቻቸው ጋር ወደ አዲስ አበባ ያቀኑት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ በቀጣይ ስለሚወስዱት እርምጃ ከአማካሪዎቻቸውና ከመሳፍንቱ፣ ከመኳንንቱ ጋራ የምክክር ጉባኤ ተቀምጠው፤ በሕዝባቸው ላይ የደረሰውን ጥቃት በተመለከተ ለሊግ ኦፍ ኔሽን አቤቱታ ለማቅረብ በስደት እንዲቆዩ በመወሰኑ፤ ንጉሱ ቤተሰባቸውን አስከትለው በባቡር ወደ ጅቡቲ ሲያመሩ፣ ዶክተር ጆን ሚሊ የሚመራው የእንግሊዝ የቀይ መስቀል የሐኪሞች ቡድን አዲስ አበባ ውስጥ ሆኖ ሕክምና እርዳታ እየሠጠ ነበር፡፡

የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ወደ ውጭ ሀገር መሰደድን ተከትሎ በአዲስ አበባ ስርዓት አልበኝነት፣ ዝርፊያና ግድያ ነግሶ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ መላዋ አዲስ አበባ ሁከት፣ ዝርፊያና ግድያ ነገሰባት፡፡በከተማይቱ ወረበሎች በየሱቁ እየገቡ ሸቀጣሸቀጦችን መዝረፍ፣ እንዲሁም በከተማይቱ ይኖሩ የነበሩ የየትኛውም ሀገር ዜጋ የሆኑ የውጭ ሰዎችን ሲያገኙ ያለምህረት መግደል ጀመሩ፡፡

በወቅቱ አዲስ አበባ የንጉሱ የሕግ ጉዳዮች አማካሪ የነበረው አሜሪካዊው ጆን ስፔንሰር የሁኔታውን አሳሳቢነት በመረዳት ሠራተኞቹን ይዞ ወደ አሜሪካ ኤምባሲ በማምራት፣ በወቅቱ የአሜሪካ አምባሳደር ከነበሩት ቫን ኤች አንገር ጋራ ተወያየ፡፡ አምባሳደሩም ስፔንሰር ሠራተኞቹ ቤተሰባቸውን ይዘው በሌጋስዮኑ እንዲጠለል ፈቀዱ፡፡

ከተማይቱ በተኩስ እየተናጠች ነው፤ ከዝርፊያው በተጨማሪ ያገኙትን መጠጥ እየጠጡ፣ በስካር ያገኙት መኖሪያ ቤትና መደብር፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን የሚዘርፉት ወረበሎችም እርስ በርሳቸው መጋደል ጀመሩ፡፡ ለሶስት ቀን በዚህ መልክ በቀጠለው ሁከት ወደ ስምንት መቶ ኢትዮጵያውያን ሕይወታቸውን ሲያጡ፤ አብዛኛዎቹ ግሪካውያን፣ አርመናውያን እንደሆኑ የሚታመን ወደ ሰላሳ የሚደርሱ የውጭ ሀገር ዜጎች ተገደሉ፡፡

ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ መሆኑን የተረዳው የአሜሪካ መንግስት ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮርኔል ሄል በአዲስ አበባ የተፈጠረው ስርዓት አልበኝነትና ትርምስ እንዲቆም ለቤኔቶ ሞሶሎኒ ጦሩን ፈጥኖ ወደ አዲስ አበባ እንዲያስገባ ጠየቀ፡፡ይህ ለሶስት ቀናት የቀጠለ ትርምስና ግድያ በነገሰባት አዲስ አበባ በተባራሪ ጥይት እየተመቱ፣ በየቦታው የወደቁ የከተማይቱን ነዋሪዎች ሕይወት ለማትረፍ በዶክተር ጆን ሚሊ የሚመራው የእንግሊዝ ቀይ መስቀል የበጎ ፍቃደኞች ቡድን ያለ እረፍት ታላቅ ስራ ሰርቷል፡፡

በአራተኛው ቀን ልክ በዛሬው ቀን፣ ከ83 ዓመት በፊት ሚያዝያ 26 ቀን 1928 ማለዳ፤ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ ነበር በየአካባቢው በተባራሪ ጥይት፣ እንዲሁም ያለምንም ምክንያት እንደ ኢላማ ተኩስ መለማመጃ፤ በወረበሎቹ በጥይት ተመተው እያጣጣሩ የሕክምና እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ተጎጂዎች ሕይወት ለማትረፍ በማሰብ በዶክተር ጆን ሚሊ የሚመራው የብሪታኒያ ቀይ መስቀል የአምቡላንስ ➔

ቡድን፣ አባላቱን በማስተባበር ለሕይወቱ ሳይሳሳ፣ በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ወደምትገኘው የአዲስ አበባ ከተማ እምብርት አራዳ ጊዮርጊስ አመራ፡፡

ዶክተር ጆን ሚሊከሌላው ከእንግሊዛዊ ባልደረባው ጋር አምቡላንሱን እየነዳ ጉዞውን በዋናው አውራ ጎዳና ላይ እንደቀጠሉ፣ ከዋናው መንገድ ተገንጥሎ ወደ መኖሪያ መንደሮች የሚያስገባ ኮረንኮች መንገድ ላይ ቆስሎ የወደቀ ሰው ተመለከቱ፡፡ የተለመደውን ሕይወት የማዳን ሥራ ለመስራት ወደዚያ ሰው ያመራሉ፡፡ በወቅቱ ባልደረባው ወደ ተጎዳው ሰው ሲሄድ፣ዶክተር ጆን ሚሊ ግን ከአምቡላንሱ አልወረደም ነበር፡፡ ወዲያው ግን ከኋላው ካኪ ኮት፣ ተነፋናፊ ሱሪ ያደረገ ወሮበላ፤ ወደ አምቡላንሱ በመጠጋት በመስኮት በኩል ዶክተሩ ላይ "ፈረንጅ!" ሲል ያንባርቅበትና ሽጉጡን አነጣጥሮ ተኮሰ፡፡

በመጠጥ የናወዘው ወሮበላ ጆን ሚሊን ደረቱ ላይ ነበር የመታው፡፡ በተፈጠረው አስደንጋጭ ነገር ለጊዜው በድንጋጤ የሚሆነውን ሁሉ ሳያውቅ "ጆን! ጆን" እያለ ዶክተሩን ሲጣራ የቆየው ጓደኛው ጆን ሚሊን ወደ ሰፈር ለማድረስ አምቡላንስዋን ሲያንቀሳቅስ ነበር ለተመሳሳይ ተግባር በዶክተር ጆኖ ሚሊ ትዕዛዝ በከተማዋ ቁስለኞችን ለማከም የተሰማራ የብሪታኒያ ቀይ መስቀል አምቡላንስ አገልግሎት ባልደረቦችን የያዘው ሌላ አምቡላንስ ካሉበት ቦታ የደረሰችው፡፡

ሁለተኛዋን አምቡላንስ ሲያሽከርክር የነበረው ፋርማሲስቱ ኤልጄ ቡነር የሕክምና እርዳታ ሰጭዎቹን ደህንነት ለመጠበቅ የታጠቁ ኢትዮጵያውያን ወታደሮችን ይዞ ነበር፡፡ አምቡላንሱን እንዳቆመም ጋትውልድ የተሰኘውን የዶ/ር ጆንሚሊ ባልደረባ ምን እንደተፈጠረ ለመጠየቅ ወደ አምቡላንሱ ጠጋ ሲል፣ ደም በደም የሆነውን የቡድናቸውን አስተባባሪ ጆን ሚሊ ከአምቡላንሱ የኋላ ወንበር ላይ ተዘርሮ ተመለከተ፡፡

ኤልጄ ቡነር የአምቡላንሱን በር ከፍቶ የተዘረረውን ጆን ሚሊን ቁስል ሲመለከት ጥይቱ በቀጥታ ሳምባውን ቦትርፋ ያለፈች መሆኗን ስለተረዳ ፣ ሕይወቱን ለማትረፍ በአፋጣኝ ወደ ዋናው ሰፈራቸው እንዲወስደው ነግሮት እሱም ከኋላ ሊከተለው ወደ አምቡላንሱ ሊሄድ ሲል በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ ያለውና ራሱን ገና ያልሳተው ዶክተር ጆን ሚሊ " የመታኝ ሰውዬ ሰክሯል፡፡ ምን እንደሚያደርግም አያውቅም፡፡ እኔ ላይ ላደረሰው ነገር ለመበቀል እናንተ በማንም ላይ እንዳትተኩሱ፤ ሌላ ደም መፋሰስን አልፈልግም፡፡" ሲል በንዴትና በድንጋጤ የሚያደርገው ያጣውን ኤልጄ ቡነርና ኢትዮጵያውያ አጃቢዎቹን ተማፀነ፡፡

አምቡላንሶቹ እየተከታተሉ ወደ ሆስፒታል አመሩ፡፡ የዶክተር ጆን ሚሊን ሕይወት ለመታደግ ሐኪሞቹ በሙሉ ተረባረቡ፤ የቀዶ ጥገና ሕክምና ካደረጉለት በኋላ ለመተንፈስ ያጋጠመውን ችግር እልባት ለመስጠት ኦክስጅን በመስጠት አድርገው ጆን ሚሊ ከሚያስተዳድረው ሆስፒታል፤ ሀያ አራት ሰዓት የቅርብ ክትትል የምታደርግለት አውሮፓዊት ነርስ በመመደብ፣ለደህንነቱ በማሰብ ወደ ብሪቲሽ ሌጋስዮን ተወስዶ በእዚያ እንዲተኛ አደረጉ፡፡

ዶክተር ጆን ሚሊና የሆስፒታሉ ሀኪሞች በሙሉ እሱን ለማዳን ሲረባረቡ ሲያይ "እኔን እንደ ማንኛውም ድንገተኛ አደጋ የደረሰበት ሕመምተኛ አድርጋችሁ አክሙኝ፤ ሌሎች አደጋ ወደ ደረሰባቸው ቁስለኞች በመሄድ እንደ እኔ ተረባርባችሁ ለማዳን ከመስራት ወደ ኋላ እንዳትሉ፡፡ አደራ!" ሲል እየቃተተ ነበር ያስጠነቀቃቸው፡፡በእርግጥም ዶክተር ጆን ሚሊ ሳያስጠነቅቃቸው እነርሱም በነዚያ ቀውጢ ቀናት ያለ እረፍት በትጋት ነበር የሕይወት ማዳን ስራቸውን ሲሰሩ የዋሉት፡፡ ህክምና እየሰጡ እያለም በተለይ ምሽት ላይ ከየት እንደሚተኮሱ ያልታወቁ ጥይቶች የሆስፒታሉን ሕንፃ፣ ግድግዳዎችን እየመቱ፣ የጣሪያ ቆርቆሮ ላይ ሲያርፍ በስጋት ሲያዳምጡና ሲያዩ ነበር ያሳለፉት፡፡

ጆን ሚሊ ወደ እንግሊዝ ሌጋስዮን ቅጥር ግቢ ከተወሰደ በነጋታው እንዴት እንዳደረና በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ በቀዶ ጥገና በተደረገለት አካባቢ የተደረገለት ፋሻ ሲቀየር ዶክተር ደብሊው ኤስ ኤም ወደ ሌጋስዮኑ አመራ፡፡ዶክተሩ ጆን

> ...ዶክተሩ ጆን ሚሊን ከተኛበት አልጋ ላይ ሆኖ ሲያገኘው ጤንነቱ ደህና ሁኔታ ላይ የሚገኝ የሚመስል መረጋጋትና ብርታት ይታይበት ነበር፡፡ ነገር ግን ሁኔታው ይህንን ይምሰል እንጂ ተስፋ አስቆራጭም ደረጃ ላይ ነበር ቢቆይም እንደሚሞት የታወቀ ነበርና...

ሚሊን ከተኛበት አልጋ ላይ ሆኖ ሲያገኘው ጤንነቱ ደህና ሁኔታ ላይ የሚገኝ የሚመስል መረጋጋትና ብርታት ይታይበት ነበር፡፡ ነገር ግን ሁኔታው ይህንን ይምሰል እንጂ ተስፋ አስቆራጭም ደረጃ ላይ ነበር ቢቆይም እንደሚሞት የታወቀ ነበርና ፡፡ዶክተር ደብሊው ኤስ ኤምፓይ ወደ ሆስፒታሉ ከተመለሰ በኋላ ሰዓታት ባለፉ ቁጥር የጆን ሚሊ ሁኔታም ቀስ በቀስ እየተባባሰ ሄደ፡፡ በዚህ ወቅት ሰር ሲድኒ በርተንና ሌሎች የእንግሊዝ ሌጋስዮን ሹማምንት ዶክተር ጆን ሚሊ ለመጨረሻ ጊዜ ከእናቱ ጋር እንዲገናኝ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡

ዶክተር ጆን ሚሊ ከተኛበት አልጋው ላይ ቁጭ ለማለት እንኳን አቅም አንሶት እያቃሰተ፣ የምትከታተለውን ስዊድናዊት ነርስ "እባክሽ ላስቸግርሽ እጄን ያዥኝ! አንቺም እኮ እረፍት ማድረግ አለብሽ፣ ልትተኚ ይገባል" በማለቱ፤ በመከራ ትራስ ተደራርቦ፣ ከጀርባው፣ ተደርድሮላት እሱን ተደግፎ ቁጭ አለ፡፡ በሽቦ አልባው የቴሌግራም ማስተላለፊያ መሳሪያ ለእናቱና ለመላ ቤተሰቡ የግሉን መልዕክት ክብርና ሠላምታ የገለፀበትን መልዕክት አስተላለፈ፡፡ እናቱም ለልጃቸው መልዕክት ምላሽ ሰጡ፡፡ ዶክተር ጆን ሚሊ ለመጨረሻ ጊዜ ለእናቱ የፃፈው መልዕክት እንዲህ የሚል ነበር፡፡ "በእውነት ነው የምለው እኔ በሆነው ሁሉ፣ በሚሆነውም ደስተኛ ነኝ" ሲል ነበር ያሰፈረው፡፡

የኢጣልያ ጦር ወደ አዲስ አበባ ከተማ በገባ በመጀመሪያ ቀን ማታ ሶስት ሰዓት ላይ ዶክተር ጆን ሚሊ ከዚህ አለም በሞት ተለየ፡፡ የጆን ሚሊ ሞት በአዲስ አበባው የሶስት ቀናት የነገሰ ሁከት ሥርዓት አልበኝነት የሞቱት አውሮፓውያንን ቁጥርን አስራ አራት አደረሰው፡:ጣልያኖች አዲስ አበባ ከተማን በያዙ በሁለተኛው ቀን ሚያዝያ 20 ቀን 1928 ዓ.ም፤ በእንግሊዝ ሌጋስዮን ቅጥር ግቢ ውስጥ ባለ ጭር ያለ የአትክልት ስፍራ፣ የዶክተር ጆን ሚሊ የቀብር ስነ ስርዓት በሌጋሲዮኑ ተጠግተው የሚገኙ አውሮፓውያን ዜጎች በተገኙበት ተፈፀመ፡፡

በአዲስ አበባ የቀብሩ ስነስርዓት ከተፈፀመ ከቀናት በኋላ ለዶክተር ጆን ሚሊ መታሰቢያ በለንደን የሴንት ማርቲን ፊሊጶስ ካቴድራል በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ እንግሊዛውን የታደሙበት ስነስርዓት ተካሄዶ ነበር፡፡ በስነስርዓቱ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የክትንበሪው ጳጳስ ራሞቹ ዶክተር ጆን ሚሊ ለፈፀመው ታላቅ አገልግሎትና ለከፈለው መስዋዕትነት መታሰቢያ ታላቁን የኤድዋርድ አራተኛ የጀግና ሜዳሊያ ከነሙሉ ክብሩ አበረከቱ፡፡

የእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ኤደን በበኩላቸው ለዶክተር ጆን ሚሊ እናት በላኩት የሐዘን መግለጫ መልዕክት " በዚህ እጅግ በሐዘን በተጎዱበት ሰዓት ልረብሾት አልፈልግም ነበር፤ ይቅርታ ያድርጉልኝና በልጅዎ አሳዛኝ ሞት የተሰማኝን ልባዊና ጥልቅ ሐዘኔን ስገልፅ በፍጥነት መጽናናትን ያገኙ ዘንድ በመመኘት ነው" ብለው ነበር፡፡

ሌላው በስነ ስርዓቱ ላይ የሐዘን መግለጫቸውን በኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት ስም ያስተላለፉት በእንግሊዝ የኢትዮጵያ ባለ ሙሉ ስልጣን አምባሳደር ዶክተር ቻርልስ ማርቲን (ሐኪም ወርቅነህ እሹቴ) "ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን እውነተኛ ወዳጅ የሆነው፣ በሙያው የብዙ ኢትዮጵያውያን ሕይወት የታደገው፣ ባለውለታችን ዶክተር ጆን ሚሊ ሕልፈት ምክንያት አንድ ሞገደኛ የሐገሬ ሰው መሆኑን ሳስብ ልቤ በሐዘን ያደማል፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ከሀዘንዎ ያፅናናዎት፣ ጠላትን ከሀገራችን አስወጥተን በድልአድራጊነት ወደ ሀገራችን ስንመለስ ለኢትዮጵያ ሠርቶ ለኢትዮጵያ ለሞተው ልጅዎመታሰቢያ ለማቆም ቃልእገባሁ" ብለው ነበር፡፡

ከዛሬ 78 ዓመት በፊት የፋሽስት ኢጣልያ ጦር ተሸንፎ የኢትዮጵያ ሠንደቅ አላማ በድል አድራጊነት ከፍ ብላ እንድትውለበልብ የሕይወት፣ የደም መስዋዕትነት የከፈሉ፤ በዚህም ለተጎናፀፈው ነፃነትና ድል ያበቁንን ጀግኖች ስናስብ ለኢትዮጵያ ሕይወታቸውን ከሰው አንዱ ዶክተር ጆን ሚሳናርድ ሚሊን እንዲህ አስታወስን፡፡ እንኳን ለ78ኛው የድል በዓል አደረሳችሁ!

# የነጻው ፕሬስ ጉዞ ከየት ወዴት?



ጃፈር ሰዩም

በደርግ ዘመን በማስታወቂያ ሚኒስትርነት ለአመታት ያገለገሉትና በዘመነ ኢህአዴግ ደግሞ የጦቢያ መጽሄት መስራችና ዋና አዘጋጅ የነበሩትና በቅርቡ በሞት የተለዩን ጋሽ ሙሉጌታ ሉሌ (ነፍሳቸው በሰላም ትረፍና) በተለይም በሥልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት ወደተለያዩ ሀገራት ተዘዋውረው የሌሎች ሀገራትን ልምድ ቀምሰው ወደ ሀገራችን ተመልሰዋል፡ ፡ በሠለጠኑ ሀገራት ህዝቡ ዴሞክራሲያዊ መብቱን ተጠቅሞ ሀሳቡን በነጻነት ሲገልጽ ተመልክተውና በፕሬሱ በኩል የነበረውን አፈና ተረድተው ማስታወቂያ ሚኒስትር በነበሩበት፤ በተለይም የደርግ የመጨረሻ አመታት የተለያዩ ማህበራትን በማደራጀት ህዝቡ የሚተነፍስበትን መንገድ ለማመቻቸት እየሞከሩ በነበሩበት ወቅት ኢህአዴግ አዲስ አበባን ተቆጣጠረ፡፡

የሽግግር መንግስት ተቋቁሞ መለስ ዜናዊ የፕሬዝዳንትነት ስልጣንን ሲቆጣጠር፤ የኦነግ ከፍተኛ አመራር አቶ ዲማ ነጋዎ በማስታወቂያ ሚኒስትርነት ተሾሙ፡፡

በሚያዝያ 1984 በአንዱ ቀን ማለዳ አቶ ሙሉጌታ ሉሌ በወቅቱ ማስታወቂያ ሚኒስትር ወደነበሩት አቶ ዲማ ነጋዎ ቢሮ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን አቀኑ፡፡ ወደ ሚንስትሩ ቀረብ ብለውም "አንድ መጽሄት ለማቋቋም አስበናልና እርዱን" በማለት ጥያቄ ያቀርቡላቸዋል፡፡ በወቅቱ ሀገራችን ሽግግር ላይ ነበረች፡፡ የፕሬስ ህግም ገና ይወጣል ተብሎ እየተጠበቀ በመሆኑ ሚንስትሩም ሁኔታውን በመግለጽ "የፕሬስ ህጉ እስኪወጣ ድረስ ምንም ማድረግ አልችልም" የሚል የክልከላ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
ሆኖም "የነጻው ፕሬስ አባት" ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉት ጋሽ ሙሉጌታ ሉሌ ተስፋ ቆርጠው እጅ መስጠትን ፈጽሞ አልፈለጉምና መላ ዘይደው ማስታወቂያ ሚንስትሩ ሊፈቅዱ የሚችሉበትን መንገድ አሳዩዋቸው፡፡ "ክቡር ሚንስትር ሆይ! ጽሁፎቻችንን ይዘን እንምጣና በሳንሱር በኩል ይለፉ!! ጥያቄዎች የሚያስነሱ ከሆነ ደግሞ ከ50 ገጽ በላይ አድርገን እናዘጋጀው" የሚል ሀሳብን አቀረቡላቸው፡፡ (በወቅቱ 48 ገጽ የሚደርስ መጽሄት ለማዘጋጀት አስበው ነበር)፡፡ 50 ገጽ ከሞላ በUNESCO ህግ እንደመጽሃፍ ሊቆጠር ሥለሚችልና በወቅቱ ማንኛውም መጽሃፍ ደግሞ ሳንሱር ተደርጎ ሊታተም ስለሚችል በሳንሱር በኩል አሳልፈው ሊያሳትሙ የሚችሉበትን መንገድ ጠቆሙ፡፡

ሚኒስትሩም ፍቃደኛ ሆኑና በሚያዝያ 1984 ጦቢያ ተወለደች፡፡ በወቅቱ ከላይ እንደተገለጸው የፕሬስ ህጉ አልጸደቀም፡፡ ከ6 ወራት በኋላ በጥቅምት 1985 አፋኙ የፕሬስ ህግ ጸደቀ፡፡ ጦቢያ የኢህአዴግን ኢሰብዓዊ ድርጊቶች በማጋለጥ ፈር ቀዳጅ ሆነች፡፡ የመጀመርያዎቹን የህትመት ውጤቶች የቀድሞው የኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጠኞች ማህበር(ኢነጋማ) ፕሬዝዳንት አቶ ክፍሌ ሙላት እንዲህ ያስታውሳቸዋል፦ "ጦቢያ፣ጸደይ፣ ሕብር እና ሩህ ለመጀመርያ ጊዜ ነጻ ፕሬሱን ተቀላቀለው ታትመው ለህዝብ መሰራጨት ጀመሩ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ እይታ፣ አዲስ ድምጽ፣ አዲስ ትሪቡን የተባሉ ጋዜጦች ብቅ አሉ፡፡ ህዝቡም በታላቅ አክብሮትና አድናቆት ተቀበላቸው፡፡" ይላል አቶ ክፍሌ ከ27 አመታት በፊት የነበረውን የፕሬሱን ጅማሮ ሲያስታውስ፡፡

ከዚያማ በመቶዎች የሚቆጠሩ የህትመት ውጤቶችም የአዲስ አበባን ጎዳና አጥለቀለቁ፡ ፡ በዚህም የተነሳ ጋዜጠኞቹ ከፍተኛ ወከባ ይፈጸምባቸው ጀመር፡፡ ፕሬሱን በእንጭጩ የመቅጨቱ ሂደት በይፋ ተጀመረ፡፡ ጸደቀ የተባለው የፕሬስ ህግም ሀሳብን በነጻነት መግለፅን አደገኛ ወንጀል አስመስሎት ቀረበ፡፡ ለይስሙላ የተፈቀደው የፕሬስ ነጻነት በርካታ ጋዜጠኞችን ለእስር፣ ለሥደትና ለሞት ዳረገ፡፡

"ኢትዮጲስ" ከሩብ ምዕተ ዓመት በፊት በ1985 ገደማ በእስክንድር ነጋ አሳታሚነት ነጻውን ፕሬስ ተቀላቀለች፡፡ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ የነበረው ተፈራ አስማረ በከፍተኛ እንግልት ታፍኖ፣ ተደብድቦ ከተሰቃየ በኋላ በፍትህ ሥም ፍትህን በሚደፈጥጠው ፍርድ ቤት በኢትዮጵያ ለመጀመርያ ጊዜ የ2 አመት እስራት ተፈርዶበት ፍርዱን ጨርሶ ተፈታ፡፡ ተፈራ በደረሰበት ከባድ ድብደባ ምክንያት ብዙም ሳይቆይ ህይወቱ አለፈ፡፡ ተፈራ አስማረ በነጻው ፕሬስ መስዋዕት በመሆኑ ታሪክ ሁሌም ያስታውሰዋል!
እስክንድርም "ዘ ሀበሻ" በሚል ስም ወደሚታተም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ጋዜጣ ተሸጋገረ፡፡ ወደ አማርኛ ተመልሶ በራሱና በባለቤቱ ሰርካለም ፋሲል አሳታሚነት ሳተናው፣ ምኒልክና አስኳል ጋዜጦችን እያሳተመ በፕሬሱ በኩል አስተዋጽኦውን ማበርከቱን እስከ ምርጫ 97 ድረስ ቀጠለ፡፡

ሲሳይ አጌና በኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ታሪክ ጉልህ ሚና ካላቸው ጋዜጠኞች ጎራ ይመደባል፡፡ ሲሳይ "ኢትኦጵ" የተሰኘችውን ተወዳጅ ጋዜጣ ለነጻው ፕሬስ አበርክቷል፡፡ ዘወትር ረቡዕ ገበያ ላይ የምትውለው ኢትኦጵ በድፍረት ከምትጽፋቸው ትንታኔዎቿና ትኩስ መረጃዎቿ በተጨማሪ ከገዢው ፓርቲ ውስጥ የሚወጡ ሚስጥሮችን ለህዝብ በማጋለጥ ትታወቃለች፡፡ በተለይም በቀድሞው የህወሃት ወታደር በጋዜጠኛ አርአያ ተስፋማርያም(ወይም በብዕር ስሙ "ኢየሩሳሌም አርአያ") የሚቀርበው "ከህወሃት መንደር የቃረምኩት" አምድ የህወሃትን ለ2 መሰንጠቅን ጨምሮ በርካታ ከባባድ ምስጢሮችን ለህዝብ አውጥቷል፡፡ ይህንን ተከትሎ የአምዱ አዘጋጅ ከባባድ ድብደባዎችን አስተናግዶ ህይወቱን ከአረመኔዎች ለማትረፍ ከሀገር ሸሸ፡፡ የኢትኦጵ ወርሃዊ መጽሄትም ተወዳጅ እንደነበር ይታወቃል፡፡

በምርጫ 97 ወቅት ፕሬሱ ቁልፍ ሚና ተጫውቷል፡፡ ስለ ምርጫ 97 ስናስብ ቶሎ ወደ አዕምሯችን ከሚመጡ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነጻው ፕሬስ ነው፡፡ ጋዜጦች በየዕለቱ ወደ አደባባይ ይጎርፋሉ፡፡ ህዝብ ግብር እየከፈለ ከሚያስተዳድራቸው ሚዲያዎች መረጃን ስለማያገኝ እነዚህ የግል ፕሬሶች አማራጭ ሀሳብ የሚገኝባቸው እስትንፋሶች በመሆን አገልግለዋል፡ ፡
በተለይ ምርጫው ሲቃረብ እነዚህ የፕሬስ ውጤቶች የሚሰሯቸው መረጃዎች፣ ትንታኔዎችና ቃለ መጠይቆች በመራጩ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ነበራቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ህዝቡ እነዚህን ጋዜጦችና መጽሄቶች መሸመት የማለዳ ተግባሩ አድርጎ አዘውትሯቸዋል፡፡
ከምርጫው መጭበርበርና መዘረፍ በኋላም የመንግስት ሚዲያዎች የለየለት የኢህአዴግ ካድሬ ሆነው ቋቅ የሚል፣ ሚዛናዊነትን የተጠየፈ፣ከጋዜጠኝነት መርህ በተቃራኒ የቆመ ዘገባን ሲያቀርቡ ህዝቡ በውጭ ሀገር ከሚተላለፉ እንደ ጀርመንና የአሜሪካን ድምጽ ሬዲዮዎች ጎን ለጎን በዋነኝነት ፊቱን ወደ ነጻው ፕሬስ ነበር ያዞረው፡፡
በምርጫ 97 ወቅት በዝረራ የተሸነፈው ህወሃት/ኢህአዴግ በምርጫው የደረሰበትን ሽንፈት ተከትሎ በጥቅምት 22/1998 የቅንጅት መሪዎችን በቁጥጥር ስር ሲያውል የነዚህን የፕሬስ ውጤቶች ቁልፍ ሚና በመረዳቱ ወዲያውኑ የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች ላይም የእስር ትዕዛዝ አውጥቶ ወደ ወህኒ ማጋዙን ጀመረ፡፡ የእስር ማዘዣውና ክሱ ከሀገር ውጪ ያሉ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጋዜጠኞችና ሌሎች የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞችንም ያካተተ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጠኞች ማህበር(ኢነጋማ) ፕሬዝዳንት የነበሩት አቶ ክፍሌ ሙላትም ለስብሰባ ኡጋንዳ በሄዱበት ጥገኝነት ጠይቀው ቀርተው ዛሬ ኑሯቸውን በአሜሪካን ሀገር በሂዩስተን፣ቴክሳስ ግዛት አድርገዋል፡፡
የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞችም ለ2 አመታት በእስርና ስቃይ ከተንገላቱ በኋላ በኢትዮጵያ ሚሊንየም ዋዜማ በፍርድ ቤት ተከራክረውና አሸንፈው ነጻ ወጡ፡፡

ኢህአዴግ "ስህተቱ"ን አሻሽሎ ነጻ ፕሬሱን ደፈጠጠው፡፡ የፕሬሱን ህግ ተጠቅሞ የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞችን ከማሸማቀቅ፣ ከማሰርና፣ ከማሰቃየትና ከፍተኛ ብር ከመቅጣት ከፍ ብሎ የብሮድካስት ባለስልጣንን ተጠቅሞ የፖለቲካ

➔

➔ ጽሁፎችን የሚያዘጋጁ ፕሬሶችን ፍቃድ ላለመስጠት ማጉላላትና ግልጽ እገዳ ማድረግ ጀመረ፡፡

እስክንድር ነጋና ሲሳይ አጌና ከሚሊንየሙ በኋላ ወደ ቀድሞ የጋዜጣ ሙያቸው ፍቃድ አውጥተው ለመንቀሳቀስ ያደረጉት ጥረት ስኬታማ አልነበረም፡፡ ፍቃድ ሰጪው ፈላጭ ቆራጩ የብሮድካስት ባለስልጣን ጋዜጠኞቹን ለወራት ያህል ካመላለሳቸው በኋላ በቀድሞው የኢትዮጵያ መሪ መለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ፈጽሞ የጋዜጣ ፍቃድ እንደማይሰጣቸው አረዳቸው፡፡

ፍቃድ ባይሰጣቸውም በጣት የሚቆጠሩ ጽሁፎችን በቀድሞዋ ተወዳጅ ጋዜጣ አዲስ ነገር ላይ አስነብበውናል፡፡ ይህንን ተከትሎም ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና ወደሎስ አንጀለስ፣ ካሊፎርኒያ አምርቶ ዓለም ዓቀፉን የPen ሽልማት ተሸለመ፡፡ ሀገሩን ከርቀት ሆኖ በፕሬሱ ለማገልገል ወስኖም ኢሳትን ተቀላቀለ፡፡

የ2ቱን ተወዳጅ የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች ለምሳሌ ያህል አነሳን እንጂ በርካታ የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች በሚሊንየሙ ዋዜማ የፖለቲካ ጽሁፎችን ማዘጋጀትና ማሳተም ከባድ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ የግዮን መጽሄት ማኔጂንግ ዳይሬክተር የሆነው አቶ ፍቃዱ ማ/ወርቅ ሁኔታውን ሲያስታውስ እንዲህ ይላል፡- “ከሚሊንየሙ በኋላ በነበሩት አመታት የጋዜጣ ፍቃድን በተለይ በፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ማውጣት ከባድ ነበር፡፡ በማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚዘጋጅ ብለን ከአድካሚ ልፋት በኋላ የምናገኘውን የጋዜጣ ፍቃድ ወደፖለቲካ እናዞረዋለን” በማለት ይጠቀሙበት የነበረውን አስቸጋሪ መንገድ ያስታውሳል፡፡

የጠቅላይ ሚንስትር ዶ/ር አብይ አህመድን ወደ ስልጣን መምጣት ተከትሎ የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች ከወህኒ ቤት መፈታት ጀመሩ፡፡ መንግስት በኢትዮጵያ እንዳይሰሩ ያገዳቸው በነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች የሚጻፍባቸው ከ200 በላይ ድረገጾችም ከአመታት እስር ተፈቱ፡፡ የተለያዩ የነጻው ፕሬስ ህትመቶችም ወደ አደባባይ ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡

የጋዜጣና መጽሄት ፍቃድም ያለምንም ማጉላላት ወዲያውኑ መሰጠት ተጀምሮ በአንጻራዊ ሁኔታ ፕሬሱ ላይ የተወሰነ ማበረታቻ ማሳየት ተጀመረ፡፡ ይሁንና ፕሬሱ እንዳይራመድ እግሩን የሸበበ ው ማነቆ ግን ዛሬም አልተፈታም፡፡ ይኸውም ነጻው ፕሬስ በእግሩ እንዲቆም ትልቁን ማስታ ወቂያ የሚሰጠው መንግስት ማስታወቂያ በመስጠትም ሆነ ሌሎች የግል ድርጅቶች ምርትና አገልግሎታቸውን በነጻው ፕሬስ ላይ እንዲያስተዋውቁ ሲያበረታታ አልታየም፡፡ ሌላው ደግሞ ሁሌም የሚነሳው የፕሬሱ ማነቆ የሆነው በየትኛውም ዓለም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ወረቀት ላይ የተጣለውን ግብር ለማንሳት መንግስት ፍላጎት አለማሳየቱ ነው፡፡ ቀጥተኛ እንቅፋቶችን በተወሰነ መልኩ የቀረፈው መንግስት ተዘዋዋሪ ማነቆዎችን ለማንሳት ግን ፍቃደኛ አልሆነም፡፡

ከምንጊዜውም በበለጠ መንግስት በነጻው ፕሬስ ላይ የሚያራምደው አቋም የሚፈተነው በምርጫ ወቅት ነውና መንግስት ዛሬ ላይ ካለፈው ስህተቱ ተምሮ የተለየ አቋም የሚራመድበትን ምህዳር ለማስፋት ትከሻውን ሰፊ አድርጎ ሜዳውን በመፍቀድ ሚናውን መጫወት ይገባዋል በማለት የዛሬውን ጽሁፌን አጠቃልላለሁ፡፡



ብሩክ አስቻለው

# ሰሚ ያጣ ጩኸት

በአንድ መንገድ ላይ ፊትና ኋላ ሆነው በቅርብ ርቀት ከሚጓዙ መንገደኞች መካከል ቀደም ብሎ የሄደውን መንገደኛ ዘራፊዎች ይዘው ንብረቱን ቀምተው እሱንም ሲደበድቡት የተመለከተው ኋለኛ፤ ከተደበደበው የበለጠ እሪታውን አቀለጠው፡፡ ምነው ምን ገጠመህ? ብለው ሌሎች ሰዎች ሲጠይቁት ያንን ሰው ደበደቡት አላቸው፤ ሰዎቹም በመገረም ታዲያ አንተ ምንህ ተነካ፣ ተደብዳቢው እንኳ እንዳንተ አላለቀሰም ሲሉት እኔም የምሄደው በዚያ መንገድ ነው፤ እሱ ላይ የደረሰበት እኔንም አያጣኝም ብዬ ነው የማለቅሰው አላቸው ይባላል፡፡

መንገደኛው ከተደበደበው የበለጠ ያለቀሰው መንገዱ ያ ብቻ ስለሆነ ይመስላል፤ ሌላ አማራጭ ቢኖረው እግሬ አውጭኝ ብሎ አማራጩን መጠቀም ይችል ነበር ብለን መውሰድ እንችላለን፡፡ በዚህ ምሳሌ መነሻነት ለመጠቃቀስ የምሞክረው ፍሬ ሀሳብ እንደሚከተለው ነው፡፡

ሐገራችን ኢትዮጵያና ህዝቦቿ መንገደኞች ናቸው፡፡ ሁሉንም ነገር ከሚያሳጣው የድህነት ማቅ ለመላቀቅ የሚኳትኑ ዜጎች እንዳሏት ሁሉ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አይነት አካሄድን በመከተል በከፊሉ የሀገራችን ክፍል ሁሉ በሚባል ደረጃ አገርን የሚያተራምሱና በየዕለቱ የምንሰማውን አሰቃቂ የሞት ዜና የሚያደራጁት፣ የሚያስፈፅሙት ከእኛው ጉያ የተገኙ፣ ከኢትዮጵያ ቀዬ የተፈጠሩ እንጂ አገር አቋርጠው የመጡ ወራሪዎች አይደሉም፡፡ ክልብ የሚያሳዝነውና ሐዘናችንን ድርብ የሚያደርገው ደግሞ ይህ ነው፡፡

መቼም ይህ ለምን ሆነ የሚል ትንታኔ ለኢትዮጵያ ህዝብ ለመግለፅ መሞከር ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል፤ በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች፣ በህትመት ውጤቶች፣ በብዙ መድረኮች እና በበሳል አክቲቪስቶች በተደጋጋሚ የተገለፀው ህገ መንግስታዊ ማዕቀፍ ያለው የብሔር፣ የጎሳ፣ የቋንቋ ፖለቲካና አደረጃጀት አሁን ለምናየው ዘርፈ ብዙ ችግር መንስኤ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነውና በዚህ ላይ ብዙ አልልም፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሚያሳዝነው እና የሚያስጨንቀው ጉዳይ ግን እዚህ ግባ የሚባል በመፍትሔው ላይ የተሰራ ስራ አለመኖሩ ነው፡፡ በዚህ አንድ አመት ብቻ ያየነውን መፈናቀልና የሰማነውን የሞት ዜና ከነአይነቱ እዚያው እዚያው ላይ እየተደራረበ አዚም እንደተደረገበት ሆነን ተላምደነዋል፡፡ ለምን የንፁሐን ደም ጩኸት ሰሚ አጣ? ለምንድን ነው ሚዛን የሚያነሳ ስራ መስራት ያቃተን? መንግስት ምንድን ነው የቸገረው? አሁን አሁንማ ከደረሰው ጉዳት ይልቅ ስለ ጉዳቱ በተዘገበው ዜና የሚሰቀቅ አመራር እየተመለከትን ነው፡፡

ጠንካራ የደህንነት አፈፃፀም አለው የሚባልለት “ኢህአዴግ” መቸም ቋቱ አልነጠፈም! ቀድሞ የመከላከል የህዝቡን ደህንነት የመጠበቅ ስራው የት መከነበት፡፡ መንግስት ጓዳውን ይፈትሽ፤ ህዝቡ የጥፋትና የሞት ስርየትን ዜና መስማት ነው የናፈቀው፤ የጥፋትና የሞት ዜና ሪፖርትን መስማት አሰቅቆታል፡፡ ማንም ሰው የሚወለድበትን ብሔር አልመረጠም፤ ነገር ግን በብሔሩ ምክንያት ብቻ በስነ ልቦና ጫና ውስጥ እየወደቀ ነው ያለው፡፡

በዚህ አክባቢ ለመግለፅ በሚዘገንን፣ በእንዲህ ዓይነት አገዳደል ተገድሎ፣ በዚያ ደግሞ እንዲህ ሆኖ… የሚሉትንና ነገ ደግሞ ምን እናይ ምን እንሰማ ይሆን? የሚሉት ሀሳቦች ስነልቦናዊ ጫና ሊያመጡ የቻሉት መንግስት ህገ መንግስትን ከማሻሻል ጀምሮ በመፍትሔዎቹ ላይ አለመትጋቱና ንፁሐንን በመቅጠፍ እኩይ ተግባር ለተሰማሩ አካላት ለጥፋታቸው ፍጥነትን እንዲጨምሩ እድል ስለከፈተላቸው ነው፡፡

ይህችን ትንሽ መጣጥፍ ልከትብ ስነሳ በተደጋጋሚ ወደ ህሊናዬ እየተመላለሰ የረበሸኝ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጓቿን በዘር ማጥፋት ያጣችው ሩዋንዳ ድርጊቱ በገሃድ ከመፈፀሙ በፊት ወይም ዋዜማው አከባቢ እኛ አገር ላይ አሁን እያየነው ያለውን አይነት መጎነታተል ይታይ እንደነበረ ሳስብ ነው፡፡ በእውነት ከልብ ያሳዝናል እንዲህ አይነት ምሳሌን አንስቶ እንደ ትምህርት ለመጥቀስ ብቻ ብለን አስበን እንኳ ሟርት እንዳይሆንብን ብንመኝም፣ ብንፈልግም፣ ለመፃፍ ቢከብድም፣ ህልም ተፈርቶ እንቅልፍ ሳይተኛ አይታደርም እንዲሉ ልንወያይበት ግድ ይለናል፡፡ እኛ ከእነርሱ የተሻለ ሁሉንም ነገር መልክ ልናስይዝ፣ ልንመክርበት፣ ልንዘክርበት፣ ልንወስንበት የምንችላቸው ብዙ ብዙ አማራጮች አሉንና ጨለምተኛ አይደለንም፡፡ ህገ መንግስትም ሆነ የብሔር አቀንቃኝነት መሻሻል ባለበት ደረጃ እና ልክ እንዲደርስና ለመገንባት ጊዜው ቢርቅብንም አልመሸምና ሰሚ ያጣ ጩኸት እየበዛባት ያለችውን ሐገራችንን ጆሮ ዳባ ልበስ የሚል ምላሽ አንስጣት፡፤

በመነሻዬ ላይ ያነሳሁት መንገደኛ “እኔ የምሄደው በዚያ መንገድ ነው” ብሎ እንደጮኸው ሁሉ እኛም በጎረቤት አገሮቻችን መንገድ ተጉዘን ፍፃሜያችን እነሱ የገጠማቸው እንዳይሆን፤ መንግስት ሰሚ ያጣውን ጩኸት ጆሮ እንዲሰጠውና ለመፍትሔውም በአፋጣኝ ሊተጋ ይገባል፡፡ ከዚህ የሚቀድም ምንም ስራ የለም፡፡ ህዝብ ያለ ሀገር፤ ሐገርም ያለ ህዝብ ሊኖር አይችልም፡፡ ፏሪ አልባ ጎጆዎች መጨረሻቸው ወና መሆን ነው፤ ከዚህ ደግሞ ማንም ምንም አያተርፍም፤ ሁሉም ከሳሪ ነው የሚሆነው፡፡ እናም ‹‹ሳይቃጠል በቅጠል›› ብለን በጊዜ መንገዱን እናስተካክል፤ ችግርን ማወቅ የመፍትሔው ግማሽ አካል ነውና፡፡



አርአያ ተስፋማርያም
(እየሩሳሌም አርአያ)

# አመጣጣችን ለዶ/ር ነጋሶ ምስጋና ለማቅረብ ነበር

ከዋሽንግተን ዲሲ ተነስተን 13 ሰዓት ከፈጀ በረራ በኋላ አዲስ አበባ ቦሌ ደረስን። የ11 ዓመት ናፍቆት ስላለ እንቅልፍ የሚባል በአይኔ ሳይዞር ነበር የደረስነው። በቀጥታ ያመራሁት ወደ ወላጆቼ መኖሪያ ነበር። በስደት እያለሁ የወላጅ እናቴንና ታላቅ ወንድሜን መርዶ በአንድ ቀን ነበር የሰማሁት። ሀዘኔ በእንባ ታጥቦ የሚወጣ ባይሆንም አለቀስኩ። አስከሬናቸው ወዳረፈበት ቤ/ክ አመራሁ። የእናቴ ሃውልት የለም። የሚመለከተውን የቀብር አስፈፃሚ ስጠይቅ ‹‹በስህተት ነው የፈረሰው›› አለኝ፤ በኡኡታና ጩኸት የታጀበ የምሬት እንባ አፈሰስኩ። ያልታመመ እግር የቆረጠና በመርፌ የሰው ህይወት የቀጠፈ ሀኪም ‹‹በስህተት ነው›› ይልሃል። ንፁሃንን በጥይት የገደለ አካል ‹‹በስህተት›› እንደሆነ ይደሰኩራል። ሁሉም ቦታ ‹‹ስህተት›› የሚል የለበጣ ቃል መስጠት የተለመደ ሆኗል። የተጎጂው ቤተሰብ የሚደርስበት የልብ ስብራትና ተደራራቢ ሃዘን በቃላት የሚገለፅ አይደለም! የደረሰበት ብቻ ነው የሚያውቀው!...

በዚህ የሃዘን ጉዳት ውስጥ ሆኜ በማግስቱ ጠዋት ለክቡር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ስልክ ደወልኩ፡ ፡ ማንነቴን ገልጬ ከልጄ ኢየሩሳሌም ጋር አገር ቤት መግባታችንን ነገርኳቸው፤ በተለመደ ፈገግታ ተሞልተው ‹‹እንኳን ደህና መጣችሁ አቶ አርአያ! ኢየሩስና አንተም ለአገራችሁ በመብቃታችሁ፣ ወገናችሁን ለማየት በመብቃታችሁ እንኳን ደስ አላችሁ!›› አሉኝ ከልብ በመነጨ የደስታ ቃል፤ እኔም ቀበል አድርጌ ‹‹ ዶ/ር ነገ ልናገኝዎት እንፈልጋለን። ኢየሩስና እና እኔ በጣም ጓጉተናል!›› አልኳቸው። ‹‹እስከ ማክሰኞ አይመቸኝም፤ ማክሰኞ ደውልልኝና የሚሆነውን እንነጋገራለን›› አሉ ዶ/ር ነጋሶ። በእኔና ልጄ ለነበረው ጉጉት የዶክተር ምላሽ በአምስት ቀናት ቀጠሮ መራዘሙ ቅር አሰኝቶናል።

ምክንያቱም ከልጄ ጋር አገር ቤት የመጣንበት ዋናው ጉዳይ ክቡር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ለልጄ ኢየሩሳሌም ለዋሉት ትልቅ ሰብዓዊ ተግባር ምስጋና ለማቅረብ ነው። ጊዜው 1998 ዓ.ም ነበር፤ ታዳጊዋ ኢየሩሳሌም አርአያ በጀርባ አጥንቷ ላይ በተፈጠረው ስኮሎይሲስ የተባለ ከባድ ችግር ምክንያት ከፍተኛ ህክምና በውጭ አገር ማድረግ እንዳለባት የጥቁር አንበሳ የሀኪሞች ፍርድ በሰጠው ደብዳቤ አሳወቀ። ሕክምናውን ካላደረገች ግን ከጥቂት ዓመት በኋላ የአልጋ ቁራኛ (ፓራላይዝድ) እንደምትሆን ያናገርኳቸው ዶክተሮች ገለፁልኝ። ይህን ከሰማሁ ቀን ጀምሮ እንቅልፍና መረጋጋት አጣሁ። ሰው ሳትሆን



**የቀድሞው ፕ/ት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እና እየሩሶሌም አርአያ**

ሰው መፍጠር የእዳዎች ሁሉ ከባድ እዳና ፈተና ነው! የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር የወቅቱ ፕ/ት አቶ ሽመልስ አዱኛ ለተለያዩ ምግባረ ሰናይ ተቋማት የሚሰጥና ‹‹ታዳጊ ኢየሩሳሌምን ተባበሩልን›› የሚል ይዘት ያለው የድጋፍ ደብዳቤ ከሀኪሞች ቦርድ ደብዳቤ ጋር፤ እንዲሁም አቶ ገነነ አሰፋ በሚያሳዝንና በጥሩ አገላለፅ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የፃፉትን አንድ ላይ አያይዤና በመቶዎች በሚቆጠር ኮፒ አባዝቼ በከተማችን ለሚገኙ የውጭ አገራት ምግባረ ሰናይ ተቋመት እየዞርኩ ሰጠሁ።

አንዳንዶቹ በሁኔታው እንዳዘኑ፣ ነገር ግን መርዳት እንደማይችሉ ሲገልፁ፤ አብዛኞቹ ምንም ዓይነት ምላሽ ሳይሰጡ ረጅም ወራት ተቆጠረ። ስማቸውን መግለፅ የማልፈልገው አንድ የነጋዴዎች ፐ/ት እና ባለሀብት ጋር አምርቼ ማስረጃዎቹን አቅርቤ አወራን። በጋዜጣ ላይ ስፅፍ ስለነበረው ስነግራቸው ይበልጥ አወቁኝ። ከማንኛውም አገር ሆስፒታል የህክምና ፕሮፖዛል ጠይቂ እንዳመጣና አስፈላጊውን የህክምና ወጪ እንዲሁም የትራንስፖርት እንደሚሸፍኑ ቃል ገብተውልኝ ወጣሁ። ዶ/ር አከዛ በሚባል ሰው አማካይነት አሜሪካ ከሚገኝ ሆስፒታል ለሕክምና የሚያስፈልገውን ገንዘብ የሚገልፅ ደብዳቤ ተላከልኝ። ከእርሳቸው ጋር ይህንን መረጃ ስንለዋወጥ ሰባት ወራት ነበር የፈጀው። ደብዳቤውን ይዤ ቃል ወደገቡልኝና ከላይ የጠቀስኳቸው ታዋቂ ባለሀብት ቢሮ ሄድኩ። ውስጤ በደስታ፣ በምኞትና በፀሎት ተሞልቶ ነበር የደረስኩት። ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ‹‹የትራንስፖርት ወጪዋን ብቻ ነው የምሸፍነው የሕክምና ወጪውን አልችልም›› ሲሉ ቃላቸውን አጥፈው ጠበቁኝ። መላ አካሌ በረዶ የፈሰሰበት ይመስል በድን የሆነ መሰለኝ። ቃል ሳልተነፍስ ቢሮውን ለቅቄ ወጣሁ።

ጥቂት ቀናት በሀሳብ ስባዝን፣ ስብሰለሰል ከቆየሁ በኋላ አንድ ሀሳብ ብልጭ አለልኝ፡ ፡ ሐምሌ 1999 ዓ.ም ነበር፤ የክቡር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ስልክ አፈላልጌ አገኘሁ። ደወልኩላቸውና በኢትኦጵ ጋዜጣ ላይ በልጄ ስም የምፅፍ ጋዜጠኛ መሆኔን በመግለፅ ማንነቴን አሳወቅኳቸው። ረጋ ባለ አንደበት ‹‹ከአመታት በፊት ድብደባ ተፈፅሞብህ እንደነበረ ሰምቻለሁ፤ ከጋዜጦችም አንብቤያለሁ። አሁን ደህና ነህ፣ ጤናህ እንዴት ነው? አሉኝ በሀዘን አይነት ስሜት፤ ደህና መሆኔን ገለፅኩላቸውና ለአንድ ጉዳይ ላነጋግራቸው እንደምፈልግ ነገርኳቸው። በወቅቱ የነበረው የመለስ ዜናዊ አስተዳደር የደህንነት ቢሮ ዶ/ር ነጋሶን ጨምሮ ከኢህአዴግ በወጡ የፖለቲካ አመራሮች ላይ የስልክ ጠለፋና የእለት ተእለት ክትትል እንደሚያደርግ በሚገባ ይታወቅ ስለነበረ ነው በአካል ማግኘትን የፈለግኩት።

ዶ/ር ነጋሶ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ቅንነት በተቀላቀለበት መልኩ ሲመልሱ ‹‹በዚህ ሳምንት አልችልም። ከነገ ሰኞ ጀምሮ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቀጠሮ አለብኝ፡ ፡ ከመኖሪያ ቤቴ ውጣ እየተባልኩ ነው። አንዱ ችሎት መውጣት የለበትም ሲል ሌላው ደግሞ ውጣ ይላል። እኔም ከሳሼ የመንግስት ወኪል ዓቃቤ ህግም በየፊናችን ይግባኝ እያልን እንገኛለን፡ ፡ የጡረታ መብቴን ስለተከለከልኩ በዚህም ጉዳይ ሰበር ሰሚ ደርሻለሁ። በነዚህ የተደራረቡ ቀጠሮዎች ምክንያት እስከ አርብ አልችልም፡ ፡ ቅዳሜ ወይም እሁድ ደውልና አመቻችቼ ለመገናኘት እሞክራለሁ›› ካሉ በኋላ አያያዙና ‹‹ግን ለምንና በምን ጉዳይ ነው እንድንገናኝ የፈለግከው አስቸኳይ ነው?›› አሉኝ በትህትና።

በውስጤ ለምን በስልክ አልግራቸውም የፖለቲካ ጉዳይ አይደለም፤ ደህንነቶች ቢሰሙትም የራሳቸው ደንታ ነው አልኩ። አዎ አስቸኳይ ነው ስላቸው ቀበል አድርገው ‹‹ንገረኝ ልስማው›› አሉ ‹‹ክቡር ዶ/ር .... ›› ብዬ ስጀምር አቋረጡኝና ‹‹ቅድም ነግሬህ ነበር። ዶክተር ብቻ በለኝ›› አሉኝ በትህትና። ‹‹እሺ ዶ/ር ልጄ ኢየሩሳሌም አሁን ዘጠኝ አመቷ ነው›› ስል የተጋረጠባትን ከባድ አደጋ እንባ እየተናነቀኝ በዝርዝር አስረዳኃቸው፡ ፡ በጥሞና ካደመጡኝ በኋላ ‹‹ውይይ .... ልጄን! ምን አይነት አሳዛኝ ነገር ነው የነገርከኝ!.... እ ምን እንዳደርግላት ነው የፈለከው?›› ሲሉ በሃዘን ተውጠው ጠየቁኝ። ‹‹ለሚያውቋቸው ኤምባሲዎችና ድርጅቶች እንዲጠይቁልኝ ነው›› አልኳቸው።

ዶ/ር ነጋሶ ‹‹ በጣም ጥሩ! የሕክምና ማስረጃዎችንና ጠቅላላ ደብዳቤዎቹን አባዝተህ በፖስታ ከተህ ነገ ጠዋት አበበ ለሚባል የቤቴ ጥበቃ ሰራተኛ ➔

ስጠው፡፡ ይሄማ ነገ ዛሬ የማይባል አስቸኳይ ጉዳይ ነው! ›› አሉኝ፡፡

ዶ/ር ነጋሶ ፖስታዎቹን ለጣሊያን፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመንና ሕንድ ኤምባሲ አምባሰደሮች እየዞሩ ሰጡ፡፡ በጣም የሚገርመው በራሳቸው ወጪ ለታክሲ እየከፈሉ ነበር በየኤምባሲው ያደረሱት፡፡ የወቅቱ የጀርመን ኤምባሲ አምባሳደር ሚ/ር ፋረን ሆልዝ ‹‹በአንተ የመጣ ጉዳይ እኔ ነው የምይዘው›› በማለት በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ምላሽ ሰጡ፡፡ ‹‹ጀርመን ሮተሪ ክለብ ›› የተባለ ግብረ ሰናይ ተቋም የ10ሺ.ህ ዶላር እርዳታ ለገሰ፡፡ ዶ/ር ነጋሶ በደስታ ተሞልተው ዜናውን በስልክ አበሰሩኝ፡፡ ጀርመን አገር ሔዳ እንድትታከም ዶ/ር ነጋሶ የጀርመን ኤምባሲ አምባሳደርን አነጋገሩ፡፡ አምባሳደሩ ፍቃደኛ ሆነው በጀርመን አገር የሚገኙ ሆስፒታሎችን የዋጋ ዝርዝር ጠየቁ፡፡ ከ20 ሺ.ህ ዶላር በታች ማግኘት ሳይቻል ቀረ፡፡

ዶ/ር ነጋሶ የህንድ ኤምባሲ አምባሳደርን አነጋረው አምባሰደሩም ኒውደልሒ የሚገኝ አፓሎ ሆስፒታልን ዋጋ በማስቀነስ በ10ሺ.ህ ዶላር እንድትታከም ከስምምነት ተደረሰ፡ ፡ ይህ ፕሮሰስ ረጅም ወራትን የፈጀ ነበር፡ ፡ ዶ/ር ነጋሶ በተዳራራቢ ጉዳይ አጣብቂኝ ውስጥ ገብተው እያለ ነበር ያልተቋረጠ ጥረት ያደርጉ የነበረው፡፡ ለስድስት ወራት በስልክ እንጂ በአካል አልተገናኘንም ነበር፡፡ በድንገት አራት ኪሎ በእግራቸው ሲጓዙ ከዶ/ር ነጋሶ ጋር ተገናኘን፡፡ ሰላምታ አስቀድሜ ማንነቴን ነገርኳቸው፡፡ ተቃቅፈን ከተሳሳምን በኋላ ሳር ቤት አከባቢ የሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ተገናኝተን እንድናወራ ቀጠሮ ሰጡኝ፡ የሳሎኑ ጣሪያ (በሲሚንቶ የተገነባ) ተሰንጥቆ የዝናብ ውሃ ያስገባል፡፡ ላስቲክ ላይ ድንጋይ ተጭኖ ቢከለልም የክረምት ዝናብ ከመግባት እንደማያግደው ዶ/ር ነጋሶ በተከፋ ስሜት ተውጠው ነገሩኝ፡፡ በሳሎኑ ግርጌ የሁለት ወጣት አይነስውራን ፎቶ ተሰቅሏል፡፡ ‹‹ማናቸው›› ስል ጠየኳቸው፡ ፡ ‹‹ያሳደኳቸው እና የማግዛቸው ወጣቶች ናቸው፡፡ ዩኒቨርስቲ ገብተዋል፡፡ የማገኛትን ጡረታ ለእነሱ ነበር የማከፋፍለው፡፡ እነ መለስ ጡረታዬን በማገዳቸው ወጣቶቹ ለችግር ተዳርገዋል›› አሉና በሀዘን ዝም አሉ፡ ፡ ሕወሓት መራሹ የመለስ ዜናዊ አመራር በዶ/ር ነጋሶ ላይ የፈፀመው የግፍ ግፍ እጅግ የሚያሳዝን ነው!.... በተለያዩ ቀናት ጎራ እያልኩ መጠየቄን ቀጠልኩ፡፡

አንድ ቀን ከመኖሪያቸው ወጣ ብለን በእግራችን እየተጓዝን ሳለ በሳር ቤት አካባቢ የተገነቡ የቱባ ባለስልጣናት ዘመናዊና ውድ ቪላዎች የባለስልጣናቱን ስምና የተገነቡበትን አመት እየጠቀሱ ነገሩኝ፡፡ ከ35ሺ.ህ እስከ 45 ሺ.ህ ብር በወር እንደሚከራዩም ገለፁልኝ፡ ፡ ዶ/ር ነጋሶ አያይዘውም 92 — 93 ዓ.ም አቶ መለስ ‹‹ሙስና ሙስና የሚል አጀንዳ ከፍቶ ነበር፡፡ ሸራተን ሆቴል አንድ ዝግጅት ላይ ከአቶ መለስ ጋር ጎን ለጎን ተቀምጠን እያለ እንዲህ አልኩት፡፡ ‹ስለሙስና አጀንዳ ከፍተሃል፡፡ ኢህአዴግ ወደ ስልጣን በመጣ በጥቂት አመታት እስከ 10 ሚሊዮን በሚደርስ ገንዘብ ቪላ ገንብተው ስለሚያከራዩት ባለስልጣናት ... አቶ .... (ሁለት የኦህዴድ ሶስት የሕወሓት ጀነራሎች ስም ጠቅሰው) ከየት አምጥተው እንደገነቡ አጣርተሃል? በደመወዛቸው ወይም ከባንክ ተበድረው አይደለም የገነቡት፡፡ ሙስና ካልክ ከነዚህ መጀመር የለብህም›› ብዬ ስጠይቀው በቁጣ አይነት ተመናጭቆ እጄን እያወራጨ ‹‹እነሱን ስከታተል አልውልም፡፡ ኮሚሽን አቋቁሜ እነሱን ስከታተል አልውልም›› ሲለኝ ‹‹ታዲያ ስለምን ሙስና ነው የምትናገረው? የከፈትከውን የሙስና አጀንዳ ማቆም አለብህ›› አልኩት፡፡ ከክፍፍሉ በኋላ የሙስና አጀንዳው አላማ ምን እንደሆነ በአደባባይ ታየ፡፡ እኔ መሬት በነፃ እንድወስድ ሲጠይቁኝ እነሱ ለሚፈፅሙት የሙስናና ውንብድና እንደማፍር ገልጩ በጭራሽ እንደማላስበው ነገርኳቸው›› ብለው ዶ/ር ነጋሶ አጫወቱኝ፡፡

ረቡዕ ሐምሌ 2 ቀን 2000 ዓ.ም ወደ ሕንድ ክልጆ ጋር የምንጓዝበት ቀን ነበር፡፡ ከቀኑ 10 ሰዓት ከኢየሩስና ከወዳጄ ጆኒ ጋር ዶ/ር ነጋሶን ለመሰናበት ሔድን፡፡ ኢየሩስን አቅፈው እየሳሙ ‹‹ሁሉም ነገር በፈጣሪ እገዛ ይሳካልሻል፤ ጤናሽ ተስተካክሎ የምታስቢው ደረጃ አምላክ እንዲያበቃሽ እመኛለሁ!›› አሉ፡፡ ተሰናብተን ከመውጣታችን በፊት ሶፋ ላይ ወደተቀመጡት ዶ/ር ናጋሶ ተራምጄ ተንበረከኩና ጉልበታቸውን ታቅፌ በየተራ እየሳምኩ ሳግና እንባ እየተናነቀኝ አመሰገንኳቸው! ‹‹ይህ እኮ ግዴታችን ነው! የእኛ ነገር ሆኖ አለመታደል እንጂ!›› አሉ፡፡ .... የአየር ነፃ ትኬት የተባበረን የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተለይ አቶ ግርማ ዋቄና አቶ ተወልደ ገ/ማርያምን በዚህ አጋጣሚ ልናመሰግን እንወዳለን፡፡

በኒውደልሒ 18 ሰዓት የፈጀ የቀዶ ሕክምና ያደረገችው ታዳጊ ኢየሩሳሌም የአልጋ ቁራኛ ከመሆን ዳነች፡፡ ጨልሞ የነበረው ሕይወቷን ብርሃን እንዲፈነጥቅበት ያደረጉት፣ ዳግመኛ የወለዷትና ነፍስ የዘሩባት ክቡር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ወደ ሕንድ ስልክ እየደወሉ ጤንነቷን ይጠይቁኝ ነበር፡፡ የደግነታቸውን ጥግ የምንገልፅበት ቃል የለንም!

ከስድስት ወር በኋላ ሁለተኛውን ቀዶ ሕክምና ካደረገች በኋላ በህንድ ቆይተን በዛው አሜሪካ እንድንገባ ኤምባሲው ፈቀደልን፡፡ ከቺካጎ እስከ ሜሪላንድ በነበራት የትምህርት ቆይታ በሁሉም የትምህርት ዓይነት ‹‹A›› በማምጣት የተለያዩ ሽልማቶችን ማግኘት ቀጠለች፡፡ በቀጣዩ አመት ‹‹በባዮ ኬሚካል ኢንጂነሪንግ›› በዲግሪ የምትመረቀው ኢየሩሳሌም አርአያ ጋር ከአሜሪካ የመጣንበትና ቀደም ሲል በመግቢያዩ እንደጠቆምኩት ዶ/ር ነጋሶን ለማመስገንና በሚቀጥለው አመት በኢየሩስ ምርቃት ፕሮግራም ላይ እንዲገኙልን የግብዣ ጥሪ ለማቅረብ ነበር፡፡

ማክሰኞ ጠዋት በታላቅ ወንድሜ ስልክ ዶ/ር ነጋሶ የላኩት የፅሁፍ መልዕክት ደረሰኝ፡፡ እንዲህ ይላል ‹Good Morning. Can you please tell Ato Araya that I apologise for not being able to meet him today. Thank you very much Dr Negaso ›› ... ሐሙስ ደወልኩና እንድናገኛቸው በልመና ጭምር ጠየኳቸው፡፡ ‹‹ቅዳሜ አማቶቼ አገር ለCheck up ስለምሄድ አይመቸኝም፡፡ ከሁለት ሳምንት በኋላ ስለምመለስ እንገናኛለን›› ሲሉኝ ‹‹እባክዎ ነገ ቤት እንምጣ›› ስል ተማፀንኳቸው፡ ፡ ፈገግ እያሉ ‹‹ነገ ጉዳዮቼን መጨረስ ስላለብኝ አይመቸኝም፡፡ ግዴለም ስመለስ እንገናኛለን›› አሉኝ፡ ፡ ቢከፋኝም እሺ ብዬ ተቀበልኩ፡፡ እኔም ልጄም ለምን እንደቸኮልንና እንደጓጓን አናውቅም፡፡ ደጉና የዋሁ መልካም ሰው ክቡር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እየሳቁ፤ ላናገኛቸው በሄዱበት ቀሩ፡፡ ሀዘናችንን መቋቋም ተሳነን! ጉጉታችን መንገድ በመቅረቱ ቁጭታችንን ያፈሰስነው እንባ አጥቦ ሲያወጣልን አልቻለም!...

ከአንድ አመት አራት ወር በፊት በማህበራዊ ድረ-ገፅ ያወጣሁት ፅሁፍ ነበር፡፡ በነጋሶ የለመለመች ህይወት በሚል ርዕሥ የልጄና የዶ/ር ነጋሶን ፎቶግራፍ ጎን ለጎን አድርጌ ለኢየሩስ የፈፀሙትን ትልቅ ሰብዓዊ ተግባር የሚያትት ፅሁፍ ነበር፡፡ በስልክ የማገኛቸው ዶ/ር ነጋሶ ‹‹ፌስ ቡክ ባይኖረኝም የፃፍከውን ሰዎች አንብበው ነገሩኝ›› አሉኝ፡፡ በዛ ሰሞን መኪና፣ የሕክምና ኢንሹራንስ የገንዘብ ድጋፍ ‹‹ ኦህዴድ ለዶ/ር ነጋሶ ፈቀደ›› የሚል ዜና ይነገር ስለነበረ ስለጉዳዩ ጠየቅኳቸው፤ ዶ/ር ነጋሶም ‹‹በፓርቲ ደረጃ አይደለም፡፡ ይህን እንዳገኝ ያደረገው ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ነው፡፡ በስልጣን ላይ እያለሁ ዐቢይ ወጣት ስለነበረ አላውቀውም፡፡ ደግመህ ደጋግመህ እንድታመሰግንልኝ (በፅሁፍ ማህበራዊ ገፅ ላይ) የምፈልገው ዶ/ር ዐቢይን ነው!›› አሉኝ፡ ፡ በወቅቱ ዶ/ር ዐቢይ የፓርቲው ፀሐፊ ነበሩ፡፡ የነጋሶ አሳዳጆች እነ ጌታቸው አሰፋና የሕወሓት አመራር ባለበት ዶ/ር ዐቢይ ደፍረው ዶ/ር ነጋሶ የተጠቀሰውን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረጋቸው ከፍ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል! የዶ/ር ነጋሶን ቃል አስተላልፌያለሁ!! በተጨማሪ ዶ/ር ነጋሶ እንዳሉትና በተለያየ ጊዜ እንደነገሩኝ ከመለስ ጎን ተሰልፈው ያዋከቡ፣ ያስጨንቁ (harassment) “መታሰር አለበት” ይሉ የነበሩና ቁልፍ ስልጣን ጨብጠው ባሉበት ሁኔታ ‹‹ኦህዴድ ነው ለነጋሶ ድጋፍ ያደረገው›› ተብሎ መሰሪዎቹን አብሮ ለምስጋና ማሰለፉ ለዶ/ር ነጋሶም ይሁን ጉዳዩን በቅርብ ለሚያውቀ የማይመስል ነገር ነው! በዶ/ር ነጋሶ የቀብር ስነ ስርዓት ፕሮግራም ላይ ሶስቱ የ ቀድሞ ቱባ የኦህዴድ ባለስልጣናት አልተገኙም፡፡

‹‹ዶ/ር ነጋሶ መታሰር አለበት›› ብለው የመለስ ተሃድሶ አቀንቃኝ ከነበሩት አንዱ ጄ/ል አለምሸት ደግፌ ሲሆኑ፤ በ1996 ዓ.ም ተፅዕተው ለዶ/ር ነጋሶና ለጄ/ል ታደሰ ጋውና ስልክ ደውለው ይቅርታ ጠይቀዋል፡፡ ጄ/ል አለምሸት በስልጣን እያሉ ላቀረቡት ይቅርታ ነጋሶ ከልባቸው ይቅር እንዳሉ ገልፀዋል፡፡ ነጋሶ ያስፈራሩኝና ወከባ ያደርሱብኝ ከነበሩት አባዱላና ጄ/ል ባጫ እንደሚገኙበት ነግረውኛል፡፡ ይቅርታ ሳይጠይቋቸው ነው ነጋሶ ያለፉት፡፡

በሚሊኒየም አዳራሽ በተከናወነው የክቡር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የአስከሬን ሽኝት ፕሮግራም ላይ የታዘብኩትን የዶ/ር ካሱ ኢላላን አሳፋሪ ድርጊት ሳልጠቅሰው አላልፍም፡፡ በቅርብ ከእኛ ትይዩ ተቀምጠው ለነበሩት ዶ/ር ካሱና ለታዳሚው የዶ/ር ነጋሶ የሕይወት ታሪክ የሚተርኩ ሁለት ብሩሸሮች ታድለው ነበር፡፡ ዶ/ር ካሱ ተቀብለው ሲያበቁ፤ እንድም ገፅ ሳይገልጡና ለማየት ሳይፈቅዱ የተቀመጡበት ወንበር ላይ ጥለውት ወጥተው ሔደዋል፡፡ በቀብር ስነ ስርዓቱም ላይ አልመጡም፡፡ የመለስ ዋና አቀንቃኝ በመሆን በነጋሶ ላይ መሰሪ ዘመቻ ከፍተው ከነበሩት አንዱ ዶ/ር ካሱ ባለፈው እሁድ የፈፀሙት አሳፋሪ ተግባር ያለፈ ማንነታቸውን ያስታወሰኝ ሲሆን፤ በስፍራው የነበሩትን ጭምር ያሳዘነ ነበር፡፡ ክቡር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን በእምባና መሪር ሀዘን ሸኘን! በምድር ፈፅመውት ያለፉት ቅዱስ ተግባር አምላክ ከደጋጎቹ ጋር በገነት እንደሚያሳርፋቸው ቅዱስ ፈቃዱ እንደሚሆን ሁሉ፤ ታሪክም ሲዘክራቸው ይኖራል!!

# የመንግስት ጋዜጠኞች ማህበር 50ኛ ዓመታቸውን አከበሩ

## የነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር አልባ ሆነዋል

የመንግስት ጋዜጠኞች ማህበር የተመሰረተበትን 50ኛ ዓመት የምስረታ የወርቅ ኢዮቤልዩ በዓል ምክንያት በማድረግ ለቀናት ሲያከናውን የቆየውን ልዩ ልዩ የበዓል አከባበር መርሃ ግብር ባለፈው ሚያዝያ 29 ቀን 2011 በስካይ ላይት ሆቴል ባካሄደው ፕሮግራም አጠናቋል።

የማህበሩ ፕሬዝዳንት የሆነው ጋዜጠኛ መሰረት አታላይ በዕለቱ መድረክ ባደረገው ንግግር በሀገሪቱ አንድ ወጥ የሆነ "የመንግስት፣ የግል" የማይባል የጋዜጠኛ ማህበር እውን ለማድረግ ከሚመለከታቸው ጋር ውይይት ተካሄዶ ወደ ስምምነት መቃረቡን ተናግሯል።

የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር ፕሬዝዳንት ናቸው ተብለው በዚሁ ፕሮግራም ንግግር እንዲያደርጉ የተጋበዙት አቶ ወንደሰን መኮንንም ውህደቱን ለመፈፀምና አንድ ጠንካራ የጋዜጠኞች ማህበር ለመመስረት በጋራ እንደሚሰሩ አረጋግጠዋል። የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር 50 ዓመት የምስረታ በዓል የማጠቃለያ ዝግጅት እንደ ዜና ሆኖ ሲቀርብ ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ጥቅል መልክ ያለው ሆኖ እናገኘዋለን። ቢሆንም ግን ይሄን ዜና እንደዜና አንብቦ የጨረሰ ማንም ሰው፤ በተለይም በዚህች መከረኛ ሀገር የዘመናዊ ግፍ ሰለባ ስለሆኑ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች የሚያውቅ የትኛውም ዜጋ ከዚህ ዜና በኂላ እጅግ በርካታ አስገራሚ፣ አሳዛኝና አስደንጋጭ እውነታዎችን አንስቶ ስለራሱም ከሌሎችም ጋር ሙግት መግጠሙ የሚጠበቅ እንደሆነ ይሰማኛል።

**በወያኔ ዘመን ሙያቸውን በተራ ጥቅም ለውጠው የገዛ ወንድሞቻቸው /የሙያ አጋሮቻቸው/ ላይ "የይሙት በቃ!" ፍርድ በአደባባይ ሲሰጡ የነበሩ "አቃጣሪ! አጨብጫቢና አድር ባይ" ጋዜጠኞች ዛሬም የሙያ ማህበራት መሪዎች ሆነው ስለ ጋዜጠኝነትና የጋዜጠኞች መብት መከበር "በፅናት ቆመን እንታገላለን" ሲሉ መስማት አስገራሚም አሳፋሪም አስደንጋጭም ነው።**

በወያኔ ዘመን ሙያቸውን በተራ ጥቅም ለውጠው የገዛ ወንድሞቻቸው /የሙያ አጋሮቻቸው/ ላይ "የይሙት በቃ!" ፍርድ በአደባባይ ሲሰጡ የነበሩ "አቃጣሪ! አጨብጫቢና አድር ባይ" ጋዜጠኞች ዛሬም የሙያ ማህበራት መሪዎች ሆነው ስለ ጋዜጠኝነትና የጋዜጠኞች መብት መከበር "በፅናት ቆመን እንታገላለን" ሲሉ መስማት አስገራሚም አሳፋሪም አስደንጋጭም ነው።

ግፈኛውን የወያኔ ጨካኝ ስርዓት በኢትዮጵያውያን ጫንቃ ላይ ገፍቶ ለመጣል ይደረግ የነበረውን የህዝቦች መራር ትግል በፅናት ቆሞ ይደግፍ የነበረውንና በርካታ ቁጥር ያላቸው አባላቱ ለሞት፣ ለእስርና ስቃይ፣ ለአካል ጥቃትና ለስደት የተዳረጉበትን፤ ፕሬዝዳንቱን ጨምሮ አብዛኞቹ አመራሮች ለህይወታቸው ሰግተው በግድ የተሰደዱበትን የቀድሞውን የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበርን (ኢነጋማ) ለማፍረስ በበረከት ስምኦን አዝማችነት በተካሄደው ፀረ ዴሞክራሲ ዘመቻ ውስጥ በፊት መሪነት ተሠልፈው የነበሩና የተከፈተበትን መጠነ ሰፊ የስም ማጥፋት ሴራ በሙሉ አቅማቸው ያግዙ የነበሩ "አረሞች!" ዛሬም "በለውጡ ዘመን" ስለጋዜጠኛና ጋዜጠኝነት መብት መከበር ሲናገሩ ማድመጥ አሳፋሪ፣ አስፈሪና አስደንጋጭም ነው። የእውነት ይህን መስማት ያማል። ከዚ ሁሉ ግፍ በኂላ ምንም እንዳልተፈጠረ ሆነው መድረኩ ላይ ለመውጣት መድፈራቸውም እንደ ታላቅ ንቀት የሚቆጠር ነውና የሚጭረው የሀዘን ስሜት ከባድ ነው።

በርግጥ ይሄ ሁኔታ ይበልጥ የሚገባቸውና ህመሙ የሚሰማቸው ከብዙኃኑ ህዝብ አንፃር ቁጥራቸው ጥቂት ይመስል ይሆናል። ግን አይደለም። የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ያንን ሁሉ መከራ ሲቀበሉ የኖሩት ለመላው ህዝብ ነፃነት፣ እኩልነትና አንድነት እንጂ ለግል ጥቅማቸው ወይም ለተወሰኑ ቡድኖች ምቾት ብለው አልነበረም። የብዕር አርበኞቹ የሞትን መራር ፅዋ የተጎነጩት፣ በየእስር ቤቱ ለስቃይ የተዳረጉት፣ ለአካል ጉዳት የተጋለጡት፣ ከማህበራዊ መብቶቻቸው የተገለሉት፣ በፍርሃትና ዛቻ ውስጥ መኖርን እንዲጠየፉ የሆኑትና የሚወዷት ሀገራቸውንና ቤተሰባቸውን ጥለው በግፍ የተሰደዱት በህዝቦች ላይ የሚደርስ በደልና ጭቆና እንዲቆም የአንድ ብሔር የበላይነት እንዲከስም የሀገር ሀብት መዝረፉና ራቁት ማስቀረቱ እንዲያበቃ፤ ከዚህም ሁሉ በላይ ሁሉም ዜጎች እኩል መብት ነፃነትና ክብር እንዲኖራቸው ለማድረግ ብለው እንጂ በምንም የተለየ ምክንት አልነበረም። ይሄን ሀቅ ብዙሃን ኢትዮጵያውያን በሚገባ ያውቁታል። የጋዜጠኛው ሞት የእያንዳንዱ ዜጋ ሞት ነው፡ ፡ ለህዝብ ጥቅም መከበር ሲታገል የሚታሰርና የሚገረፍ፣ ከዚህም የከፋ ሰብዓዊ ጥቃት የሚደርስበት ጋዜጠኛ ህመሙን ከቆመለት ህዝብ ጋር ሲጋራው የኖረው ነው።

ስለዚህም የትኛውም የጋዜጠኞች ጉዳይ የጋዜጠኞቹ ብቻ የሚሆንበት ምክንያት የለውም፡ ፡ ይልቁንም ጉዳዩ የመላ ሀገሪቱ ህዝቦች ጉዳይ ሆኖ ሁሉም ጉዳዬ የሚለው ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን በኖረበት አገር፤ ያውም ብዙሃኑ የግፍ ሰለባዎች በህይወት ተርፈው ህያው ምስክሮች መሆን በሚችሉበት በዚህ ጊዜ፤ ይበልጡንም ደግሞ ግፈኞቹ በቆፈሩት ጉድጓድ ራሳቸው እየገቡበት ባለበትና በምንገኝበት፤ የመንግስት ሥርዓት ለውጥ እውን በሚሆንበት ጊዜ የጋዜጠኞቹን ማህበር አፈራርሰው ጋዜጠኝነት አሁን ላለበት ከፍተኛ ተዓማኒነትና ክብር ማጣት ከፊት ሆነው ሌላውን ሲመሩ የኖሩ "ደፋሮች!" ዛሬም ስለጋዜጠኛና ጋዜጠኝነት በድፍረት ሲናገሩ መስማት ከዚህም በላይ ለጋዜጠኞች መብት መከበር እንደሚሰሩ "አስመሳይ!" ንግግር ሲያደርጉ ማድመጥ በርግጥም ያማል! ያስደነግጣል! ያናድድማል!

የገዛ ጓደቹን ‹‹በ30 ዲናር የሸጠ ሆዳም›› የትኞቹ ጋዜጠኞች አባላቱ እንደሆኑ የማይታወቅን የነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር መሪ ነኝ ብሎ በድፍረት መድረክ ላይ ቆሞ ሲናገር ማድመጥ ከግል ስሜት ኮርኳሪነቱም በላይ ሌላ መሰረታዊ ጥያቄንም ያስነሳል።

በእነ ዶ/ር ዐቢይ የሚመራው የሥርዓት ለውጥ እንቅስቃሴ ይደረግ በነበረ ጊዜ በዛሚ ሬዲዮ የክብ ጠረጴዛ ፕሮግራም ለወያኔ ሲያጨበጭቡና ሲያቃጥሩ "መጣሁ መጣሁ" እያለ የነበረውን ለውጥም በሚችሉት ሁሉ ለማደናቀፍ ህዝብን በመረጃ ሲያሳስቱ የነበሩ አድርባዮች የጋዜጠኞች መብት ተሟጋቾች ሆነው በአደባባይ መታየታቸው በርግጥም አንድ መሠረታዊ ጥያቄን ይጭራል።

ይኸውም "በእርግጥ ወያኔ ወድቃለች ወይ? ሥርዓቱ ተውጧል ወይ?" የሚል ጥያቄ ነው። የለውጡ መንግስት ለውጡ እውን እንዲሆን የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ለከፈሉት ረጅምና መራር መስዋዕትነት እውቅና መንፈግ የፈለገም የሚያስመስል ነው። አንዳንዶች እንደሚሉት ለውጡን ያመጣነው እኛ ብቻ ነን የሚል "የኬኛ" ፖለቲካ ሠላባ የመሆኑን እውነት በብርቱ እንድንጠረጥር የሚያደርገንም ነው።

በሰሩት ጥፋትና የበረከት ስምኦንን ትዕዛዝና እቅድ ለማስፈፀም በሄዱበት ርቀት ልክ በህግ ጭምር ተጠያቂ መሆን የሚገባቸው ‹‹ሆዳሞች!›› ራሳቸውን የጋዜጠኛ ማህበራት መሪዎች አድርገው መቀጠላቸውና በመንግሥትም ስፖንሰር እየተደረጉ ያሉበት ሁኔታ ወደፊትም ገና ብዙ የምንነጋገርበት ሲሆን፣ በዚህ አጋጣሚ ግን መንግሥትንም "እረፍ!" ማለት ተገቢ ይመስለኛል። የሥርዓት ለውጡ እውነተኛነት ላይ ከባድ ጥላ የሚጥልበት ጉዳይ ስለሆነ ጋዜጠኞችን ሲያራክሱና ሲያስመቱ የነበሩ አቃጣሪዎችን ጉዳይ በጥንቃቄ መመርመር ይኖርበታል።

## እንዳርጋቸው... ከገፅ 27 የዞረ

### 3. የሰላማዊ ትግል ወሳኝነት

ግንቦት 7 ንቅናቄ አመጽንም ጭምር ያካተተ የትግል ስልት በስራ ላይ ለማዋል የወሰነው ምርጫ ስላልነበረው ነው። ሰላማዊና ህጋዊ የሆነው የፖለቲካ ምህዳር በወያኔ ሲዘጋ ምርጫው በባርነት መኖር ወይም መሳሪያ አንስቶ ለነፃነት መታገል ነበር። ነፃነት ለመረጥነው ሁለገብ የትግል ስልት አመጽን ጨምሮ ማካሄድ የግድ ነበር። ወደፊትም ቢሆን አንድ ህዝብ ነፃነቱን ማስከበር የሚችልበት ሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ከተዘጋ ያዋጣል ብሎ ባሰበው መንገድ ሁሉ ለነፃነቱ የሚታገልበትን የትግል ስልት፣ መብቱን የገፈፉት ሀይሎች፣ ወያኔ እንዳደረገው ሊነግሩት መብት የላቸውም ብዬ አምናለሁ። ሆኖም ግን የአመጽ ትግል እንዲህ በቀላሉ የሚመረጥ ጉዳይ መሆን የለበትም። በተለይ በሀጋራችን ሁኔታ፣ ከሌላ ሀገር በበለጠ የአመፅ ትግል ሀገርና ህዝብን አደጋ ላይ የሚጥል ሊሆን እንደሚችል በቂ መረጃ አለን። ወያኔን ለማስወገድ በአንድ ቦታ የሚጀመር የአመጽ ትግል ሀገርና ህዝብን አደጋ ላይ የሚጥል ሊሆን እንደሚችል በቂ መረጃ አለን። ወያኔን ለማስወገድ በአንድ ቦታ የሚጀመር የአመጽ ትግል በቋፍ ላይ በነበረው ሁኔታ የተነሳ በመላው ሀገሪቱ አመጽ እንዲቀጣጠልና በሺዎች የሚቆጠሩ የሽፍቶች አለቃ በየቦታው እንዲፈሉ በማድረግ ሀገሪቱን ገሀነብ ሊያደርግ የመቻል እድሉ ሰፊ ነበር። የዘርና የድህነት ፖለቲካ አንድ ላይ ሲደመሩ ደግሞ ገሀነቡን የከፋ ሊያደርጉት እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል።

"አግ7 ጀምሮት የነበረው የአመጽ ትግል ተስፋፍቶ ቢሆን ኖሮ ምን ሊያስከትል ይችል ነበር?" የሚል ጥያቄ ሳነሳ ስጋት የሚሰማኝ ለዚህ ነው። ዕድለኞች ሆነን ያለብዙ ደም መፋሰስ ውሉና ማለቂያው ምን እንደሆነ በማይታወቅ የአመጽ ትግል ሀገሪቱ ሳትጥለቀለቅ ለውጥ በሀገራችን ተከስቷል። ይህ ለውጥ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ለመታገል እድል ከፍቷል። በሀገራች ሁኔታ የዚህን እድል ታሪካዊ ትርጉም አሳንሰን ማየት የለብንም።

ሰላማዊና ህጋዊው የፖለቲካ ምህዳሩ እንዳይጠብ፣ እንዳይሰናከል ከምራችን ሁላችንም ሀላፊነታችንን መወጣት ይገባናል። ይህ እንደ አዲስ የተከፈተ የፖለቲካ ምህዳር አልጋ በአልጋ እንደማይሆን ይታወቃል። ነገር ግን በአመጽ ይመጣ ከነበረው ለውጥ መዘዝ ጋር ስናነፃፅረው የገጠመንና የሚገጥመን ችግር ከባድ አይደለም። የሰላማዊና ህጋዊ የፖለቲካ ምህዳሩን ጤንነት የማስጠበቅ ሀላፊነት የተፎካካሪ ድርጅቶች ብቻ የሥራ ድርሻ እንዳልሆነ እናውቃለን። እኛ የድርሻን በሚገባ እየተወጣን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ይህንን ምህዳር በመንከባከብ የራሱን ሀላፊነት መታገል ይኖርብናል።

ሌላው የሰላማዊና ህጋዊ ትግል አማራጭ ትልቅ ትርጉም ያለው ለፖለቲካ ድርጅቶችም ጭምር ነው። የሚስጥር ድርጅት የፈለገውን ያህል ቀና መሪዎችና አሰራሮች ቢኖሩት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሊሆን አይችልም። በዚህ የተነሳ ግልፅነትና ተጠያቂነት ሙሉ በሙሉ በእንዲህ አይነት ድርጅት ውስጥ መስፈን አይችልም። እንዲህ አይነት ድርጅት ከውስጥም ከውጭም ለሚመጡ አሉባልታዎች የተጋለጠ ነው። "መሪዎች ወይም አባላት አስቸጋሪዎች ሆነው ከድርጅቱ ከተባረሩ ድርጅት የሚጎዳ ሚስጥር ያወጣሉ" በሚል ስጋት ስብዕና የሌላቸው በብዙ እንከኖች የተሞሉ ግለሰቦችን ተሸክሞ እንዲሄድ ድርጅቱ ይገደዳል። በተለይ በእንደኛ ዓይነቱ ዴሞክራሲ ለመመስረት በሚውተረተር ሀገር ውስጥ ድርጅቶች ገና ከመነሻው በሚስጥር አሰራር የተነሳ ዴሞክራሲያዊ እንዳይሆኑ መሆናቸው ትልቁ ጉዳት ያስከትላል። የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የሚጀምረው ዲሞክራሲያዊ ድርጅት በመፍጠር እንደሆነ እየታወቀ፤ በሚስጥር ስራ ስም ተገዶ ፀረ ዴሞክራሲያዊ ባህልና ድርጊቶች በአንድ ድርጅት ውስጥ መፍቀድ መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል ግልፅ ነው። በዚህ የተነሳ ህጋዊና ሰላማዊ ትግል ለዴሞክራሲ ግንባታ ወሳኝ መሆኑን እንረዳለን። አዲሱ ፓርቲ ይህ ተረድቶ ለ ሰላምና ለህጋዊነት ምቹ ሊሆን ይገባዋል እንላለን።

### 4. በአርያነት የመምራት ትርጉም

መሪዎች የሚናገሩትን መኖር መቻል አለባቸው። መሪዎች የሚያስቀምጡትን መመሪያ ለመፈፀም የመጀመሪያ መሆን አለባቸው። መሪዎች በጣፈጠ ቋንቋና በስሜት ለሚያቀርቡት ራዕይ በቅድሚያ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለባቸው። በተለይ ከንቅናቄያችን ተመክሮ የተረዳነው ነገር ቢኖር በአርያአነት የሚመሩ መሪዎች ከሚመሩት አባል ጋር በቅርበት በመገናኘትና መስራት አለመቻላቸው አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ነው። በተለይ ወያኔን በመሳሪያ ጭምር መታገል ይኖርብናል የሚል አቋም ወስዶ የመሳሪያ ትግሉ በሚደረግበት ምድር ተገኝቶ የሚገነባውን ሰራዊት ገና ከጅምሩ በፖለቲካ፣ በሞራል፣ በአስተሳሰብ፣ በዲሲፕሊን፣ ማነፅ ካልተቻለ ምን ያህል አደገኛ ሁኔታ መፍጠር እንደሚቻል በተጨባጭ ያየነው ጉዳይ ነው። ለላቀ አላማ በጁ የገባን መሳሪያ የገዛ ጓዱን ማስፈራሪያ፣ ውሎ አድሮ እድል ቢያገኝ ነፃ አወጣዋለሁ ብሎ የተነሳለትን ህዝብ መጨፍጨፍና መዝረፊያ ሊያደርግ የሚችል ጭራቅ ሰራዊት መፍጠር እንደሚቻል ሁላችንም የምናውቃቸው በቂ መረጃዎች አሉን።

ሰላማዊና ህጋዊ ሁኔታ ውስጥ የሚደረግ ትግል እንዲህ አይነት አደጋ በውስጡ የሌለው ቢሆንም ለድርጅታቸው ራዕይ መሳካት ሌት ተቀን ሲደክሙ፣ በሁሉም መስክ ከማንም በላይ የድርጅትን አቅምና ብቃት ለማሳደግ እረፍት የለሽ ህይወት ሲገፉ በአርአያነት የሚታዩ በርካታ መሪዎች የሌሉት ድርጅት የትም አይደርስም። በስራ ትጋት ብቻ አይደለም፣ በቀን ተቀን ህይወታቸው የሚመሩትን አብዛኛው ህዝብ የማይመስሉ፣ ትዕግስት፣ ትህትና፣ ሆደ ሰፊነት ያላቸው በርካታ መሪዎች የሌሉት ድርጅት ፍፃሜው ምን ሊሆን እንደሚችል ግልፅ ነው።

የሚኖርበትን ወረዳ የፓርቲ ስራ የሚንቅ የድርጅት መሪ ሌሎችም አባላት ወረዳቸውን እንዲንቁ የሚያደርግ ነው። በየወረዳቸው ቤት ለቤት እየዞሩ አባላትን ለማሰባሰብ ጥረት ሲያደርጉ የማይታዩ መሪዎች፣ "ቤት ለቤት እየዞራችሁ አባላት መልምሉ" ቢሉ ከምር እንደማይወሰዱ ማወቅ አለባቸው። ሰላማዊ ሰልፍ ጠርተው ከፊት የማይቀድሙ መሪዎች ወይም ፈፅሞ በሰልፉ የማይገኙ መሪዎች ተመሪ የሌለው ድርጅት ታቅፈው ብቻቸውን እንደሚቀሩ የታወቀ ነው።

የጉልት ነጋዴዋን ለድርጅት ገንዘብ አውጭ የሚል መሪ አንድ ሳንቲም የድርጅት ገንዘብ አላግባብ ሲያጠፋ ፈፅሞ መገኘት የሌለበት ብቻ ሳይሆን፣ ማዋጣት ከሚገባው በላይ አዋጥቶ በተግባር ካላሳየ በግብዝነት ቢላዎ የሚመራውን ድርጅት እየገዘገዘ የሚያርድ ነው። በተለይ ዛሬ በሀገራችን ተናጋሪ በበዛበት፣ አድማጭ በጠፋበት ዘመን አባላትንና ህዝብን ማሳመኛው መንገድ በምሳሊያዊነት መምራት ብቻ ነው። በጦር ሜዳ አንድ ሰራዊት ከቆመለት አላማ ይበልጥ ለአዛዡ ካለው ፍቅር ከምር እንደሚዋጋ ተደጋግሞ ታይቷል። በሰላማዊ ትግልም ልዩነት የለውም። በመሪዎቻቸው መልካም ስብዕና ተስበው ሚሊዮኖች አንድ ድርጅት እንዲቀላቀሉ ብሎም አንድ ድርጅት የሚጠይቃቸውን ማናቸውንም መስዋዕጥነት ሊከፍሉ በታች ወርደው በቀበሌ ጭምር የድርጅት ሀላፊነት ለሚይዙት ሁሉ የሚያስፈልግ ጥበብ ነው። መሪ መሪ ነው። በሀገር ደረጃም ይሁን በቀበሌ።

ከዚህ መስራች ጉባኤ በፊት በዛሬው ጉባኤ ለመገኘት ድርጅታቸውን አክስመው ዝግጅት ካደረጉ የቀድሞ 6 ድርጅቶች መሪዎችና የተወሰኑ አባላቶቻቸው ጋር ለመተዋወቅ እድል አግኝቻለሁ። ሁሉም ካለፈ የውድቀት ታሪካችን የተማሩ ለመሆናቸው በጋራ ለመስራት ባሳዩት ቅንነት መረዳት ትችላላችሁ። ከዚህ ዘመን በፊት የማይታሰብ የአላማ አንድነትና ሥምምነት ላይ የተደረሰው በሚገርም አጭር ጊዜ ውስጥ ነው። ለዚህ ታሪካዊ ወሳኝ ጉባኤ መብቃት በተዓምር ደረጃ የሚቆጠር ነው።

ለጉባኤተኞች የማስተላልፈው መልዕክት የሀገራችን ችግር የመሪዎች ችግር ብቻ አይደለም። የተመሪዎችም ችግር ነው። በቀደሙት ዘመናት ተመሪዎች መብታቸውን በነሀስ ሳህን ለመሪዎች እያስረከቡ በራሳቸው ላይ አምባገነኖች እንዲሰለጥኑባቸው ያደርጉ ነበር። የአሁኑ ዘመን ችግር ደግሞ ሌላ ሆኗል። ሁሉም መሪ መሆን ስለሚፈልግ ተመሪ የጠፋበት ሁኔታ ውስጥ ገብተናል። ለመነዳት የተዘጋጁ አባላት እጣቸው ባርነት እንደነበር ሁሉ ለመመራት ዝግጁ ያልሆኑ አባላት ከሚነዱት አባላት የከፋ እንጂ የተሻለ እጣ እንደማይጠብቃቸው ማወቅ አለባቸው። ሁሉም መሪ መሆን ስለማይችል መሪ የተመረጠ ብቻ ይሁን ብለናል። በተመረጠ መመራት የሰለጠነ ድርጅት ባህል ነውና ይህን ባህል እንላበስ እላለሁ።

## ውድ ወገኖቼ

በመጨረሻም

በሀገር ውስጥና በመላው አለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የዛሬውን ጉባኤ ውጤት በጉጉት እየጠበቁ ነው። አዲሱ ፓርቲ በእውንም የገበሬው፣ የላብአደሩ፣ የመምህሩ፣ የሰራዊቱ፣ የመንግስት ሰራተኛው፣ ጥሮ ግሮ ሃብት የሚያፈራው ባለሀብት፣ የምሁሩ፣ የባለሙያው፣ የወጣቱ፣ የሴቶች፣ የአካል ጉተኞች በየውጭ ሀገሩ ስራ ፍለጋ ካገሩ ተገፍቶ የተሰደደው ኢትዮጵያዊ፤ የፓርቲ መብትና ጥቅም አስከባሪ የሚያደርገው የፓርቲ ፕሮግራምና አደረጃጀት እንዳለው አውቃለሁ። ለእምነቶች ፣ለቋንቋዎች፣ ለባህሎች መከበርና መበልፀግ የቆመ ፓርቲ እንደሆነ አውቃለሁ። በማህበራዊ ፍትህ በተቃኘው ፕሮግራሙና አሳታፊ ዴሞክራሲን የህልውናው መሰረት ባደረገው ድርጅታዊ ቁመናው አማካይነት የሀገርንና የህዝብን የነፃነት፣ የዴሞክራሲ፣ የፍትህ፣ የሰላምና የብልፅግና ጥም ማርካት የሚያስችል ታሪካዊ ስራ ሊሰራ እንደሚችል እምነቴ ነው። የዚህ ታሪካዊ ስራ የመጀመሪያው እርምጃ በዛሬው እለት ይጀመራል። ይህን ጉበኤ በአርቆ አሳቢነት ከግል ስሜትና ፍላጎት ውጭ ሀገርንና ወገን ብቻ እያያችሁ በስኬት አጠናቃችሁ አዲስ ታሪክ ፃፉ።

***ዘላለማዊ ክብር ለዚህ ዕለት ላበቁን ሰማዕታት!***
***ኢትዮጵያ ለዘላለም በክብር ትኑር!***
***አመሰግናለሁ!***



ነአምን ዘለቀ

# አርበኞች ግንቦት 7 ንቅናቄ መክሰምና ሀገራዊ የዜግነትና የማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ ምስረታ

ዛሬ ታሪካዊ ቀን ነው። አርበኞች ግንቦት 7 አባላት በሀገራችን ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ለመጨረሻም ባደረገው ጉባኤ ንቅናቄው መክሰሙ ይፋ ተደርጎአል። በጉባኤው ላይ ለተሳተፋችሁም፣ ለመሳተፍ ያልቻላችሁም የንቅናቄያችን አመራሮችና አባላት ሁሉ ያለኝን አድናቆትና አክብሮት በድጋሚ ለመግልጽ እወዳለሁ። በርካታ ድንቅዬ ኢትዮያጵያውያን ጀግኖች የማየተካውን ህይወታቸውን ለፍትህ፣ ለነጻነት፣ ለኢትዮጵያ አንድነት የገበሩበት፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጀግኖች በየእስር ቤቱ የማቀቁበት፣ አካለ ጎዶሎ ለሆኑበት፣ በሺዎች በሀገር ውስጥም በውጭው አለም ብዙ ብዙ የደከሙበትና መስዋእትነት የከፈሉበት ይህ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ውስጥ ሰፊና ጉልህ ሚና የነበረው የአግ 7 ንቅናቄ፣ ዛሬ ላይ ለደረስንበትም ብዙ ተግዳሮቶች ያሉት ነገር ግን ተስፋ ሰጪ ለውጥ የራሱን ከፍተኛ አሰዋጽኦ ማድረጉ ግልጽ ነው። የንቅናቄው አባልና አመራር ሆኜ የድርሻዬን ለትግሉ በማበርከቴ ከፍተኛ የሆነ የህሊና እርካታ ይሰማኛል። ምንም እንኳን ከዚያ በቀደሙ በርካታ አመታት በልዩ ልዩ የትግል መድረኮች ያልተቋረጠ እንቅስቃሴ ባደርግም በአርበኞች ግንቦት 7 ውስጥ ያደረኩት ሁለንተናዊ አስተዋፅኦና የትግል ድርሻ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል ለማለት እችላለሁ።

ጉባኤው ከመደረጉ በፊት የንቅናቄው ሁለት የስራ አስፈጻሚ አባላት መልቀቃቸውን ይፋ ካደረጉ በኋላ በስልክም በመልእክት ሳጥንም ጥያቄ የጠየቃችሁኝ ነበራችሁ። በዚህ አጋጣሚ የእኔን ምልከታ ለማካፈል እወዳለሁ። ሁለቱ የስራ አስፈጻሚ አባላት የለቀቁበትን ምክንያቶች ተመልክቼዋለሁ። ኮማንደር አሰፋ ማሩ በጣም የማከበርው፣ ገና ከጅምሩ ንቅናቄው ወደ ኤርትራ ትጥቅ ትግል ለመጀመር ሲገባ ጀምሮ ለትግሉ ከፍተኛ መስዋእትነት የከፈለ፣ የወታደራዊ ዘርፉ ዋና አዛዥና የስራ አስፈጻሚ አባል በመሆን ብዙ አስተዋጽኦ ያደረገ ጓድ ነው። ጨዋ፣ ትሁት፣ ሰው አክባሪ፣ ትግስተኛ፣ ትጉህ ሰራተኛ፣ አስተዋይ ሰው ስለመሆኑ ለመመስከር እችላለሁ። ወደ ኤርትራ በረሃ ስመላለስ ለሰራዊቱ የፖለቲካና የወታደራዊ ስልጠናዎች ከመስጠትም ሆነ ከሌሎች ተግባራት ጋር ተያይዞ በጣም ተቀራርበን ሰርተናል። ጓን ከበድ ዘሪሁን፣ በመጨረሻው ጉባኤ ወደ ስራ አስፈጻሚ ኮሜቴ ተመርጦ የጽ/ቤት ሃላፊ በመሆን ያገለገለ፣ በጣም ጠንካራ ሰራተኛና ፈጣን አምሮ ያለው ስለመሆኑ መመስከር እወዳለሁ። ነገር ግን ጓን ከአንዳርጋቸው ጋር የተደረገን የግል ንግግር ሚዲያ ላይ ማውጣቱ በጣም እንዳሳዘነኝና በፍጹም ያልተጠበኩት መሆኑን ሳልገልጽ ለማለፍ አልፈልግም።

ሁለቱም የንቅናቄው የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያነሱዋቸው ጉዳዮች ላይ በዝርዝር ገብቼ ይህ ልክ ነው፣ ያኛው አይደለም ወደሚል ሙግት ለመግባት አልፈልግም፣ ይህ ምንም ለማንም የሚጠቅም አይደለም። በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ንቅናቄውንና አመራሩን ለማጠልሸት ለሚፈልጉ ዳግም እድል ለመስጠት አልፈልግም። አንድ ጉዳይ ግን ከእነሱ ጋር የምጋራው አለ፤ ጥያቄ ስትልኩልኝ ለነበራችሁ መልስ ይሆናል የሚል ተስፋ አለኝ። ይሄውም ከሰራዊቱ መልሶ ማቋቋም ጋር በተያያዘ ሁለቱም ሆኑ በርካታ የንቅናቄው አባላት በተደጋጋሚ የሚያነሱት ከባዱ ጉዳይ ነው። የንቅናቄውን ውስጣዊ ጤንነት የተፈታተነ፣ ስሜቶች እንዲሻክሩ፣ ብሎም እኔም ሆኑኩ ሌሎቹ እንዲለቁ መንስኤ የሆነው በዋነኝነት ሊነሳ የሚችለው ማእከላዊ ችግርና ምክንያት ከዚህ ጋር የተገናኘው ጉዳይ ነው ብዬ አምናለሁ። የሚከተሉትን ነጥቦች ላስቀምጥ፦

1. ከጅምሩ ሰራዊቱ እንዴት፣ መቼ፣ በምን ሁኔታ መልሶ እንደሚቋቋም መከተል የሚገባን ሂደትና እርምጃዎች በሚመልከት በደምብ የታሰበበት አለመሆኑ፣ ከለውጡ መሪዎች ጋር የሰራዊቱ ዲሞቢላይዚሽና መልሶ ማቋቋም፣ የአግ 7ን ወደ አገርቤት መግባትና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ድርድር በተደረገበት ጊዜና ከዚያ በኋላ በዝርዝር ተቀምጦ የመግባቢያ ሰነድ በአለም አቀፍ ደረጃ እንደሚደረገው አለመፈረሙ።

2. ሆናም በኤርትራ በርሃ በተደረገ ጉባኤ ላይ ሰራዊቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚቋቋም (2-3) ወር ጊዜ ተብሎ መነገሩ፣ ቃል መገባቱ። ለዚህም ንቅናቄው ሳይሆን አፍሪድ የሚባል የበጎ አድራጎት ድርጅት ጉዳያቸውን እንደሚከታተል በጉባኤ መነገሩ።

3. ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገቡ የተቃዋዊ ድርጅቶች ታጣቂዎችን በሚመለከት በባለቤትነት የሚሰራ የመልሶ ማቋቋም ጽ/ቤት በጠቅላይ ሚኒስትሩ በዶ/ አብይ አህመድ ይቋቋም እንጂ፣ ያለምንም ተቋማዊ ብቃትና በቂ የፕሮግራምና የፕሮጀክት ሙያተኞች ያልተመደቡለት፣ በግማሽ ጊዜ የሚሰራ ሃላፊና ጸሃፊ ብቻ ያሉት አቅመ ቢስ ተቋም መሆኑ። ይህ ደግሞ የገቡትን የአግ 7 ንም ሆነ የሌሎች ሃይሎች ሰራዊት አባላት መልሶ ለማቋቋም የጀርመን መንግስት ቃል የገባውን መጠነ ሰፊ ገንዘብ ለመስጠት እንደማይፈልግ፣ ምክንያቱም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አቅመ ቢስ መሆኑና እምነት እንደሌላቸው ጀርመኖች በግልጽ የነገሩን ሁኔታ ስለነበር።

4. ይህ የመልሶ ማቋቋም ሂደት መጓተት በሰራዊቱ ውስጥ የፈጠረው ጭንቀት በሌሎቻችንም ላይ እየተጋባ የውዝግብ መንስኤ መሆኑ።

5. ሁኔታው እንዲስተካከል በሊ/መንበሩ፣ በዋና ጸሃፊው፣ እኔም በበኩሌ ከመንግስት አካላት ጋር ያደረግናቸው ጥረቶችና ጉትጎታዎች ውጤት ሳያስገኙ መቆየታቸው፣ ጠ/ሚንስትሩ ዶ/ር አብይ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥበት በርካታ ወራት ፈጀ። ማለትም ማንዴቱ ከመልሶ ማቋቋም ጽ/ቤት ወደ ብሄራዊ አደጋ መከላከል ኮሚሽን እስኪዛወርና ስራዎች እስኪጀመር ድረስ 2-3 ወር የተባለው 8 ወራት ፈጅቷል። ውሳኔው የተሰጠው በማርች ወር አጋማሽ ውስጥ እኔ ኢትዮጵያ እያለሁ ነበር።

6. ያም ሆኖ የሰራዊቱ የመልሶ ማቋቋም ስልጠናና እንዲሁም የመቋቋሚያ ድጎማዎች ገና በጅምር ላይ ናቸው። በመሆኑም በሆረታ ካምፕ፣ ጎንደር የሚገኙት የሰራዊት አባላት አግ7 ላደረገው የመክሰም ጉባኤ በዚሁ ሳቢያ ተወካዮች እንዳልላኩ ነው የምረዳው። ቢያንስ ሁሉንም በጋራ የሚወክሉ አባላት መርጠው ለመላክ እንዳልፈቀዱ ነው የሰማሁት። (እኔ በጃንዋሪ አጋማሽ የሄድኩኝ ጊዜ፣ አቶ አንዳርጋቸውም ከሁለት ሳምንት ከእኔ ቀድሞ በሄደ ወቅት የነገርናቸው፤ ጉዳያቸው ከሁለት ወር ባነሰ ጊዜ እንደሚጀመር ነበር።)

7. ለዚህ ለገባንበት ሁኔታ ተጠያቂው ሁላችንም እንደአመራርና አባላት ሀገር ውስጥ ከመገባቱ በፊት በተደረገው ጉባኤ ላይ ያደረግናቸው ውሳኔዎች መንስኤ ይመስሉኛል። ውሳኔዎቹና አማራጮቹ ምን መሆን ነበረባቸው ወደሚለው ለመግባት አልሻም። በተለይም ግን በሰራዊቱ ዲሞቢላይዜሽናን መልሶ ማቋቋም ላይ የተደረገው ውሳኔ ሲታይ ቢሆንስ ወይን ባይሆንስ (possible scenarios) የሚሉትን በደምብ ያላገናዘበ ነበር። “ምንም ሌላ ስራ የለም፤ ዋናው ስራ የፓርቲ ማቋቋም ስራ ብቻ ነው” የሚል አመለካከት በአመራሮች አካባቢ በመስፈኑም ጭምርና የሰራዊቱን ጉዳይ ሰብ ኮንትራክት አፍሪድ በሚል ለተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅት ተሰጠ ቢባልም በወቅቱ አፍሪድ በጠቅላይ ሚንስትሩ ጽ/ቤት ስር የተቋቋመውን የፕሮጄክት ጽ/ቤት በሰራዊቱ መልሶ ማቋቋም ዙሪያ ለመርዳት ሲሞክር በሩ ተዘግቶበት ምንም ማድረግ እንዳይችል የተደረገ ድርጅት ነበር በወቅቱ።

8. የአግ 7 ሰራዊት መልሶ ማቋቋም እንደ አንድ ዋና ጉዳይ በጋራ ሃላፊነት የነበረበትና ሰራዊቱ ጭምር የመረጣቸው የስራ አስፈጻሚ አባላት ቢያንስ የሰራዊቱ መልሶ ማቋቋም እስኪጀመር በባለቤትነት መንፈስ፣ በጋራ መነጋገርና አስፈላጊውን ለመወስን የሚያስችል ሁኔታ ስላልነበር ቀደም ሲል እንዳልኩት ሊመጡ የሚችሉ አዳዲስ ተግዳሮቶችና ችግሮች (unforeseen and emerging new conditions) ስላልታዩ፣ ችግሮቹም ሲመጡ ከጋራ ውሳኔና እንቅስቃሴ ይልቅ በጥቂት አመራሮች በተለይም ብዙ በተደራረቡ ስራና ውጥረት ውስጥ በነበሩ አመራሮች እጅ የሰራዊቱ ጉዳይ ስለተያዘም ጭምር ይመስለኛል። ለዚህም ነው በወቅቱ ይህ ጉዳይ እኔንም እንደአመራር ይመለከተኛል፣ ተጠያቂነትም አለብኝ፤ ብዙ የጭንቀት ድምጾች ከሰራዊቱ እየሰማሁ ነው በሚል ችግሩን ለመፍታት የግሌን ጥረት ለማድረግ ብዙ በሮችን ለማንኳኳት ጥረት ያደረኩት።

በእኔ ምልከታ ለዚህ ለተፈጠሩ ቅራኔዎችና ክፍተቶች ሌላው ምክንያት ደግሞ መደረግ የሚገባቸውን ውሳኔዎች ለመወሰን ዶ/ር አብይ አህመድና የሚመለከታቸው ባለስልጣኖች ብዙ ጊዜ ስለፈጁ ነበር። አስፈላጊው ውሳኔ በወቅቱ አለመወሰኑ፣ ማንዴቱ ወደ ሌላ ተቋም ወደ ብሄራዊ አደጋ መከላከልና መልሶ ማቋቋም ኮሚሽንም ከዞረ እስከአሁንም የተጨበጠ ውጤት አለመኖሩ (ከ 9 ወራት በሁዋላም) በንቅናቄውና በሰራዊቱ ውስጥ ሊፈጥር የሚችለውን መሻከርና ጤናማ ያልሆነ ሁኔታ ለማየት አለመቻሉም ጭምር ይመስለኛል።

በመጨረሻም አግ 7 በከሰመበት ጉባኤ 1ኛ- የሰራዊቱንና ተዛማጅ ጉዳዮች የሚከታተል ባለቤት ለማድረግ መወስኑ 2ኛ- እንዲሁም ሰፉ ያለ የንቅናቄው ሃብት ሰራዊቱ መልሶ እስኪቋቋም ድረስ ለሚያስፈልጉ ወጪዎች እንዲውል መወሰኑ በጣም ጥሩ እርምጃና ሁሉንም የውሳኔው ባለቤቶች የጉባኤ አባላትን በጣም የሚያስመሰግን ነው እላለሁ።

ለወደፊቱም ከእነዚህ መሰል ስህተቶች ቀጣዩና አዲሱ ፓርቲ ትምህርት እንደሚወስድ ተስፋ አደርጋለሁ። ለሚመሰረተው ሀገራዊ የዜግነትና የማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ በድጋሚ መልካም ምኞቴንና አጋርነቴን በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ።

ፖለቲካ

# አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ

# ስለ አዲሱ ፓርቲ ምን አሉ?



አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ግንቦት አንድ ቀን ሰባቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ውህደት በመጡበት ዕለት በኢትዮጵያ የስብሰባ ማዕከል ጉባዔ ላይ ያደረጉትን ንግግር እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

በቅድሚያ በመንግስት ደረጃ ፖሊሲ ተቀርፆ፣ ዜጎች ይገደሉ፣ ይታሰሩ፣ ተሰቅለው ይገረፉ፣ ይዘረፉ፣ ይሳደዱና ይሰደዱ የነበረበት የግፍ ዘመን አብቅቶ፣ እናንተም፣ እኔም፣ ሁላችንም፣ ያ ክፉ ዘመን በጋራ የመከራ ህይወት ያስተሳሰረን የኢትዮጵያ ልጆች በእንዲህ ዓይነት መድረክ ተገናኝተን ለዛሬው ቀን በመብቃታችን ፈጣሪያችንን አመሰግናለሁ።

በእነሱ ትከሻ ላይ ቆሜ ነውና የዛሬውን ድንቅና የነገውን ብሩህ ቀን እያየሁ ያለሁት፣ ይህን ቀን እንድናይ ሲሉ፣ ይህን ቀን እንዳያዩ ሆነው እስከ ወዲያኛው ላሸለቡት ጀግኖች ሰማዕታቶቻችን ለዘላለሙ በጋራ ማስታወሱን እንዳንረሳ አደራ እላለሁ።

በዛሬው ታሪካዊ እለት "የመክፈቻ ንግግግር ታደርጋለህ" የሚል መመሪያ ሲሰጠኝ ራሴን ብዙ ጥያቄ ጠይቄአለሁ። ብዙ መነገር ያለባቸው ነገሮች እንዳሉ አውቃለሁ። ለምን ንግግሩን የእናንተን ስሜት በሚቀሰቅሱ፣ ስለ አዲሱ ፓርቲ የወደፊት ብሩህ እጣ አልናገርም ብዬ ነበር። ግን ቀልቤ አልወደደውም። ለምን ስለ አዲሱ ፓርቲ ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ አልናገርም ብዬ አስቤ ነበር። እሱ ደግሞ የራሱ የጉባኤ የውይይት ነጥብ ነውና ዋጋ የለውም አልኩ። እንዳውም ውብ ፕሮግራምና መተዳደሪ ደንብ መቅረፅ በራሱ በቂ ስላልሆነ ሀሳቡን ናቅሁት። መጨረሻ ላይ የመጣልኝ ሀሳብ የብዙ አመታት የፖለቲካ ትግል ታሪክ ያለኝ ሰው ነኝና ለምን ከዚህ ተመክሮዬ የተወሰነውን በተለይ ለአዲሱ ፓርቲ ይጠቅማል ብዬ የማስበውን የሚያካፍል ንግግር አላደርግም ብዬ ወሰንኩ። በተለይ በሀገሪቱ ህግ የተነሳ በፖለቲካ ድርጅት ውስጥ መራጭም ሆነ ተመራጭ መሆን ስለማልችል ለዚህ አዲስ ፓርቲ ተመክሮዬን በመስራች ጉባኤው ላይ ባጭሩ አቅርቤ መሄዱ የተሻለ ነው ብዬ ወሰንኩ። ለዚህም ነው ወደ ዘመናችን ጠጋ ያለውን የቅርቡን የፖለቲካ ድርጅት ተመክሮዬን በምሳሌነት በማቅረብ የጉባኤ መክፈቻ ንግግሬን ለማድረግ የወሰንኩት። ንግግሬን በ4 መሰረታዊ ርዕሶች ክፍዬዋለሁ።

የአመራር የጋራ ራዕይ ወሳኝነት
ውህደት ያለመርህ አደገኛነት
የሰላማዊ ትግል ስልት ወሳኝነት
በአርአያነት የመምራት ወሳኝነት

## 1. የአመራር የጋራ ራዕይ ወሳኝነት

የአርበኞች ግንቦት 7 ንቅናቄ የሁለት ድርጅቶች ውህደት ነው። የግንቦት 7 ንቅናቄና የአርበኞች ግንባር ውህደት ነው። እዚህ ላይ በትምህርት መልኩ የማነሳው ከግንቦት 7 ንቅናቄ አመራር ጋር የተያያዘውን ቁምነገር ብቻ ነው። የግንቦት 7 ንቅናቄ የአመራር የጋራ ራዕይ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ የታየበት ድርጅት ነው። መሪዎች አላማቸው ከግል ጥቅምና ፍላጎት ያልተሳሳረ ከሆነ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታም ውስጥ እያለፉ አንድነታቸውን ጠብቀው መሄድ እንደሚችሉ የታየበት ድርጅት ነው። ይህ በተለይ ከአርበኞች ግንባር ጋር በውህደት የተቀላቀለው የግንቦት ንቅናቄ መሪዎች ድርጅቱ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ የዚህ ድርጅት አመራር አካላት የነበሩ ግለሰቦች ለ11 ዓመታት በአንድነት ለመዝለቅና በሀገራችን ታሪክ ያልተለመደ ባህል ትተው እያለፉ ነው። በተለይ ንቅናቄው በሚስጥር የሚሰራ እጅግ አስቸጋሪና ፈታኝ ውሳኔዎችን እየወሰነ የመጣ ድርጅት መሆኑን ግምት ውስጥ ስናስገባ መሪዎቹ በአንድነት መዝለቃቸው የበለጠ የሚያስገርም ነው።

የዚህ ክንዋኔ ሚስጥር አባላቱ የተሰባሰቡት ለአንድና አንድ አላማ ብቻ፣ ይህም ሀገርና ህዝብን ለመታደግ በመሆኑ ነው። በድርጅት ውስጥ ለሚያዝ ስልጣንና ጥቅም ወይም ትግሉም በድል ቢጠናቀቅ ከዚህ ድል የግል ስልጣንና ጥቅም የሚፈልጉ ግለሰቦች ባለመሆናቸው የተገኘ ውጤት ነው። የዚህ ተመክሮ ድምዳሜ የሚያሳየው የአንድ ድርጅት አባላት መሪዎቻቸውን ሲመርጡ ለግል ዝና፣ ስም፣ ክብርና ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጡ እንዳልሆኑ ማረጋገጥ እንደሚኖርባቸው ነው። በአንድ ድርጅት ውስጥ የሚሰባሰቡ መሪዎችም በምንም ዓይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ቢያልፉ ከግል ስሜታቸውና ፍላጎታቸው በላይ የገዘፈ ሀገራዊና ህዝባዊ አላማ ያላቸው መሆኑን መዘንጋት እንደሌለባቸው የሚጠቁም ትምህርት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የግል ስሜታቸውን ፍላጎታቸውንና ጥቅማቸው የሚያሳድዱ መሪዎች ያሉበት ድርጅት ሲጀመር ታግሎ አታጋይ መሆን የማይችል ይሆናል። በትግሉ ሂደት እየተሰነጣጠቀ መጨረሻው የምስኪን አባላቱን መስዋዕትነት ከንቱ ያስቀራል። በእንዲህ አይነት መሪዎች የተሞላ ድርጅት በአንድ አጋጣሚ ለድል ቢበቃም በግል ፍላጎትና ጥቅም የሚነዱ መሪዎቹ ውሎ አድሮ በህዝብ ቁጣ ተዋርደው ከስልጣን የሚወገዱበት ሁኔታ መፈጠሩ የማይቀር ነው። በሀገራችን ያየናቸው ሶስት የተለያዩ መንግስትታ መሪዎችና ባልደረቦቻቸው መጨረሻ አሳፋሪ የሆነው የራሳቸውን ጥቅምና ፍላጎት ከህዝብና ከሀገር ፍላጎትና ጥቅም በላይ በማድረጋቸው ነው። ሀገርና ህዝብ ሳያልፍለት በድርጅትና በሀገር መሪነት በሚገኝ ጥቅም ያልፍልኛል የሚል ስሌት መነዳት መጨረሻው ውርደት መሆኑን በመረዳት መሪዎች የራሳቸውን ፍላጎት ከህዝብ ፍላጎት መሟላት ጋር አቆራኝነተው ማየት እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው። በአርበኞች ግንቦት 7 ውስጥ እንዲህ አይነት አመለካከት የነበራቸው አባላት አልነበሩም ማለት አይደለም። በተለይ ግንቦት 7 ከአርበኞች ግንባር ጋር ያደረገው ውህደት ከተፈፀመ በኋላ የግል ፍላጎታቸውን በድርጅትና በአባላቱ ኪሳራ ብሎም በሀገርና በህዝብ ኪሳራ ለመግፋት የሞከሩ ግለሰቦች ብቅ ማለታቸው አልቀረም። ንቅናቄው እራሱን አክስሞ ከሌሎች ጋር ወደ ውህደት ሲመጣ በተለያዩ ሚድያዎች በአሁኑ ወቅት ከማንም በላይ ጎልቶ የሚሰማው ጩኸት የእነዚህ ግለሰቦች ጩኸት ነው።

ንቅናቄው ለዛሬው ቀን ቢበቃም እነዚህን በመሰሉ ሰዎች የተነሳ እጅግ ፈታኝ የሆነ የትግል ዘመን ማሳለፉን ሳናስታውስ አናልፍም።

## 2. ውህደት ያለመርህ አደገኛነት

ከአርበኞች ግንቦት 7 ተመክሮ የተገኘው ልምድ በጊዜያዊ ምክንያት ተገፋፍተው ድርጅቶች መርህ አልባ ጥምረት ወይም ውህደት ከፈፀሙ ምን አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንደሚወድቁ ነው። የአርበኞች ግንቦት 7 ውህደት የሁለቱ ድርጅቶች አመራርና አባላት ሰፊ የባህል የአመለካከትና የተግባር ልዩነት የታየበት በመሆኑ ብዙ ችግሮች ውስጥ የወደቀ ደርጅት ሆኖ ነበር። ውህደቱ የራሱ ፕሮፓጋዳ ጠቀሜታ የነበረው ቢሆንም በተግባር ንቅናቄውን ሽባ የሆነ ድርጅት እንዲሆን አድርጎት ነበር። አዲሱ ድርጅት ከዚህ መማር የሚገባው ነገር ቢኖር ውህደት ከሚፈጥራቸው ድርጅቶች ጋር ተመሳሳይ የፖለቲካ ባህል፣ አመለካከትና ራዕይ ያላቸው መሆኑን በጥብቅ መመርመር እንደሚገባው ነው። ሌላው የውህደቱ ትልቅ ትምህርት ድርጅቶች በጋራ እንሰራለን የሚል ስምምነት ሲደርሱ ስምምነቱ በመሪዎች ብቻ የተወሰነ እንዳይሆን የሚኖረውን ጠቀሜታ መገንዘብ ነው። ከላይ መሪዎች የተጣመሩበት ወይም የተዋሃዱበት ድርጅት መሪዎቹ በተለያዩ ምክንያቶች ቢጋጩ ድርጅቱን መልሰው ሰንጥቀው የየድርጅቶቻቸውን አባላት ይዘው ከውህደቱ እንዲወጡ የሚያስችላቸው መሆኑ ነው። በዚህ የተነሳ ድርጅቶች በጋራ ለመስራት ሲስማሙ ከጥምረት ይልቅ ውህደት ተመራጭ መሆኑ ነው። ውህደቱ ሁሉም የተዋሃዱ ድርጅቶችን አባላት ያካተተ የመሪዎች ምርጫ በማድረግ እንዲጠናቀቅ ማድረጉ ትልቅ ትርጉም ያለው ጉዳይ ነው። የተዋሃደውና በጋራ አመራሩን የመረጠውን ድርጅት በመሪዎች ግጭት በቀላሉ ለመሰንጠቅ ወይም ማፍረስ የማይቻል እንደሆነ የአግ7 ተሞክሮ ጥሩ ትምህርት ነው። እንዲህ አይነት ውህደት በመፈፀሙ አንዳንድ መሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከድርጅቱ ቢወጡም ድርጅቱ አንድ ሆኖ መቀጠል ችሏል። ይህ ተመክሮ የአዲሱ ፓርቲ የውህደት መርህ ሆኖ ተግባራዊ እየሆነ መሆኑ የሚማር ድርጅት እየተፈጠረ እንደሆነ በጎ ማሳያ ነው።

ቀሪውን በገፅ 27 ይመልከቱ